ከሐምሌ 2017
-
መስከረም 2018

ቅጽ. 101፣ ቁጥር 3

የሰንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት



## ክፍል ሦስት

# ወንጌል
# እንደ ዮሐንስ መሠረት

በክርስቶስ ስንኖር፣ ስለ እርሱ ስንል
ለመደሰት ሆነ ለመሰቃየት እንበረታለን።

የጎልማሶች የሰንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች
ክፍል ሶስት

# ወንጌል እንደ ዮሐንስ መሠረት

## በክርስቶስ በመኖር፣ ስለ እርሱ ስንል ለመደሰት ሆነ ለመሰቃየት እንበረታለን።

ከሐምሌ 2017 - መስከረም 2018 ጥራዝ. 101፣ ቁጥር 3

ማውጫ

1. የሱስ፣ ስምዖን እና ማርያም ............................................ 5
2. የድል አድራጊ አገባብ ............................................ 10
3. የሱስን ማየት እንፈልጋለን ............................................ 15
4. የአገልጋዮች አገልጋይ የሱስ ............................................ 20
5. መንገድ፣ እውነት እና ህይወት ............................................ 26
6. የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ ............................................ 31
7. እውነተኛው የወይን ግንድ የሱስ ............................................ 36
8. የወንድማማችነት ፍቅር ............................................ 41
9. የመንፈስ ቅዱስ ተልእኮ ............................................ 46
10. ክርስቶስ ስለ ደቀ መዛሙርቱ ጸለየ (1) ............................ 52
11. ክርስቶስ ስለ ደቀ መዛሙርቱ ጸለየ (2) ............................ 57
12. የክርስቶስ ለፍርድ መቅረብ ............................................ 62
13. ስምዖን ጴጥሮስ ............................................ 67

የሰንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ፣ የዕለት ተዕለት የጥናት መርሃ ግብር፣ ያለ ተጨማሪ አስተያየት በመጽሐፍ ቅዱስ እና በትንቢት መንፈስ ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው። ጥቅሶቹ እጥር ምጥን እንዲሉ እና ቀጥተኛ ሀሳቦችን ለማቅረብ በተቻለ መጠን አጭር እንዲሆኑ ተደርገዋል። ቅንፎች [] ግልጽነትን፣ ትክክለኛ አውድ እና ምቹ ተነባቢነትን ለማረጋገጥ በአንዳንድ ሁኔታዎች ተጨምሯል። ከምንጭ ላይ ተጨማሪ ጥናት ማድረግ በጥብቅ ይመከራል።

ምሳሌዎች ፡ አዶቤ ስቶክ በገጽ. 25፣ 72፤ የካርታ መርጃዎች በገጽ 4፣ 51፣ 72፤ የፊት ሽፋን ላይ የሰብከት እይታ

የቅጂ መብት © 2025 በሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ተሃድሶ እንቅስቃሴ አጠቃላይ ጉባኤ፣ የሰንበት ትምህርት ክፍል መምሪያ፣ 5240 ሆሊንስ መንገድ፣ ሮአኖክ፣ ቨርጂኒያ 24019፣ አሜሪካ።

ስልክ፡ 1-540-362-1800 • ድር፡ www.sdarm.org • ኢ-ሜይል፡ info@ sdarm.org

# መቅድም

በዮሐንስ ወንጌል መሠረት የወንጌል ትምህርቶችን ስንቀጥል ፣ ወደ የሱስ ምድራዊ አገልግሎት የመጨረሻ ቀናት መቃረብ እንጀምራለን። የትንቢት መንፈስ እንዲህ ይለናል፡- "በየቀኑ የተወሰነ ሰዓት ስለክርስቶስ ሕይወት ማሰላሰል ለእኛ ይበጀናል። የሕይወቱን ታሪክ በዘርፍ በዘርፉ አድርገ እያንዳንዱን ትዕይንት፤ በተለይ የሕይወቱን መደምደሚያ ታሪክ በአዕምሮ ዓይን ማየት ይገባናል። ለእኛ ያደረገልንን ታላቅ መስዋዕት የዚህን ያህል በጥልቀት ያሰብንበት እንደሆን፣ በእርሱ ላይ ያለን እምነት አይዋልልም። ፍቅራችን ይጸናል፣ መንፈሱም ጠልቆ ይሰርጽብናል። መጨረሻ ለመዳን ከፈለግን በመስቀሉ ሥር ሆነን የንስሐንና የትህትናን ትምህርት መማር አለብን።"—The Desire of Ages, p. 83.

ሐዋርያው ስለ እውነተኛው ጥናት የሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተገለጠበትን የመለኮታዊ ጥበብ፣ ፈቃድ እና ኃይል፣ በእርሱም የመዳን መንገድ ለሰዎች ሁሉ ስለተከፈተለት እና ስለተገለጠለት ስለየሱስ ክርስቶስ ማጥናት እንደሆነ ተናግሯል። የሱስ የሁሉ ነገር ፈጣሪ፣ የሕይወት ምንጭ፣ የዓለም ብርሃን፣ የአብ ማንነት ሕያው መገለጥ እንደሆነ ተጠቅሷል። የእግዚአብሔር ፈቃድ "ሁሉም ወደ ንስሐ እንዲደርሱ" (2ኛ ጴጥሮስ 3፡9)፣ የሚለው የበመንፈስ ቅዱስ ሥራ፣ በዮሐንስ ወንጌልም ተገልጧል፣ ከዚያም የሰው ልጅ እጣ ፈንታ ወደተወሰነበት ወደ ጌቴሴማኒ ይመራናል።

ከመጽሐፉ ዋና ዓላማዎች አንዱ የተበተኑት፣ ከየሱስ ጋር ምንም ዓይነት ግላዊ ግንኙነት ያልነበራቸው እና የአረማውያንን አስተሳሰቦች እያሳደጉ ያሉ ክርስቲያን አማኞች፣ እውነተኛውን ጥበብ እና እውነተኛውን ብርሃን እንዲያገኙ መርዳት ይመስላል። ሌላው የዮሐንስ ጽሕፈት ጠቃሚ ዓላማ ክርስቲያኖች በክፍለ ዘመኑ መገባደጃ ላይ በቤተ ክርስቲያኑ ላይ የሚደርሱትን አንዳንድ ችግሮችን እንዲጋፈጡ ማዘጋጀት ነበር፡ የድሮ እግዚአብሔርን መምሰል እየቀነሰ (ራዕይ 2፡ 4) እና የዓለም ፍቅር በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል እየገነነ መጥቷልና (1ኛ ዮሐንስ 2፡15)። እንደ ግኖስቲዝም ያሉ መናፍቃን መንጋውን እየወረሩ ነበር። ግኖስቲሲዝም ክርስቶስ የሰውን ተፈጥሮ ወሰዶ በእውነት በሥጋ መገለጡን ይክዳሉ። ግኖስቲኮች ሰዎች ክርስቶስን እንዳላዩት፣ ያዩት ነገር መገለጥ ብቻ እንደሆነ ያስተምሩ ነበር። ስለዚህ፣ በዮሐንስ 1፡14 ላይ የተገለጠው እውነት በተለይ በዚያ ዘመን ትልቅ ቦታ ነበረው። ቤተ ክርስቲያን እየተጋፈጠችው የነበረችው ሌላው አደጋ ከሮማውያን ባለሥልጣናት የሚደርስባቸው ስደት ነው።

የዮሐንስ ወንጌል ጥንት ለነበረችው የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ትልቅ እገዛ እንደነበረው ምንም ጥርጥር የለውም። ለዘመናት ለነበሩት የክርስቶስ ተከታዮች ታላቅ ረድኤት ሆኖላቸዋል - እንደዚሁም ዛሬ ለእኛም ትልቅ ረድኤት ነው።

በዚህ ተከታታይ ትምህርት ውስጥ ስንቀጥል የእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎቹ አምላክ ይስጠን!

የጄነራል ኮንፈረንስ ሰንበት ትምህርት መምሪያ

## የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ

## ሰንበት፣ ሰኔ 28፣ 2017




# በታሂቲ ለሚገኘው ለአሩ ቤተክርስቲያን

ብዙ ጊዜ ውብ ከሆነው ሞቃታማ እና ማራኪ መልክዓ ምድሮች ጋር የተቆራኘው የታሂቲ ደሴት በፈረንሳይ ፖሊኔዥያ ውስጥ ይገኛል፣ ይህ የፈረንሳይ የባህር ማዶ ግዛት 121 ደሴቶችን ያቀፈ በ1,359 ስኩዌር ማይል (3,418 ኪሎ ሜትር) ስፋት ያለው ሲሆን ከደቡባዊ ፓስፊክ ውቅያኖስ 1,242 ስኩዌር ማይል (2,000 ካሬ ኪሎ ሜትር) የሚሸፍን ቦታ ይይዛል።

ከታሪክ አንጻር፣ በእነዚህ በርካታ ደሴቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ብዙ አማልክታዊ እምነቶች አመለካከታቸው ፀሐይን ማምለክን፣ ሰው በላነትን (ካኒባልዝም) እና የመንፈስ አምልኮን ጨምሮ ብዙ አረማዊ ልማዶች እንዲፈጠሩ አድርጓል። በ1797 ወደ እነዚህ ደሴቶች የመጡ የብሪታኒያ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ባደረጉት ጥረት የክርስትና መግባት ለውጦችን አምጥቷል። በኋላም ፈረንሳዮች መጥተው በ1800ዎቹ መገባደጃ አካባቢውን በቅኝ ገዙ። በአሁኑ ጊዜ ወደ 279,000 ከሚጠጉ ነዋሪዎች መካከል 54% ፕሮቴስታንት፣ 38% ካቶሊክ ናቸው፣ የተቀሩት ደግሞ ሌሎች እምነቶችን የያዙ ናቸው።

በ1982 ከወንድም አልፍሬዶ ካርሎስ ሳስ ጉብኝት ጋር የተሃድሶ መልእክት ወደ ፈረንሳይ ፖሊኔዥያ ደረሰ። የመጀመሪያዎቹ አባላት፣ በአጠቃላይ 24 ነፍሳት፣ ከአንድ ዓመት በኋላ ተጠመቁ። የወንጌል መልእክት በደሴቶቹ ላይ መስፋፋቱን የቀጠለ ሲሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በርካታ የቤተክርስቲያን ቡድኖች ተመስርተዋል።

የሚያሳዝነው ዛሬም ድረስ በፈረንሳይ ፖሊኔዥያ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያናችን የራሷ የሆነ ቤተ ክርስቲያን (ሕንጻ) የላትም እና ወንድሞቻችን የሚገናኙት በተከራዩት ህንፃዎች ወይም በአባላት የግል ንብረት ላይ ነው። በእግዚአብሔር ቸርነት እ.ኤ.አ. በ2013 ከብዙ ጾምና ጸሎት በኋላ ከታሂቲ ፓፔቴ ከተማ 20 ኪ.ሜ ርቄት በሚገኘው በአሩ ቀጠና ተገዛ።

የዚህ ቤተ ክርስቲያን አነስተኛ አባላት ለብዙ አመታት የግል ጥቅምን መሠዋዕት በማድረግ ጥረቶችን አድርገዋል፣ በየሳምንቱ የቬጀቴሪያን ምግቦችን በማብሰል እና በመሸጥ ይህንን ንብረት መግዛት ችለዋል። ለዚህ መሬት ለመክፈል ጠንክረው የሠሩ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን አርአያነት ያለው ጥረት ቢያደርጉም በዚህ የምድር ታሪክ የመጨረሻ ቀናት የእውነትን መልእክት ለማዳረስ የሚረዳ ሕንፃ መሥራት ግን በእጅጉ አስፈልጓል።

ስለዚህ በአለም ዙሪያ የሚገኙ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን በአሩ ውስጥ ህንፃ ለመገንባት የሚያስችለውን ሀብት በማዘጋጀት በፈረንሳይ ፖሊኔዥያ ዋና ከተማ ውስጥ እንደ አጥቢያ ቤተክርስትያን እና ሴሚናሮች ፣ የካምፕ ስብሰባዎች እና የጤና ስራዎች የሚሠራበትን ሕንጻ ለመገንባት እንድትረዱን በአክብሮት እንጠይቃለን።

በ1ኛ ዜና 22፡19 ላይ ያለው የሚያንጽ ቃል ዛሬም እንዲህ ሲል ያስተጋባልናል፣ “ተነሥታችሁ የአምላክን የእግዚአብሔርን መቅደስ ሥሩ። እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ እና ስራውን በአለም ሁሉ ላይ ያስፋ።

ወንድሞቻችሁ እና እህቶቻችሁ ከፈረንሳይ ፖሊኔዥያ

ሰንበት፣ ሰኔ 28፣ 2017 **1ኛ ትምህርት**

## የሱስ፣ ስምዖን እና ማርያም

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “ስለዚህ እልሃለሁ፥ እጅግ ወዳለችና ብዙ ያለው ኃጢአትዋ ተሰርዮላታል፤ ጥቂት ግን የሚሰረይለት ጥቂት ይወዳል።” (ሉቃስ 7፡47)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ**፡ Testimonies for the Church, vol. 4, pp. 485–487, 550–552.

*“የሱስ የእያንዳንዱን ነፍስ ሁኔታ ያውቃል። እኔ በጣም ኃጢአተኛ ነኝ ትል ይሆናል። ትሆንም ይሆናል። ነገር ግን ኃጢአተኛ እንደሆንህ መጠን የሱስ በጣም ያስፈልግሃል። በኃጢአቱ ተጸጽቶ እያለቀሰ ወደ እርሱ የሚመጣውን ሁሉ የሱስ ይቀበላል። የተደበቁ ኃጢአቶችን ሁሉ ቢያጋልጥም ለሌሎች ሳያሳውቅ ማንኛውንም ድንጉጥ ነፍስ ያበረታታል። ይቅርታ ለማግኘትና ለመለወጥ ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ ይቅር ይላል።”*—The Desire of Ages, p. 568.

## 1. ወደ ቢታንያ የተደረገ የመጨረሻ ጉብኝት **እሁድ፣ ሰኔ 22**

### ሀ. ክርስቶስ ቢታንያን በጐበኘበት ወቅት በየሩሳሌም የነበረውን ሁኔታና ይህ ሁኔታ በስምዖን ግብዣ ላይ በነበሩ አንዳንድ ሰዎች ላይ ምን ተጽዕኖ እንዳሳደረ ግለጽ። ዮሐንስ 11:55–57፤ መዝሙረ ዳዊት 55:21

*“የቢታንያው ስምዖን የየሱስ ደቀ መዝሙር እንደሆነ ተደርጐ ይገመት ነበር። ይህ ሰው የክርስቶስን ተከታዮች በይፋ ከተቀላቀሉት ጥቂት ፈሪሳ ውያን አንዱ ነበር። ስምዖን የሱስን እንደ አስተማሪ ተቀብሎ መሲሕ ይሆን ይሆናል የሚል ተስፋ ቢኖረውም እንደ አዳኝ አልተቀበለውም ነበር። ባሕርዩና የሕይወት መርሖው አልተለወጡም ነበር።”*—Ibid., p. 557.

### ለ. ስምዖን ምን ታላቅ በረከት አግኝቷል? ከዚያም ለየሱስ ምስጋና ያቀረበው እንዴት ነው? ሉቃስ 7፡36

*“ስምዖንን ወደ የሱስ እንዲቀርብ ያደረገው ከሥጋ ደዌ መፈወሱ ነው። ክርስቶስ ለመጨረሻ ጊዜ ቢታንያን ሲጐበኝ ስምዖን ለተደረገለት ችሮታ ውለታ ለመክፈል ሲል ለየሱስና ለደቀ መዛሙርቱ ግብዣ አዘጋጀ።”*—Ibid.

## ሀ. ብዙውን ጊዜ በማህበራዊ ስብሰባዎች ውስጥ በድብቅ፣ ከመጋረጃ በስተጀርባ የሚሆነው አይነት ሁኔታ፣ በዚህ ግብዣ ላይም እንዴት እንደነበረ ግለጽ። መዝሙረ ዳዊት 55:21

*"በዚህ ግብዣ ላይ ብዙ አይሁዳውያን ተገኝተው ነበር። ክርስቶስና ሥራው ከምንጊዜውም የበለጠ የሕዝብን ስሜት ስለሳቡ በኢየሩሳሌም ውስጥ ብዙ ግርግር ተከሰተ። በድግሱ ላይ ከነበሩት ሰዎች መካከል ብዙዎቹ የየሱስን እንቅስቃሴ በጥሞና ሲከታተሉ አንዳንዶቹ በጥላቻ ዓይን ይመለከቱት ነበር።"*— The Desire of Ages, p. 557.

## ለ. በስምዖን ግብዣ ላይ ማርያም ያደረገችውን ድርጊት ተናገር። ሉቃስ 7:37፣ 38፤ ዮሐንስ 12፡3

*"ማርያም ግን ከየሱስ አንደበት የሚወጣውን ቃል በንቃት ታዳምጥ ነበር። የሱስ በመሐሪነቱ ኃጢአትዋን ይቅር ስላለላትና ወንድምዋን ከሞት ስላስነሳላት ማርያም በጣም ደስ ብሎአት ነበር። የሱስ በቅርብ ጊዜ እንደሚሞት ሲናገርስምታ ስለነበር ስለዚህ ነገር የተሰማትን ሐዘንና ለየሱስ የነበራትን ከፍተኛ ፍቅር ለመግለጽ ፈለገች። ስለዚህ የሱስን ለመቀባት «እጅግ ውድ የሆነ ሽቶ የሞላበት የአልባስጥሮስ ብልቃጥ» ብዙ ገንዘብ ወጭ አድርጋ ገዛች። በዚያን ጊዜ ብዙ ሰዎች የሱስ ሊነግሥ ነው ብለው ያስወሩ ስለነበር የማርያም ሐዘን ወደ ደስታ ተለወጠና ለጌታዋ ክብር ለማሳየት የመጀመሪያዋ መሆን ፈለገች። የሽቶውን ቢልቃጥ ሰብራ በሽቶው የየሱስን ራስና እግሮች ከቀባች በኋላ ተንበርክካ እያለቀሰች እግሮቹን በእንባዋ አርሳ በተንዠረገገው ረጅም ጸጉርዋ አበሰችው።*—Ibid., pp. 558, 559.

## ሐ. ይሁዳ ይህን ድርጊት የተቀበለው በምን መልኩ ነበር? ዮሐንስ 12:4፣ 5 ማቴዎስ 26:8፣ 9

*"[ማርያም] ድርጊትዋን ማንም እንዲያውቅባት አልፈለገችም ነበር። ነገርግን የሽቶው መዓዛ ክፍሉን ስላወደው በዚያ የነበሩት ሁሉ ምን እንዳደረገች አወቁባት። ይህ ድርጊት ይሁዳን በጣም ስላናደደው ቀይቶ የሱስ የሚለውን ከመስማት ፈንታ የደረሰውን የገንዘብ ኪሳራ ለምን በቸልተኝነት ተመለ ከተው በማለት የሱስን እያማ በአጠገቡ ከነበሩት ሰዎች ጋር ማንሾካሾክጀመረ። በመሰሪ አነጋገሩ ሰዎች ቅሬታ እንዲያድርባቸው ለማድረግ ሞከረ።"* —Ibid., p. 559.

## ሀ. እንደ እውነቱ ከሆነ ይሁዳ ማርያም የየሱስን እግር ሽቶ የቀባችበትን ድርጊት ለምን ተቸ? ዮሐንስ 12፡6

*"ይሁዳ የሐዋርያት ገንዘብ ያዥ ስለነበረ ከነበራቸው ጥቂት ገንዘብ እየሰረቀ ለግል ጥቅሙ በማዋል የገንዘባቸውን መጠን አመናመነው። ይሁዳ ሊገኝ የሚቻለውን ገንዘብ ሁሉ እየሰበሰበ በከረጢት ውስጥ የማስቀመጥ ጉጉት ነበረው። በከረጢቱ ውስጥ የሚጠራቀመው ገንዘብ ብዙውን ጊዜ የሚያገለግለው ለድኾች በጐ አድራጐት ነበር። እርሱ አስፈላጊነቱን ያላመነበት እቃ በተገዛ ቁጥር ይህ ኪሳራ ለምን አስፈለገ? ይህ እቃ የተገዛበት ገንዘብ ለድኾች አገልግሎት እንዲውል ለምን በከረጢቱ ውስጥ እንዲቀይ አይደረግም? ይል ነበር። የማርያም የልግስና ድርጊት ከእርሱ የራስ ወዳድነት ባሕርይ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ሐፍረት ስለተሰማው እንደልማዱ ተቃውሞው ለክቡር ዓላማ የተሰነዘረ ለማስመሰል ሲል ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘወር ብሎ «ይህ ሽቶ በሶስት መቶ ብር ተሸጦ ገንዘቡ ለድኾች ለምን አልተሰጠም?» አለ። «እርሱ ይህን የተናገረው ለድኾች አዝኖ ሳይሆን ሌባ ስለነበረ ነው። የገንዘብ ከረጢት የሚይዝ እርሱ በመሆኑ በከረጢቱ የሚከተተውን ገንዘብ መውሰድ ለምዶ ነበር።» ይሁዳ ለድኾች የሚራራ ልብ አልነበረውም። የማርያም ሽቶ ተሸጦ ገንዘቡ በይሁዳ እጅ ቢገባ ኖሮ ድኾች የሚያገኙት ጥቅም አይኖርም ነበር።*—The Desire of Ages, p. 559.

## ለ. ደቀ መዛሙርቱ ይሁዳን የተመለከቱት እንዴት ነበር? እሱስ ራሱን እንዴት ይመለከተው ነበር? ዮሐንስ 13፡29

*"ይሁዳ ስለ ራሱ የማስተዳደር ችሎታ ከፍተኛ ግምት ነበረው። የሒሳብ ሥራ እውቀት ስለነበረው ራሱን ከጓደኞቹ አብልጦ ይገምት ነበር፣ ጓደኞቹንም የእርሱን የበላይነት አምነው እንዲቀበሉ አደረጋቸው። እነርሱ በእርሱ ላይ አመኔታ እንዲኖራቸው ስላደረገ በእነርሱ ዘንድ ከፍተኛ ተሰሚነት ነበረው።* —Ibid., pp. 559, 560.

## ሐ. ዘውትር ስለሌሎች ሰዎች የሚያጉረመርሙትን ብዙውን ጊዜ የሚገፋፋቸው ምን እንደሆነ ግለጽ—እና ይህም ስሜታቸው ስስ የሆኑ ነፍሳትን እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል ግለጽ። ይሁዳ 1፡16

*"ማርያም ትችቱን ስለሰማች ደነገጠች። ባደረሰችው የገንዘብ ኪሳራ ምክንያት እህቷ ትቆጣኛለች ብላም ፈራች። ጌታ የሱስ ራሱ እንደ ብኩን ሰው ይገምተኝ ይሆን ብላ አሰበች። ያለ አንዳች ክርክር ሹልክ ብላ ልትሔድ ነበር።*—Ibid., p. 560.

## ሀ. ሲሞን የራሱ የፈሪሳዊነት ኩራቱ ላይ የማርያም ድርጊት ምን ተጽዕኖ አሳደረበት? የሱስንስ ምን ብሎ ፈረደበት? ሉቃስ 7፡39

*"የግብዣው ባለቤት የነበረው ስምዖን ስለ ማርያም ስጦታ ይሁዳ የሰነዘረው ትችት ተባባሪ ስለነበር ስጦታውን በተመለከተ የሱስ የወሰደው አቋም አስገረመው» ከተጋባዥዎቹ መካከል ብዙዎቹ ክርስቶስን በጥርጣሬና በቅሬታ መንፈስ ይመለከቱት እንደነበር ስላወቀ ፈሪሳዊ ኩራቱ ተነካበት።* . . .

*"ክርስቶስ ስምዖንን ከሥጋ ደዌ በመፈወስ የቁም ሙት ከመሆን አዳነው። አሁን ግን ስምዖን የአዳኛችንን ነቢይነት ተጠራጠረ። ክርስቶስ ማርያም እንድትቀርበው በመፍቀዱ፣ ኃጢአትዋ እጅግ የከፋ ስለሆነ ይቅርታ ሊደረግላት የማይቻል ነው በማለት ዘልፎ ስላላባረራትና የረከሰች ሴት መሆንዋን እንደተገነዘበ ባለመግለጹ ስምዖን የየሱስን ነቢይነት እንዲ ጠራጠር አደረገው።"*—The Desire of Ages, p. 566.

## ለ. የሱስ በስምዖንና በማርያም ሕይወት መካከል ስለነበረው ነገር ምን ያህል እንደሚያውቅ እንዴት ገለጸ? ሉቃስ 7፡40-43 የሱስ ስምዖንን የገሠጸው እንዴት ነው? ለምንስ? ሉቃስ 7፡44-46

*"[ስምዖን]እንደዚህ ያስብ የነበረው ስለ እግዚአብሔርና ስለ ክርስቶስ ባለማወቁ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ እንደ አባቱ ቸር፣ ርህሩህና መሐሪ መሆኑን አልተረዳም። እንደ ስምዖን አስተሳሰብ ከሆነ የማርያም ንስሐ መግባት መታሰብ አልነበረበትም።*

*"ነቢዩ ናታን የዳዊትን ኃጢአት በምሳሌ እንዳስረዳው ሁሉ እንዲሁም ክርስቶስ ስምዖን እንዲረዳው የፈለገውን መልእክት በምሳሌ ነገረው። የሱስ በራስ ላይ የመፍረድን ኃላፊነት በአስተናጋጁ ላይ ጣለበት። ስምዖን አሁን በንቀት ዓይን የሚያያትን ሴት ኃጢአት እንድትሠራ አድርጓት ነበር። ... ስምዖን ከማርያም የተሻልሁ ጻድቅ ነኝ ይል ስለነበር የሱስ የእርሱ ኃጢአት ምን ያህል ትልቅ እንደነበር ሊያሳየው ፈለገ። አምስት መቶ ብር ከሃምሳ የሚበልጠውን ያህል የስምዖን ኃጢአት ከማርያም ኃጢአት እንደሚበልጥ ሊያስረዳው አሰበ።"*—Ibid., pp. 566, 567.

## ሐ. የሱስ የማርያም ኃጢአቷ ተሰርዮላታል ብሎ ሲናገር አይሁዳውያን ምን ምላሽ ሰጡ? ሉቃስ 7:48፣ 49 የክርስቶስ ምሳሌ በስምዖን ልብ ላይ ምን ተጽዕኖ አሳድሯል?

*"ስምዖን ራሱን ከድሮው በተለየ አኳኋን ማየት ጀመረ። ከነቢይ በላይየሆነው ጌታ ማርያምን እንዴት እንደተቀበላት ተመለከተ። ክርስቶስ በነቢይዓይን በፍቅርና በቅድስና የተሞላውን ልብዋን እንደተመለከተ ተረዳ። ከእርሱ በላይ በሆነ ጌታ ፊት እንዳለ በተገነዘበ ጊዜ ሐፍረት ተሰማው።"*—Ibid., p. 567.

## 5. የሲሞን መለወጥ | ሐሙስ፣ ሰኔ 26

### ሀ. በውጤቱ እርግጠኛ ባንሆንም እንኳ እንደ ስምዖን ካሉ ኃጢአተኞች ጋር በቅንነት እንድንነጋገር ለምን እንበረታታለን? ምሳሌ 9:8፤ ያእቆብ 5:20

*"ማርያም ኃጢአትዋ ይቅር የተባለላት ኃጢአተኛ ስትሆን እርሱ ግን ኃጢአቱ ይቅርያልተባለለት ኃጢአተኛ ነበር። በማርያም ላይ ተግባራዊ እንዲሆን የፈለገው ጥብቅ የፍትህ ሕግ እርሱን ወንጀለኛ አደረገው።*

*"የሱስ በእንግዶቹ ፊት በይፋ ስላልዘለፈው ስምዖን በየሱስ ደግነት ልቡ ተነካ። በማርያም ላይ እንዲደርስባት የፈለገው ነገር በእርሱ ላይአልደረሰበትም። ክርስቶስ ትክክለኛውን ነገር እንዲረዳ በማድረግና በርህራሄና በፍቅር ልቡን ለመሳብ እንደሚሻ እንጂ ኃጢአቱን በሌሎች ፊት ለማጋለጥ ፍላጐት እንደሌለው ተረዳ። ከባድ ዘለፋ ስምዖን ኃጢአቱን እንዲናዘዝ አያደርገውም ነበር፣ ነገር ግን ትእግሥት በተሞላበት መንፈስ የተሰጠው ምክር ስሕተቱን እንዲያምን አደረገው። ለጌታ የሚከፍለው ዕዳ ምን ያህል ብዙ እንደሆነ አወቀ። ትዕቢቱ ወደ ትሕትና ተለውጦ ንስሐ ስለገባ እብሪተኛው ፈሪሳዊ አንገቱን የደፋና ሕይወቱን ለመሰዋት የተዘጋጀ ደቀ መዝሙር ሆነ።"*—The Desire of Ages, pp. 567, 568.

### ለ. የሱስ ማርያም ስላደረገችው ድርጊት ምን ብሏል? ምን አበረታች ቃላት ነግሯታል? ማቴዎስ 26:12፣ 13፤ ሉቃስ 7፡50

*"ሰው ሁሉ ማርያምን ከሁሉ የባሰች ኃጢአተኛ አድርጐ ይገምታት ነበር። ክርስቶስ ግን ሕይወትዋን በዚያ አኳኋን እንድትመራ የተደረገችበትን ሁኔታ ያውቅ ነበር። የሱስ ያች ኃጢአተኛ ሴት የነበራት ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል እንድትጠፋ ማድረግ ሲችል፣ ፈጽሞ አላደረገውም። ተስፋ ከመቁረጥና ከጥፋት ያዳናት እርሱ ነው። ልብዋንና ሕሊናዋን በቁጥጥሩ ሥር ያደረገውን አጋንንት የሱስ ሰባት ጊዜ ሲገስጸው ሰምታለች። የሱስ ለእርስዋ ሲል ወደ አባቱ በከፍተኛ ድምጽ እንደጮኸ ሰምታለች። ምንም ዓይነት እንከን ለሌለው ለየሱስ ንጽሕና ኃጢአት ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ ስለ ተገነዘበች በእርሱ ብርታት አሸነፈች።"*—Ibid., p. 568.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች | አርብ፣ ሰኔ 27

**1. ከአምላክ ጋር በማደርገው ጉዞ የማርያምን ዓይነት ጥሩ ባሕርያትን ማዳበር የምችለው እንዴት ነው?**

**2. በግብዣው ላይ የይሁዳን ዓይነት አመለካከት ስመለከት ምን ማስጠንቀቂያ ማስተዋል አለብኝ?**

**3. የስምዖን ሐሳብ ከገባበት ዓይነት ወጥመድ መራቅ የምችለው እንዴት ነው?**

**4. ክርስቶስ ለማርያም የተናገራቸው የማጽናኛ ቃላት በሕይወቴ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት መቼ ነው?**

**5. የሱስ ስምዖንን ስሕተቱን እንዲያምን እንዴት እንዳደረገው መማር ያለብኝ ለምንድነው?**

# የድል አድራጊ አገባብ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “ለጽዮን ልጅ። እነሆ፥ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉአት ተብሎ በነቢይ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ።” (ማቴ 21፡5)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** The Desire of Ages, pp. 569–579.

“ክርስቶስ የሩሳሌምን ከልጆቿ ጋር ሊያድን መጣ፤ ነገር ግን የፈሪሳዊያኑ ኩራት (ትዕቢት)፣ ግብዝነት፣ ቅናት እና ክፋት ዓላማውን ከዳር ከማድረስ ከለከሉት።”—The Desire of Ages, p. 577.

## 1. በደብረ ዘይት ተራራ ላይ — እሁድ፣ ሰኔ 29

### ሀ. የሱስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሩሳሌም ሲቃረቡ ሁለቱን አስቀድሞ የላካቸው ከምን ዓይነት ትዕዛዝ ጋር ነው? ማቴዎስ 21:1-5

“ወደ ኢየሩሳሌም ለመሔድ በማሰብ የሱስ አንዲት አህያ ከነግልገልዋ እንዲያመጡለት ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ላከ። አዳኛ ችን በተወለደ ጊዜ ያስተናገዱት እንግዶች ነበሩ። የተኛበት የከብቶች መመ ገቢያ ግርግም በውሰት የተገኘ ነበር። አሁን ደግሞ ምንም እንኳን በሺ በሚቆ ጠሩ ተራራዎች ላይ የሚሰማሩት የእንስሳ መንጋዎች የእርሱ ቢሆኑም (መዝ.50:10) እንደ ንጉሥ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ለመግባት የሚቀመጥበትን እንስሳ ለማግኘት የማያውቀው ሰው እርዳታ አስፈለገው።—The Desire of Ages, pp. 569, 570.

### ለ. የደቀ መዛሙርቱን ተግባር ግለጽ። ማቴዎስ 21:6፣ 7

“ደቀ መዛሙርቱም በደስታ ስሜት ልብሳቸውን እንደ ድብዳብ ሠርተው ጌታቸውን አስቀመጡት። እስከዚያ ጊዜ ድረስ የሱስ ሁልጊዜ በእግሩ ይሔድ ስለነበር አሁን በእንስሳ ላይ ተቀምጦ ለመሔድ መፈለጉ መጀመሪያ ደቀ መዛሙርቱን አስገርሞአቸው ነበር። ነገር ግን የሱስ ንጉሥነቱን አውጆ በንጉሣዊነት ክብርና ኃይል ወደ ርዕሠ ከተማዋ ሊገባ ነው በሚል የደስታ ተስፋ ልባቸው ፈካ።”—Ibid., p. 570.

## ሀ. ሕዝቡ የሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚመጣ ሲሰሙ ምን አደረጉ? ዮሐንስ 12:12፣ 13

“[ደቀ መዛሙርቱ] እንስሶቹን ለማምጣት ተልከው በሔዱ ጊዜ የጋለ ምኞታቸውን ለየሱስ ወዳጆች ስለተናገሩ ወሬው በሰፊው ተናኘ፣ የሕዝቡም ምኞት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ።”—The Desire of Ages, p. 570.

## ለ. ሕዝቡ በዚያ አስደሳች አጋጣሚ ላይ የሱስን መሲሕ አድርገ እንዲያከብሩት ያደረገው ምንድን ነው? ዘካርያስ 9:9፤ ዮሐንስ 12:14፣ 15

“ወደ ከተማዋ የንጉሥን አገባብ በተመለከተ የሱስ የተከተለው የአይሁ ዶችን ባሕል ነው። እርሱ ተቀምጦ የሔደባት እንስሳ የእሥራኤል ነገሥታት ይቀመጡባት የነበረችው ዓይነት ስትሆን እንዲሁም መሲሑ ወደ መንግሥቱ የሚመጣው በዚሁ አኳኋን መሆኑ አስቀድሞ በትንቢት ተነግሮ ነበር። የሱስ በአህያው ውርንጫ ላይ እንደተቀመጠ የድል አድራጊነት ዜማ አየሩን አጥለቀለቀው። ሕዝቡም መሲሕና ንጉሣችን ነው ብለው በጭብጨባ ተቀበሉት። የሱስ ከዚያ በፊት ለመቀበል ፈቃደኛ ያልነበረውን የአክብሮት መግለጫ ስለተቀበለ ይህን ሁኔታ ደቀ መዛሙርቱ የሱስ በምድራዊ ዙፋን ላይ ይቀመጣል የሚለው ተስፋቸው የመፈጸሙ ምልክት እንደሆነ አድርገው ተረጎሙት።”—Ibid

## ሐ. ለመዳን የጓጉ ሰዎች የመዝሙረኛውን ቃላት በደስታ ያስተጋቡት እንዴት ነው? ማቴዎስ 21:9፤ መዝሙረ ዳዊት 118:26

“ሕዝቡም ነጻነታቸውን የሚያገኙበት ጊዜ እንደደረሰ አመኑ። ሮማውያን ወታደሮች ከኢየሩሳሌም ሲወጡና እሥራኤል ነጻ አገር ስትሆን በዓይነ ሕሊናቸው ታያቸው። ሁሉም ተደስተውና ስሜታቸው ተነሳስቶ ስለነበር ለእርሱ አክብሮታቸውን ለመግለጽ ተወዳደሩ። ድምቀት ያለውና የተዋበ ውጫዊ ሥነ ሥርዓት ሊያካሒዱለት ባይችሉም ከተደሰተ ልብ የመነጨ ስግደት አቀረቡለት። በውድ ዋጋ የተገዛ ገጸ-በረከት ሊያቀርቡለት ባይችሉም ልብሳቸውንና የወይራና የዘንባባ ዝንጣፊዎች በመንገዱ ላይአነጠፉለት። የድል አድራጊነት ጉዞውን በንጉሣዊ ደረጃ ለመምራት ባይችሉም ከሥነ ፍጥረት የድል አድራጊነት ምልክት ከሆነው ከዘንባባ የተቀጠፉ ዝንጣፊዎችን ከፍ አድርገው እያውለበለቡ ሆሳዕና እያሉ አዜሙለት።”—Ibid.

## ሀ. አንዳንድ ፈሪሳውያን፣ ሕዝቡ ክርስቶስን ሲያወድሱ ሲሰሙ ምን ምላሽ ሰጡ? ዮሐንስ 12:19፤ ሉቃስ 19፡39

"በቅንአትና በተንኮል ስሜት የበገኑት ፈሪሳውያን ትዕይንቱን በተመለከቱ ጊዜ የጋለውን ሕዝባዊ ስሜት ለመለወጥ አሰቡ። ያላቸውን ሥልጣን ሁሉ በመጠቀም ሕዝቡን ጸጥ ለማሰኘት ሞከሩ፣ ነገር ግን ተማጽኖአቸውና ዛቻቸው የሕዝቡን የድጋፍ ስሜት አባባሰው። ያ በከፍተኛ ቁጥር የወጣ የሕዝብ ሠራዊት የሱስን ያነግሠዋል የሚል ስጋት አደረባቸው። የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ በሕዝቡ መካከል ተሹለክልከው በማለፍ ወደ የሱስ ቀረቡና በተግሳጽና በዛቻ መንፈስ «ደቀ መዛሙርትህን ዝም አሰኛቸው» ሲሉ አነጋገሩት። እንደዚህ ያለ ጩኸት የበዛበት ትዕይንት ሕገ-ወጥ እንደሆነና በሹማምንቱም እንደማይፈቀድ ገለጹ።"— The Desire of Ages, p. 572.

## ለ. የሱስ ምን መልስ ሰጣቸው? ሉቃስ 19፡40

"ያ የድል አድራጊነት ትዕይንት እግዚአብሔርያቀደው ነበር። በነቢዩ አስቀድሞ የተነገረ ስለነበር ሰው የእግዚአብሔርን ዕቅድ የመለወጥ ኃይል አልነበረውም። ሰዎች የእግዚአብሔርን ዕቅድ ተግባራዊ ማድረግ ቢሳናቸው ኖሮ ግዑዝ ድንጋዮች እንዲናገሩ በማድረግ ልጁን በምስጋና ድምጽ እንዲቀበሉት ያደርግ ነበር።"—Ibid., p. 572.

"እንዲሁም ካህናቱና ገዥዎቹ ምድር የፀሐይን ብርሃን እንዳታገኝ ለመሸፈን እንደመሞከር ያለውን፣ ዓለም የከበረውን የጽድቅ ፀሐይ ጨረሮች እንዳታገኝ ለማድረግ፣ ለመሸፈን ሞክረው ነበር። ምንም ተቃውሞ ቢያጋጥመውም የክርስቶስ መንግሥት በሕዝብ ዘንድ መመስከሩ አልቀረም።"—God's Amazing Grace, p. 47.

"ሰው ሥራውን ለማደናቀፍ ወይም ለማፍረስ የሚችለውን ሁሉ ቢያደርግም የአምላክ ሥራ ግን ለዘላለም ወደፊት መጓዙን ይቀጥላል።"—The Story of Jesus, p. 85.

## ሐ. ይህ አስደናቂ ሁኔታ የትንቢት ፍጻሜ መሆኑን ሕዝቡ ያወቀው እንዴት ነው? ዘካርያስ 9፡9

"ዝም የተሰኙ ፈሪሳውያን ወደ ኋላ ሲመለሱ የዘካርያስ ቃላት በመቶዎች የሚቆጠሩ ድምፆች ከፍ ብለው ተስተጋብተው ነበር። Ibid., p. 572–575.

## ሀ. የሱስ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም በገባበት ቀን እንዲህ ያለ ታላቅ ሰልፍ (ትዕይንት) እንዲደረግ የፈቀደው ለምን ዓላማ ነበር? ዮሐንስ 12:16፣ 23–28

"የሱስ ከዚያ በፊት በምድራዊ ሕይወቱ እንደዚህ ያለ ትዕይንት እንዲደረግ የፈቀደበት ጊዜ አልነበረም። ይህ ዓይነት ድርጊት ውጤቱ ምን እንደሚሆን አስቀድሞ ታይቶታል። ወደ ስቅለት እንደሚያደርሰውም ያውቃል። አሁን ግን አዳኝ መሆኑን እንደዚህ በይፋ ለማሳወቅ አቀደ። የጠፋውን ዓለም ለማዳን የታቀደው የተልዕኮው መደምደሚያ የሆነው መስዋዕት ትኩረት እንዲያገኝ ፈለገ። ሕዝቡ ለፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ሳለ ለመስዋዕት በሚቀርበው በግ የሚመሰለው የሱስ በገዛ ፈቃዱ ራሱን ለቁርባን አቀረበ። የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በሚቀጥሉት ዘመናት ዓለምን ለማዳን የሱስ መሞቱን በጥሞና ልታጤነውና ልትመረመረው የሚገባት ርዕስ ነው። ከዚህ ርዕስ ጋር ግንኙነት ያለው መረጃ ሁሉ በማያጠራጥር አኳኋን መረጋገጥ አለበት። በዚያን ጊዜ የሰው ሁሉ ዓይን በእርሱ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ አስፈላጊ ነበር፤ ከታላቁ መስዋዕት አስቀድሞ የተፈጸሙት ድርጊቶች ሁሉ ሰዎች በመስዋዕቱ ላይእንዲያተኩሩ የሚያደርጉ መሆን ነበረባቸው። ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ከተከሰተው ሰልፍ በኋላ ሰው ሁሉ የሱስ ወደ መጨረሻው ትዕይንት ባደረገው ግስጋሴ ላይ አተኮረ።

ከዚህ የድል አድራጊነት ጉዞ ጋር የተፈጸሙት ድርጊቶች ሁሉ የመወያያ አርዕስት ስለሆኑ የሱስን በእያንዳንዱ ሰው አእምሮ ውስጥ እንዲቀረጽ አደረጉት። ብዙ ሰዎች ከስቅለቱ በኋላ እነዚህን ድርጊቶች ከአሟሟቱና ከደረሱበት ፈተናዎች ጋር በማያያዝ ስላስታወሱ ትንቢቶችን እንዲመረምሩና የሱስ መሲሕ መሆኑንም እንዲያምኑ አደረጋቸው፣ በዚህም ምክንያት በየአገሩ እምነቱን የሚቀበሉት ሰዎች ቁጥር ሊበዛ ቻለ።"—The Desire of Ages, p. 571.

## ለ. በሚገርም ሁኔታ ግን የሱስ ከተማዋን ሙሉ ገጽታ ሲመለከት ምን አደረገ—ለምንስ? ሉቃስ 19፡41-44

"ሰው ሁሉ ተሰብስቦ በሚሰግድለት የደስታ ትዕይንት መካከል የእሥራኤል ንጉሥ አለቀሰ። ይህ ለቅሶ ከደስታ ስሜት ገንፍሎ የወጣ ሳይሆን ለመቋቋም ከሚያዳግት ስቃይ የመነጨ ከማቃሰት ስሜት ጋር የተያያዘ እንባ ነበር። ከዚያ የነበረው ሕዝብ ሁሉ በድንገተኛ ሐዘን ተዋጠ። የአድናቆት ጩኸታቸው ሁሉ ተቋረጠ። ብዙዎች ምክንያቱን የማያውቁት የሐዘን ስሜት አድሮባቸው ከየሱስ ጋር አብረው አለቀሱ።

"የሱስ እንባውን ያፈሰሰው የሚደርስበትን ስቃይ በማሰብ አልነበረም። .... የየሱስን ልብ እንደ ጦር የወጋው ፍቅሩን ችላ በማለት የእግዚአብሔርን ልጅ የናቀችውን፣ የእርሱን ማንነት ለመቀበል የሠራቸው ተአምራት ሊያሳምንዋት ያልቻለችውንና ሕይወቱን ለማጥፋት የተዘጋጀችውን ኢየሩሳሌምን ማየቱ ነው።"—Ibid., p. 576.

## 5. ወደ የሩሳሌም መግባት | ሐሙስ፣ ሐምሌ 03

### ሀ. የሱስ ወደ የሩሳሌም ሲገባ ገዥዎቹ በግርግሩ መካከል ምን ጥያቄ ጠየቁ እና ምን መልስ አገኙ? ማቴዎስ 21:10፣ 11

"ስልፈኛው ሕዝብ ከደብረ ዘይት ተራራ ለመውረድ እንቅስቃሴ እንደ ጀመረ ወዲያውኑ ሹማምንቱ ደረሱ። ከሕዝቡ ላይ የሚታየው የጋለ የደስታ ስሜት ምክንያቱ ምን እንደሆነ ለማወቅ ፈለጉ። «ይህ ማን ነው?» ብለው በጠየቁ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ለጥያቄው መልስ ሰጡ። በአንደበተ ርቱዕነት ስለ ክርስቶስ በትንቢት የተነገረውን እንደሚከተለው ዘርዝረው አስረዱ።—The Desire of Ages, p. 578.

### ለ. የሱስ ወደ ከተማዋ እንደደረሰ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ምን አደረገ? ማቴዎስ 21:12-16፤ መዝሙረ ዳዊት 8፡2

"ከሶስት ዓመታት በፊት የቤተ መቅደሱ አለቆች በየሱስ ትእዛዝ ምክን ያት ስለሸሹ ውርደት ደርሶባቸው ነበር። ከዚያ ጊዜ አንስቶ ፍርሃታቸውና የዚያን ተራ ሰው ትእዛዝ ያላንዳች ተቃውሞ መቀበላቸው ይገርማቸው ነበር። ስለዚህ ይህ ክብረ-ነክ ድርጊት ሊደገም አይችልም የሚል ስሜት አደረባቸው። ይሁን እንጂ ካለፈው ጊዜ የበለጠ አሁን ደነገጡ፥ ትእዛዙንም ለመፈጸም ተቻኮሉ። ትእዛዙን ላለመቀበል የደፈረ አልነበረም። ካህናቱና ነጋዴዎቹ ከብቶቻቸውን እየነዱ ከየሱስ ፊት ሸሽተው ሔዱ። ...

ሰፍር ቁጥር የሌለው ሕዝብ ከቤተ መቅደሱ ሲሸሽ ብዙ ሰዎች ከዚያው ቀርተው ነበር። በኋላ የመጡት ሰዎች ከነዚህ ጋርስለተቀላቀሉ የቤተ መቅደሱ አደባባይ በሕሙማን ተጥለቀለቀ፥ የሱስም ለእነርሱ አገልግሎት መስጠቱን ቀጠለ።"—Ibid., pp. 591, 592.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች | አርብ፣ ሐምሌ 04

1. የፈሪሳውያን አመለካከት በዛሬው ጊዜ የሚደገመው እንዴት ነው?
2. ክርስቶስን ቃል የተገባለት ንጉሥ አድርገው ያከበሩት ሰዎች ተለይተው የሚታወቁት በምንድን ነው?
3. የሱስን ለኢየሩሳሌም እንዳደረገው ለእኔም እንዲያለቅስልኝ የሚያደርገው ምን ሊሆን ይችላል?
4. በዘካርያስ 9:9 ላይ የነበረው ትንቢት በዚህ ወቅት ፍጻሜውን ያገኘው እንዴት ነው?
5. ክርስቶስ በዚህ ጊዜ ይህን ያህል የሕዝብ አድናቆት እንዲሰጠው የፈቀደው ለምንድን ነው?

ሰንበት፣ ሐምሌ 12፣ 2017

3ኛ ትምህርት

# የሱስን ማየት እንፈልጋለን

**የመታሰቢያ ጥቅስ፦ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች።" (ዮሐንስ 12:24)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** Christ's Object Lessons, pp. 80–89

*"የሰይጣን መንግሥት ሊገለበጥ የሚችለው በክርስቶስ ሞት ብቻ ነው፤ ሰውም የሚቤዠው፣ አምላክም የሚከብረው በዚህ መንገድ ብቻ ነውና።"*—The Desire of Ages, p. 624.

## 1. ከምስራቅ እና ከምዕራብ — እሁድ፣ ሐምሌ 06

### ሀ. የሱስን በልደቱ ማለትም በህይወቱ መጀመሪያ ላይ የፈለጉት እነማን ነበሩ እና ወደ እሱ ምን አመጡ? ማቴዎስ 2:1፣ 2፣ 10፣ 11

### ለ. አሁን፣ በአገልግሎቱ መጨረሻ ላይ የሱስን የፈለጉት እነማን ናቸው፣ እና ማንን ይወክላሉ? ዮሐንስ 12፡20 ይህስ ምን ያስተምረናል? ማቴዎስ 8፡11

*"በሕይወቱ መጀመሪያ ላይ ሰብአ ሰገል ከምስራቅ መጥተው እንዳዩት ሁሉ እንዲሁም እነዚህ [የተወሰኑ የግሪክ ሰዎች] በሕይወቱ መጨረሻ ላይ እርሱን ለማየት ከምዕራብ መጡ። ሰብአ ሰገል ለአዳኛችን ስጦታ ይዘው ከአረማውያን አገርተነስተው የሱስ ወደነበረበት የከብቶች በረት መጡ። እንደዚሁም እነዚህ ግሪኮች የዓለምን አገሮች ጉሳዎችና ሰዎች በመወከል የሱስን ለማየት መጡ። ስለዚህ የአገሮች ሁሉ እና የዘመናት ሁሉ ሕዝቦች ወደ አዳኛችን መስቀል ተስበዋል።* . . .

*"ግሪኮች የሱስ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱን ሰምተው ስለ ነበር አንዳንዶቹ ካህናቱንና ሹማምንቱን ከቤተ መቅደሱ አስወጥቶ የዳዊትን ዙፋን በመያዝ በእሥራኤል ላይ ሊነግሥ ነው የሚል ወሬ አሰራጩ። ስለዚህ እነዚህ ከግሪክ አገር የመጡ ሰዎች የየሱስን ትክክለኛ ተልዕኮ ለማወቅ ስለፈለጉ « የሱስን ማየት እንፈልጋለን፣» ብለው መጡ።"*—The Desire of Ages, pp. 621, 622.

## ሀ. ግሪኮች ፍላጎታቸውን እንዴት ገለጹ? ዮሐንስ 12፡21

## ለ. የሱስ ልመናውን የተረዳበትን ሂደትና ልቡ ለጥያቄው ምላሽ የሰጠው እንዴት እንደሆነ አብራራ። ዮሐንስ 12:22፣ 23

"«የሱስን ማየት እንፈልጋለን» የሚለውን የዓለምን የጉጉት ጩኸት በሰማ ጊዜ ፊቱ ፈካ አለና ክርስቶስ «እነሆ የሰው ልጅ የሚከበርበት ሰዓት ደርሶአል፣» ሲል ተናገረ። የግሪኮቹ ጥያቄ የሚከፍለው ትልቅ መስዋዕት ውጤት ናሙና መሆኑን ተገነዘበ።"—The Desire of Ages, p. 621.

"የሱስ ይህን በሰማ ጊዜ ከአይሁዶች በቀር ሌላ ሰው ከማይገባበት የቤተ መቅደስ ክልል ወጥቶ ወደ ውጩ አደባባይ በመሔድ ግሪኮቹን አነጋገራቸው።"—Ibid., p. 622.

## ሐ. ክርስቶስ እነዚያን እንግዶች ለመርዳት ያሳየው ርኅራኄ ሊያነሳሳን የሚገባው እንዴት ነው? ሉቃስ 14:23፤ መክብብ 11:1፣ 2

"የእውነትን እውቀት ለሚሰሙት ሁሉ ለማዳረስ የተቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን፤ የሚሰሙትም ብዙዎች ናቸውና። በትልልቅ ከተሞች እግዚአብሔርን እውነት ለመስማት የሚሹ ብዙ ቅን ነፍሳት አሉ። . . . መልእክቱን ደግማችሁ አውጁ፣ አሁንም መልእክቱን ድገሙ፣ የሚሉ ቃላት ተደጋግመው የተነገሩኝ ቃላት ነበሩ። ለሕዝቤ በመጀመሪያ በተሰበከባቸው ቦታዎች መልእክቱን እንዲደግሙ ንገራቸው፣ ... ።"—Evangelism, p. 394.

"ልዩና አስደናቂ ትርኢት ማሳየት እንዳለብን አልተነገረንም። እውነት በአውራ ጎዳናዎች እና መንገዶች መሰበክ አለበት፣ ስለዚህም ሥራ በማስተዋልና በምክንያታዊ ዘዴዎች መከናወን አለበት። ... ማሳየት አስፈላጊ ቢሆን እንኳ ክርስቶስ በምድራችን ሲመላለስ የሠራው ሥራ ለእኛ ምሳሌ ሊሆን ይገባል። ሥራችን ልክ እንደ ክርስቶስ ከቲያትርና ትኩረት ሳቢ ልዩ ከሆኑ ነገሮች ርቀን መሆን አለበት። ኃይማኖት ስሜት አይደለም፣ ይልቁንም ንጹህ፣ ቅዱስ፣ የሚለውጥ፣ የሚቀድስ ተጽዕኖ፣ መንፈሳዊ ሕይወት ከፍታን የሚያመጣና ለመዳን የሚሆን መሆን አለበት።"—Ibid., p. 396.

## ሀ. የሱስ በስንዴ እህል ፍሬ እና በተልእኮው መካከል ምን ንጽጽር አድርጓል? ዮሐንስ 12፡24

*“በመሬት ውስጥ የተቀበረው ዘር ፍሬ ያፈራል፣ ያ ፍሬ እንደገና ይዘራል። በዚህ አኳኋን በቀራንዮ መስቀል ላይ የተፈጸመው የክርስቶስ ሞት ለዘላለም ሕይወት የሚሆን ፍሬ ያፈራል። የዚህ ሞት ፍሬ የሆኑት ጻድቃን ስለዚህ መስዋዕት እያሰላሰሉ ለዘላለም ይኖራሉ።*

*“የማትሞት የስንዴ ዘር ፍሬ ለማፍራት ስለማትችል ብቻዋን ትቀራለች። ክርስቶስ ቢፈልግ ኖሮ ሕይወቱን ከሞት ለማዳን ይችል ነበር። ይህን ቢያደርግ ኖሮ ግን ብቻውን ይቀር ነበር። ይህም ማለት ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ማምጣት አይችልም ነበር ማለት ነው። የሱስ ለሰብአዊነት ሕይወትን ለማስተላለፍ የቻለው ሕይወቱን በመስጠት ብቻ ነው። ከየሕዝቡ፣ከየነገዱና ከየቋንቋው ተውጣጥተው ወደ እግዚአብሔርየተመለሱትን ቁጥር ስፍር የሌላቸውን የወንጌል ፍሬዎች የሚያፈራ ዘርለመሆን የቻለው ወደ መሬት ወድቆ በመሞቱ ብቻ ነው።”*—The Desire of Ages, p. 623.

## ለ. የሱስ ስለ ስንዴ ፍሬ በተናገረው ምሳሌ ላይ የተጠቀመው ሁለተኛ ነገር ምንድን ነው? ዮሐንስ 12:25፣ 26

*“የክርስቶስ የሥራ አጋር በመሆን ፍሬ ለማፍራት የሚፈልጉ ሁሉ መጀመሪያ ወደ መሬት ወድቀው መሞት አለባቸው። ሕይወታቸው በዓለም ፍላጎት ፈር ውስጥ ገብቶ መቀበር አለበት። ራስ ወዳድነትና የራስ ፍላጎት ስሜት መጥፋት አለበት። ራስን የመሰዋት ሕግ ራስን የማዳን ሕግ ነው። ገበሬ እህሉን በመሬት ላይ በመጣል እንደሚያባዛ ሁሉ በሰውም ሕይወት እንደዚሁ ነው። መስጠት መኖር ማለት ነው። እንድትኖር የምትፈልግ ሕይወት እግዚአብሔርንና ሰውን ለማገልገል ያለ ቁጠባ ትሰጣለች። ለክርስቶስ ሲሉ በዚህ ዓለም ሕይወታቸውን የሚሰው ሁሉ ሕይወታቸውን ለዘላለም ይጠብቃሉ።*

*“ለራስ አገልግሎት ብቻ የሚውል ሕይወት እንደተበላ እህል ይቆጠራልS ምክንያቱም ይጠፋል አድገትም የለውም። አንድ ሰው ሁሉን ነገር ለራሱ መሰብሰብ፣ ለራሱ መኖር፣ ማሰብና ማቀድም ይችላል። ነገር ግን ሕይወቱ ያልፋል፣ የሚያተርፈው ነገርም አይኖርም። ራስን ብቻ የማገልገል ሕግ ራስን የማጥፋት ሕግ ነው።*

“[ዮሐንስ 12:26 ጠቅሷል።] *የክርስቶስን የመስዋዕት መስቀል የተሸከሙ ሁሉ የክብሩ ተካፋይ ይሆናሉ። የሱስ በተዋረደበትና በተሰቃየበት ወቅት ልቡን ያስደሰተው ነገር ቢኖር ደቀ መዛሙርቱ የእርሱ ክብር ተካፋይ መሆናቸው ነው። እነዚያ ደቀ መዛሙርት የየሱስ የራስ መስዋዕት ፍሬ ነበሩ።”*—Ibid., pp. 623, 624.

## ሀ. የሱስ በመስቀል ላይ ስለመሞቱ ባሰበ ጊዜ ምን ጸሎት አቀረበ? ዮሐንስ 12:27፣ 28 (የመጀመሪያው ክፍል)።

"በዚህ ሁኔታ ላይ በነበረ ጊዜ የሱስ መራራውን ጽዋ በቅድሚያ እንደቀመሰ ያህል ነበር። በብቸኝነቱ ሰዓት ሰብአዊነቱ ትቶት ሲሸሽ፣ በሰዎች ሁሉ ፊት በእግዚ አብሔር እንደተቀጣ፣ እንደተመታና እንደተሰቃየ በሚመስልበት ወቅት እግዚአብሔር እንኳ የተለየው ይመስል ነበር። በሰው ሁሉ ፊት ክፉ ወንጀ ለኛ መስሎ በመቅረብ አሳፋሪና የውርደት ሞት የመሞቱ ትውስታ ሰቀጠ ጠው። የሱስ ከሰይጣን ጋር የሚያደርገው ግብግብ፣ የሰብአዊ ኃጢአት አሰ ቃቂ ሸክምና ኃጢአትን በተመለከተ የእግዚአብሔር ቁጣ ምን እንደ ሚመስል ባስታወሰ ጊዜ መንፈሱ ዝሎ የሞት ግርጣት በፊቱ ላይ ጉልቶ ታየ።

"ወዲያውኑ ለአባቱ ፈቃድ የመገዛት መለኮታዊ ስሜት አደረበትና «የመጣሁት ለዚች የመከራ ሰዓት ነው። አባት ሆይ! ስምህን አክብረው፣» አለ። የሰይጣን መንግስት የሚገለበጠው በክርስቶስ ሞት ብቻ ነው። ሰው የሚድነውና እግዚአብሔርም የሚከበረው በዚሁ ሁኔታ ብቻ ነው። የሱስ ስቃይን ለመቀበል ፈቃደኛ ሆነ፣ መስዋዕትነትንም ተቀበለ።—The Desire of Ages, p. 624.

## ለ. ከሰማይስ ምን መልስ ተሰማ? ዮሐንስ 12፡28 (የመጨረሻው ክፍል)። በዙሪያው የቆመው ህዝብስ ምን አለ? ዮሐንስ 12፡29

"ይህ ሰማያዊ ድምጽ እንደተሰማ ካንዣበበው ዳመና እንደ ነጸብራቅ የተወረወረ ብርሃን የሳት አጥርና የመለኮታዊ ኃይል እቅፍ መስሎ የሱስን ከበበው። ሕዝቡ ይህን ትዕይንት በፍርሃትና በመገረም ይመለከቱ ነበር። ጸጥ ብለው በድንጋጤ የሱስን አተኩረው ተመለከቱ። የአብ ምስክርነት ከተሰጠ በኋላ ደመናው ወደ ላይ ወጣና ተበተነ። በዚህ እኳኋን በአብና በወልድ መካከል የታየው ግልጽ ግንኙነት ለጊዜው ተገታ።

"«በዚያ የቆሙ ሰዎች ይህን በሰሙ ጊዜ ነጐድጓድ ነው! አሉ። ሌሎች መልአክ ነው የተናገረው! አሉ።» የሱስን ለማየት የመጡት ግሪካውያን ዳመናውን አዩ፣ ከሰማይ የተነገረውን ድምጽ ሰምተው ትርጉሙን አስተ ዋሉ፣ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑ ስለተገለጸላቸው ማንነቱን በትክክል ተገነዘቡ።

"የሱስ በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ በተጠመቀ ጊዜና በተራራ ላይበተለወጠ ጊዜ የእግዚአብሔር ድምጽ ተሰምቶ ነበር። አሁን ደግሞ በአገልግሎቱ መጨረሻ ላይ ብዙ ሰዎች በነበሩበትና በልዩ ሁኔታ ለሶስተኛ ጊዜ ተሰማ።"—Ibid., p. 625.

## 5. የአይሁዳውያን አለማመን | ሐሙስ፣ ሐምሌ 10

### ሀ. የሱስ ያደረጋቸው ብዙ ተአምራት ባዩ ጊዜ፣ እንዲሁም ከሰማይ የመጣው ድምፅ በሰሙ ጊዜ፣ አብዛኞቹ አይሁዶች ለእሱ ምን ምላሽ ሰጡ? ዮሐንስ 12፡37-41

"ይህ የእግዚአብሔር ድምጽ ከመሰማቱ ትንሽ ቀደም ብሎ የሱስ ስለ አይሁዶች ትክክለኛ ሁኔታ እውነቱን ግልጥልጥ አድርጎ ተናግሮ ነበር። የመጨረሻ ጥሪ አቀረበላቸው፣ የሚጠፉ መሆኑንም ነገራቸው « በዚህ ጊዜ ነበር እግዚአብሔር የልጁን ተልዕኮ በድጋሚ ያረጋገጠው። ይህን በማድረጉ እሥራኤላውያን የናቁትን እርሱ እውቅና ሰጠው። ስለዚህም ነው የሱስ «ይህ ድምጽ የመጣው ስለ እናንተ ነው እንጂ ስለ እኔ አይደለም፣» ያለው። ያ ድምጽ የየሱስ መሲሕነት የመጨረሻ ማስረጃና የሱስ እውነቱን ለመናገሩና የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆኑ ምልክት ነበር።"—The Desire of Ages, p. 625.

"በአንድ ወቅት አይሁዳውያን የሱስን «እኛ አይተን በአንተ እንድናምን ምን ተአምር ታደርጋለህ? ምንስ ትሠራለህ?» ብለው ጠይቀውት ነበር። ዮሐ 6:30። እነዚህ ሰዎች ዓይናቸውን ስለዘጉና ልባቸውን ስላደነደኑ ነው እንጂ ቁጥር ስፍር የሌለው ምልክት ተሰጥቶአቸው ነበር። አሁን ራሱ እግዚአብሔር አብ ስለተናገረ ተጨማሪ ምልክት እንዲያሳያቸው ለመጠየቅ ባይችሉም ለማመን ግን ፈቃደኛ አልሆኑም። - Ibid., p. 626.

### ለ. አንዳንድ ገዥዎች የክርስቶስ ተልእኮ እውነት መሆኑን እርግጠኞች ቢሆኑም ከወሰዱት እርምጃ እንድንጠነቀቅ ማስጠንቀቂያ የተሰጠን እንዴት ነው? ዮሐንስ 12:42፣ 43

"እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ከሚገኘው ክብር ይልቅ ከሰው የሚገኘውን ክብር ወደዱ። ራሳቸውን ከውርደትና ከሐፍረት ለማዳን ሲሉ ክርስቶስን ካዱ፣ ዘላለማዊ ሕይወትንም ችላ አሉ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በዘመናት ሁሉ ስንት ሰዎች ይህንኑ ነገር አድርገው ይሆን ኩቶ!"—Ibid.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች | አርብ፣ ሐምሌ 11

1. ክርስቶስ ሲወለድ እርሱን የፈለጉት ሰዎች እና አሁን ደግሞ ግሪኮች ምንን ያመለክታሉ?
2. የስንዴ እህል ፍሬ ምሳሌ በሕይወቴ ላይ የሚሠራው እንዴት ነው?
3. ብዙዎች ነጐድጓድ ነው ብለው በሚያስቡበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ድምፅ መለየት ያለብኝ እንዴት ነው?
4. የአይሁድ ገዥዎች ከተሰማቸው ከየትኞቹ ፍርሃቶችና ጭንቀቶች ነው መራቅ ያለብኝ?
5. ስለተቀበረው የስንዴ እህል ፍሬ ሁለቱን ሁኔታዎችን አብራራ።

# የአገልጋዮች አገልጋይ የሱስ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና።” (ዮሐ. 13፡15)።**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** The Desire of Ages, pp. 642–651.

“*መላው የክርስቶስ ሕይወት ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ አገልግሎት ነበር። ‘ለመገልገል ሳይሆን ለማገልገል፣’ (ማቴዎስ 20:28) የሚለውን ትምህርት ነበር ድርጊቱ በሙሉ የሚገልጠው።*”—The Desire of Ages, p. 642.

## 1. አረማዊ አስተሳሰብ — እሁድ፣ ሐምሌ 13

### ሀ. የአይሁድ እምነት (የክርስቶስን ደቀ መዛሙርት ጨምሮ) የበከለውና ዛሬም እኛንም ሊበክለን የሚችለው፣ ከሉሲፈር የመነጨው የትኛው አጥፊ አስተሳሰብ ነው? ሉቃስ 22:24፣ 25

“*ሉሲፈር የተመኘው የእግዚአብሔርን ኃይል እንጂ ባሕርዩን አልነበረም። ሉሲፈር ከፍተኛ ማዕረግ ለማግኘት ተመኘ፣ በእርሱ መንፈስ የሚመራ ሁሉ ያንኑ ነገር ያደርጋል። ስለዚህ መቃቃር፣ አለመግባባትና ጠብ መከተሉ አይቀርም። የበላይነት የኃያላኑ ሽልማት ይሆናል። የሰይጣን መንግሥት የኃይል መንግሥት ነው። በዚህ መንግሥት ሥር የሚተዳደር ሰው ሌላውን የእድገቱ መሰናክል እንደሆነበት ወይም ከፍ ወዳለ ቦታ ለመሸጋገር እንደመረማመጃው አድርጐ ያየዋል።* - The Desire of Ages, pp. 435, 436

“*በዚያ ዘመን በዓለማዊ መንግሥታት ዘንድ ማዕረግ ማለት የግል እድገት ማለት ነበር። ተገዥው ሕዝብ የሚኖረው ለገዥው ክፍል ጥቅም ነበር። ታዋቂነት፣ ሐብትና ትምህርት ለመሪዎች ጥቅም ሲባል የብዙሐኑ ሕዝብ መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች ነበሩ። በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት ሰዎች ኃላፊነት መወሰን፣ መደሰትና መግዛት ሲሆን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት ሰዎች እጣ ፈንታ ግን መታዘዝና ማገልገል ነው። ሃይማኖትም እንደሌላው ነገር ሁሉ የሥልጣን ጉዳይ ነበር። ሕዝቡ ማመንና መተግበር የሚጠበቅባቸው አለቆቻቸው ያዘዙዋቸውን ነበር። ሰው በሰውነቱ ለራሱ የማሰብና የመሥራት መብቱ ፈጽሞ አይታወቅም ነበር።*”—Ibid., p. 550.

“*በአንዳንድ ሰዎች ላይ በሚታየው፣ በመንፈሳዊ ትዕቢት፣ ሌሎችን ለመምራት ባላቸው ፍላጎት፣ እንዲሁም ለክብር ወይም ለሥልጣን ባላቸው ከፍተኛ ጉጉት… ቤተ ክርስቲያን ሊትታወክና ሰላምዋን ልታጣ ትችላለች።*”—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 241.

## ሀ. ከፍተኛ ሥልጣን ለማግኘት ካለ ከፍተኛ ጉጉት በተቃራኒ የሆነ፣ የሱስ የመሠረተው መሠረታዊ ሥርዓት ምንድነው? በዚህ ረገድስ ምን ምሳሌ ሰጥቶናል? ሉቃስ 22:26፣ 27፤ ዮሐንስ 13፡13-16

"ክርስቶስ በልዩ መርሖች ላይ የተመሠረተ መንግሥት በማቋቋም ላይነበር። ሰዎችን የጠራቸው ለሥልጣን ሳይሆን አገልግሎት እንዲሰጡና ብርቱዎቹ የደካሞችን ችግር እንዲያቃልሉ ነው። ኃይል፣ ማዕረግ፣ ልዩ ችሎታ ወይም ትምህርት የነበረው ሁሉ ሰዎችን የማገልገል ከፍተኛ ግዴታ ተጥሎበታል። ...

"በክርስቶስ መንግሥት የአለቃ ተጽዕኖ ወይም ያለ ፈቃድ የሚደረግ የሥነ ምግባር ግዳጅ የለም። የሰማይ መላእክት ወደ መሬት የሚመጡት እኛን ለመግዛትና እንድንሰግድላቸው ለማስገደድ ሳይሆን የምሕረት መልእክተኛ በመሆን ሰብአዊ ዘርን ከወደቀበት በማንሳት ከሰዎች ጋር ለመተባበር ነው።"—The Desire of Ages, pp. 550, 551.

## ለ. ተፈጥሯዊ ዝንባሌያችን በእርሱ ልንተካው በሚጋበው፣ ክርስቶስ የተሳሳቱ ሰዎችን ያስተናገደበትን አያያዙን ግለጽ። ፊልጵስዩስ 2:3፣ 4

"በባህሪያችን ውስጥ ባለን ልምድ የሌሎችን ስህተቶች እና ውድቀቶች ላይ ማትኮር እና አቃቅር ፈላጊነት የሰበአዊ ፍጥረት ተፈጥሯዊ ዝንባሌ ቢሆንም ነገር ግን መልካም ባህርይ አይደለም።

"ወንድም ቢ. ከወንድሞቹ ጋር አንድነት ለማምጣት አይሞክርም፣ በራስ የመተማመን ስሜቱ ከሌሎች ጋር አንድነት ቢፈጥር ባይፈጥር ምንም የተለየ ነገር እንደለለ እንዲሰማው አድርጎታል። አእምሯቸው (የአስተሳሰብ አድማሳቸው) ከእሱ በጣም ያነሰ እንደሆነ እና አስተያየታቸውንና ምክሮቻቸውን መቀበል ለእሱ ትልቅ ውርደት እንደሆነ ይሰማዋል። . . . በጣም ጥበበኛ እና ብዙ ልምድ ያለው እንደሆነ ስለሚሰማው ሌሎች እንኟ እሱ በምንም ነገር ላይ ጥንቃቄ ማድረግ እንደማያስፈልገው ያምናል። ስለራሱ ችሎታዎች ከፍተኛ ግምት ያለው እና በእራሱ ስኬት ላይ ስለሚተማመን ለማንኛውም ድንገተኛ አደጋ ዝግጁ ነኝ ብሎ ያምናል።"—Testimonies for the Church, vol. 3, pp. 444, 445

"አንዳንዶች እንደ ደመና በላያቸው ላይ ተሸክመው የሚዞሩት፣ ሌሎች የሚተነፍሱበትን ከባቢ አየር የሚያቀዘቅዘውና የሚያሳድሩት ዓለማዊ ራስ ወዳድነት ተጽዕኖ የሌሎች ነፍሳትን ሕመም ያስከትላል እንዲሁም ብዙውን ጊዜ እያቀዘቀዛቸው እስከ ሞት ያደርሳቸዋል።"—Ibid., p. 528.

"በወንድሞች መካከል ያለው ፍቅር ከራሳቸው ይልቅ ሌሎችን እንዲመለከቱ (እንዲመርጡ) የሚመራቸው ከሆነ የራሳቸውን መንገድ እና ምኞት ለሌሎች ሲሉ መተው ይኖራል።"—Gospel Workers, p. 447.

## ሀ. ከፋሲካ ጥቂት ቀደም ብሎ ሐዋርያቱ ምን ያሳስቧቸው ነበር? ማቴዎስ 20:20–24፤ ሉቃስ 22፡24

"«ከሁላችን የሚበልጥ ማን ነው? እያሉ እርስ በርሳቸው ይከራከሩ ጀመር።» ክርስቶስ ባለበት የዚህ ዓይነት ውድድር መታየቱ አዳኛችንን እጅግ አሳዘ ነው፣ አቀሰለውም። ደቀመዛሙርቱ የሱስ በዳዊት ዙፋን ላይተቀምጦ ሥልጣን ይይዛል ከሚለው እምነት አልተላቀቁም ነበር። እያንዳንዳቸው በዚያ መንግሥት ከፍተኛ ሥልጣን ለማግኘት ይመኙ ነበር። የራሳቸውንና የሌሎችን ችሎታ በማ መዛዘን ሌሎችን ከፍ አድርጐ ከማየት ፈንታ ራሳቸውን ለማስቀደም ፈለጉ። ቀደም ሲል ያዕቀብና ዮሐንስ በክርስቶስ ዙፋን ግራና ቀኝ ለመቀመጥ ያደ ረጉት ጥያቄ ሌሎቹን አስቆጥቶ ነበር። ሁለቱ ወንድማማቾች ከፍተኛውን ማዕረግ ለማግኘት ደፍረው መጠየቃቸው አሥሩን ደቀመዛሙርት ስላስከፋቸው ሁለቱን የማግለል አዝማሚያ አስግቶ ነበር። በትክክል እንዳልተገመገሙና ታማ ኝነታቸውና ችሎታቸው እንዳልታወቀላቸው ተሰማቸው። ያዕቀብንና ዮሐንስን በማግለል የከረረ አቋም የነበረው ይሁዳ ነበር።

ደቀመዛሙርቱ ወደ ሰገነቱ ሲገቡ ልባቸው በቅሬታ መንፈስ ተሞልቶ ነበር። ይሁዳ ተሻምቶ ከየሱስ በስተግራ በኩል ተጠግቶ ሲቀመጥ ዮሐንስ ከየሱስ በስተቀኝ ተቀመጠ። ይሁዳ ከፍተኛ ደረጃ ካለ ለኔ ይገባኛል ባይነበር። ያ ከፍተኛ ማዕረግ ከክርስቶስ ቀጥሎ ያለ ነው፡ ብለው ገምተው ነበር።"—The Desire of Ages, pp. 643, 644.

## ለ. ቀደሞ የተነገረው ምሳሌ፣ ግን ደቀ መዛሙርቱ ረስተውት የነበረና በመካከላቸው ሌላ አለመግባባት እንዲፈጠር ያደረገው ምን ነበር? ማቴዎስ 18:1-4

"ለአለመግባባት መንስኤ የሆነ አንድ ነገር ተፈጠረ። በድግስ ጊዜ አገልጋይ የእንግዶችን እግር እንዲያጥብ ማድረግ የተለመደ ሥርዓት ስለነበር ለዚህ አገልግሎት አስፈላጊው ነገር ሁሉ ተዘጋጅቶ ነበር። ማንቆርቆሪያው፣ ገበቴውና ፎጣው ለእግር እጥበቱ ቀርቦ ነበር። እግር የሚያጥብ አገልጋይባለመኖሩ ያን አገልግሎት መፈጸም የደቀመዛሙርቱ ፈንታ ነበር። እነርሱ ግን እግር ማጠብ ክብራቸውን የሚነካ ወይም የሚያዋርዳቸው ስለመሰላቸው የአገልጋይ ሥራ ላለመሥራት ወሰኑ። ሁሉም አይመለከተንም በማለት በግድየለሽነት መንፈስ ዝም ብለው ተቀመጡ። በዝምታቸው ራሳቸውን ዝቅ ለማድረግ አለመፈለጋቸውን ገለጹ።"—Ibid., p. 644.

"ቃላቶቻችን በእግዚአብሔር ጆሮ እንዴት እንደሚሰሙ፣ ራስ ወዳድነት አስተሳሰባችን በእሱ ፊት እንዴት እንደሚታይ፣ ሌሎችን በምንፈርድበት እና በምንኮንንበት ጊዜ እናስብ፣ እነሱ በልባቸውም ሆነ በዓላማቸው በእግዚአብሔር ፊት ከእኛ የተሻሉ ሊሆኑ ይችላሉና።"—The Signs of the Times, February 19, 1885.

## ሀ. የሱስ ደቀ መዛሙርቱ ቅድሚያ እንዲወስዱ በትዕግሥት ከጠበቀ በኋላ በመጨረሻ ምን አደረገ? ዮሐንስ 13፡3-5

"[ዮሐንስ 13:5 የተጠቀሰው] ይህ ድርጊት የደቀ መዛሙርቱን ዓይን ከፈተላቸው። ከፍተኛ ሐፍረትና ውርደት ተሰማቸው። በአንደበት ያልተገለጸውን ተግሳጽ አስተዋሉ፣ እራሳቸውንም በልዩ ሁኔታ ማየት ጀመሩ።

በዚህ አኳኋን የሱስ ፍቅሩን ለደቀመዛሙርቱ ገለጸላቸው። የራስ ወዳድነት መንፈሳቸው እጅግ ቢያሳዝነውም ስለነበረባቸው ችግር ውዝ ግብ ማንሳት አልፈለገም። በዚህ ፈንታ ሊረሱት የማይችሉ ማስረጃ ሰጣቸው።"—The Desire of Ages, pp. 644, 645.

## ለ. ጴጥሮስ ተራው ሲደርስ ምን አደረገ? ዮሐንስ 13፡6-8 (የመጀመሪያ ክፍል)።

"ጴጥሮስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያምንበት ጌታ እንደ አገልጋይ ሲሠራ ማየት የማይችለው ነገር ሆነበት። ጌታ ያን ያህል ራሱን በማዋረዱ የጴጥሮስ ሰውነት በመላ ታወከ። ለዚህ ሲል የሱስ ወደ ዓለም እንደመጣ መገንዘብ ተሳነው።"—Ibid., pp. 645, 646.

## ሐ. ይሁዳ ለሰይጣን ፈተናዎች ምን ያህል እጁን ሰጥቶ ነበር—ክርስቶስስ ይህን እንደሚያውቅ ያሳየው እንዴት ነበር? ዮሐንስ 13:2፣ 10፣ 11

"ከፋሲካ ቀደም ብሎ ይሁዳ ከካህናቱና ከጸሐፍቱ ጋር ሁለት ጊዜ ተገናኝቶ የሱስን አሳልፎ ሊሰጣቸው ተዋውሎ ጨርሶ ነበር። ነገር ግን ይህን ካደረገ በኋላ ከፉ ነገር ያልሠራ ንጹህ ሰው በመምሰልና በድግሱ በሚደረገው ዝግጅት ለመሳተፍ የሚፈልግ ዓይነት መስሎ ከደቀ መዛሙርቱ ጋርተቀላቀለ። ደቀመዛሙርቱ የይሁዳን ዕቅድ አላወቁም። ምስጢሩን ያወቀበት የሱስ ብቻ ነበር ሆኖም ለነፍሱ ይላላለት ስለነበር አላጋለጠውም። ስለ ኢየሩሳሌም መጥፋት በማዘን እንዳለቀሰ ሁሉ ለይሁዳ ተጨነቀለት። እንዴት ልተውህ እችላለሁ? በማለት ጌታን ያስጨነቀው ፍቅር ለይሁዳ ተሰምቶታል። የሱስ አቧራ የለበሱትን እግሮች አጥቦ በፎጣ በሚያደርቅበት ጊዜ ይሁዳ ንስሐ ለመግባት ልቡ በጣም ተነክቶ ነበር። ነገር ግን ራሱን ዝቅ ለማድረግ አልፈለገም።"—Ibid., p. 645.

## 5. የእግር እጥበት አስፈላጊነት | ሐሙስ፣ ሐምሌ 17

### ሀ. የሱስ በዚህ ድርጊት ምን ለማድረግ ፈልጎ ነው? ዮሐንስ 13፡8 (የመጨረሻው ክፍል)።

*"ጌታችን በፈጸመው ድርጊት ይህ የትሕትና መግለጫ አገልግሎት የተቀደሰ የእምነት መመሪያ ሆነ። ደቀመዛሙርቱ ጌታ የሰጣቸውን የትሕትናና የአገልገሎት ትምህርት ዘወትር ለማስታወስ እንዲረዳቸው ይህን ሥርዓት መፈጸም ነበረባቸው። "ይህ የእግር እጥበት ሥርዓት የሱስ ለቅዱስ ቁርባን ቅድመ ዝግጅት ያቋቋመው ነው። ትዕቢት መቃቃርና ሹመት ለማግኘት መጒሻሸም እያለ ከክርስቶስ ጋር አንድነት መመሥረት አይቻልም። ይህ ዓይነት መንፈስ እያለ የሥጋና የደሙን ቁርባን ለመቀበል ዝግጁ አንሆንም። ስለዚህ የሱስ የትሕትናው መታሰቢያ የሆነው ሥርዓት መጀመሪያ እንዲከናወን ወሰነ።"*—The Desire of Ages, p. 650.

### ለ. የሱስ እግርን ከማጠብ ሥነ ሥርዓት በኋላ የተናገራቸው ቃላት የትኞቹ ናቸው? ዮሐንስ 13፡12-17

*"ደካሞች ነን፣ ብዙ ጊዜም ተሳስተናል። ወደ ጌታ በንስሐ እና ኃጢአትን በመናዘዝ እንመለስ። በጌታ ቤት ስርአት ለመካፈል ስንሰበሰብ በአቅማችን ማስተካከል የሚቻል እስከሆነ ድረስ ስህተታችን ሁሉ ለማስተካከል እንጣር። በወንድምህ ፊት እግሩን ለማጠብ ጎንበስ ስትል ለራስህ እንዲህ በል፣ ይህን ወንድሜን ከእኔ እንድለይ የሚያደርግ አንድ ነገር በልቤ ውስጥ ይኖር ይሆንን? ከሆነ ኃጢአትህን ከልብህ በመናዘዝ አስወግደው። በዚህም ልብ ለልብ ይጸናል እንዲሁም የእግዚአብሔርም በረከት ይገለጣል።"*—Reflecting Christ, p. 283.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች | አርብ፣ ሐምሌ 18

1. በሰማያዊውና በምድራዊ አመለካከት መካከል ያለውን ልዩነት ግለጽ።
2. የወንድሜን እግር ለማጠብ ፈቃደኛ ካልሆንኩ ምን እምቢ እያልኩኝ ነው?
3. የይሁዳ ውስጣዊ ሁኔታ ለእኔ ማስጠንቀቂያ የሚሆነው እንዴት ነው?
4. ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን አመለካከት እንዴት እንደለወጠ ግለጽ።
5. እግር የማጠብ ሥነ ሥርዓት ዓላማ እና ጠቀሜታ ምንድን ነው?

# የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ
## ሰንበት፣ ሐምሌ 26፣ 2017



## ለጂ.ሲ. ትምህርት ክፍል



ትምህርት ልክ እንደ መቀደስ የህይወት ዘመን ስራ ነው። ከመጀመሪያዎቹ ዓመታት ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ፣ ትምህርት ሁል ጊዜ የሰው ልጅ ልምድ ውስጣዊ አካል ይሆናል። በዚህ ሰንበት ይህንን የቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ አካል ተደራሽነቱን ለማስፋት እንድትረዱን እንጠይቃለን።

ሚስዮናውያን መሆንን ከመጀመሪያዎቹ ዓመታት መማር አለብን። “እያንዳንዱ እውነተኛ ደቀ መዝሙር ወንጌላዊ ሆኖ በአምላክ መንግሥት ውስጥ ይወለዳል።”—The Desire of Ages, p. 195. “ለልጆችህም አጥብቀህ አስተምራቸው፥ በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተናገርአቸው” (ዘዳ 6፡7)። በዚህም ድል ነስተን ድላችንን ካስጠበቅነው፣ ኃጢያት እና ኃጢአተኞች በማይኖሩበት በሰማይም እንኳን የትምህርት ስራ ይቀጥላል።

አሁን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ፣ ቤተ ክርስቲያናችን በሰበአዊ ቤተሰብ ውስጥ ለእያንዳንዱ የዕድሜ ክልል ተገቢውን ትምህርታዊ መሠረት ለመመሥረት ቁሳቁሶችን ለማቅረብ ዝግጁ መሆን አለባት።

በሚያሳዝን ሁኔታ፣ አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት መሰረታዊ ትምህርቶችን ከማስተማር ይልቅ ወደ ዓለማዊነት ማስተማሪያ ማዕከላት ተቀይረዋል። ብዙዎች ትምህርት በልጆቻቸው ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንደሚያሳድር በመገንዘባቸው ለአምላክ ክብር በሚሆን መልኩ ለማስተማር የሚረዱ ቁሳቁሶችን ጠይቀዋል። ስለዚህ የጂ.ሲ. ትምህርት ክፍል ይህንን ዓላማውና ትኩረቱ አድርጎ አጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርት እየፈጠረ ነው። ከአስተማሪዎቻችን እና ከሌሎች ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች ጋር በመተባበር ይህንን ስርአተ ትምህርት የማዘጋጀት ስራ በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ነው።

ሆኖም የፕሮጀክቱ ወጪ ከተገኘው ከሀብት ድጋፍ ድምር ይበልጣል። ቁሳቁሶቹን ለማዘጋጀት፣ ለመተርጎም እና በድሃ ሀገራት ላሉትም ከአቅማቸው ጋር ተመጣጣኝ ለማድረግ የእናንተን ለጋስ አስተዋጽዖ እንፈልጋለን። የእናንተ ድጋፍ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ቁሳቁሶች እንድናዘጋጅ ያስችለናል፣ ይህም የሚጠቀሙባቸው ተማሪዎች “ለዚህ ሕይወት ጠቃሚ እና ለዘላለም አምላክን ለማገልገል ብቁ እንዲሆኑ” ያስችላልና።”—Counsels to Parents, Teachers, and Students, p. 495.

ይህ ፕሮጀክት ትልቅ እንደሆነ እንገነዘባለን፣ ነገር ግን እጅግ አስፈላጊም ነው። በእናንተ ድጋፍ ከሂሳብ እስከ ቋንቋ እስከ ማህበራዊ ሳይንስ ድረስ ያሉትን ከእኛ መካከል ታናናሾቹ የሆኑ እንኳን የወንጌልን መልእክት በተቻለ መጠን ለአለም ሁሉ ለማድረስ የሚረዱ ቁሳቁሶችን እናዘጋጃለን።

አስቀድሚን እናመሰግናለን እና እግዚአብሔር ስጦታዎችንና ሰጭዎችን ይባርክ!

የጂ.ሲ. ትምህርት ክፍል

## መንገድ፣ እውነት እና ህይወት

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “የሱስም። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።” (ዮሐንስ 14፡6)።**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ**፡ Testimonies for the Church, vol. 8, pp. 265–269.

*“ይህች ምድር በበደል ምክንያት ከሰማይ ተቋርጣ ነበር፤ በሰውና በፈጣሪው መካከል የሚያገናኘው መስመር ተቋረጠ፤ ነገር ግን ሰው ወደ አባቱ ቤት እንዲመለስ መንገዱ ተከፈተ።”*—My Life Today, p. 260.

### 1. የሱስ ወደ አባቱ መመለሱን አስታወቀ — እሁድ፣ ሐምሌ 20

### ሀ. የሱስ በምድር ላይ የተልእኮውን ፍጻሜ ያሳወቀው በምን ቃል ነው? ዮሐንስ 13፡33 ሌላ ምን አይነት መልዕክት አስተላልፏል ዮሐንስ 13:34፣ 35

*“ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ከሰጣቸው የመጨረሻዎቹ ትእዛዛት አንዱ ‘እኔ እንደ ወደድኳችሁ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ’ የሚለው ነው። ዮሐ . 13፡34 ዛሬ እኛ ይህን ትዕዛዙን እየታዘዝን ነው ወይስ ክርስቶስን የማይመስል ሸካራ ባሕርይን እያዳበርን ነው? በማንኛውም መንገድ ሌሎችን አስከፍተን ወይም አቁስለን ከሆነ፣ ጥፋታችንን መናዘዝና እርቅን መፈለግ ግዴታችን ነው። በረከቱን ልንለምን በእግዚአብሔር ፊት ስንቀም ልናደርግ የሚገባን በጣም አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት ይህ ነውና።* —Christ’s Object Lessons, p. 144

### ለ. በጴጥሮስ እና በየሱስ መካከል የጌታን መለየት በተመለከተ ምን ውይይት ተደረገ? ዮሐንስ 13፡36–38

*“ብዙዎች ዛሬ ጴጥሮስ በሙሉ በራስ መተማመን ጌታውን አልክድም ብሎ በቆመበት ቦታ ቆመዋል። እነዚህ ከራስ መተማመናቸው ብዛት የተነሳ በቀላሉ በሰይጣን ወጥመዶች ውስጥ ይወድቃሉ። ነገር ግን ደካማነታቸውን የሚገነዘቡ ሁሉ ከራሳቸው በላይ በሆነ ኃይል ይታመናሉ። ከዚያም ወደ አምላክ ሲመለከቱ ሰይጣን በእነርሱ ላይ ምንም ኃይል አይኖረውም። በራሳቸው የሚታመኑ ግን በቀላሉ ይሸነፋሉ።”*—Our High Calling, p. 307.

## ሀ. የሱስ ሰገነት ላይ እያለ ለደቀ መዛሙርቱ ምን አጽናኝ ቃል ነግሯቸዋል እንዲሁም ምን ቃል ገባላቸው? ዮሐንስ 14:1፣ 2

*"[ዮሐንስ 14:1-4 የተጠቀሰው] ወደ ዓለም የመጣሁት ለእናንተ ብየ ነው። የምሠራውም ስለ እናንተ ነው። በሔዱሁም ጊዜ በቅንነት ለእናንተ እሠራለሁ። እናንተ እንድታምኑ በማለት ራሴን ለዓለም ለመግለጽ መጣሁ። አሁንም ስለ እናንተ ከአብ ጋር ለመተባበር ወደ እርሱ እሔዳለሁ ማለቱ ነበር። የክርስቶስ መለየት ደቀ መዛሙርቱ ይደርስብናል ብለው ከሰጉት ነገር ተጻራሪ ነው። የእርሱ መለየት የመጨረሻ መለያየት ማለት አልነበረም። እርሱ የሚሔደው ለእነርሱ ቦታ ለማዘጋጀት ሲሆን ካዘጋጀላቸው በኋላ ተመልሶ ይመጣና እርሱ ወዳለበት ይወስዳቸዋል። እርሱ ቦታ በሚያዘጋጅላቸው ጊዜ እነርሱ በበኩላቸው ባሕሪያቸውን በመለኮታዊ አምሳያ ማነጽ ነበረባቸው።*—The Desire of Ages, p. 663.

## ለ. ክርስቶስ በመልእክቱ ውስጥ ምን አስፈላጊ ድርጊትን አካቷል? ዮሐንስ 14፡3

*"የክርስቶስ ዳግም ምጽዓት የተስፋ ቃል በደቀ መዛሙርቱ አእምሮ ውስጥ ሁል ጊዜ ትኩስ ሆኖ ይቆይ ነበር። ወደ ሰማይ ሲወጣ ያዩት የሱስ፣ በዚህ ምድር ያሉትን ራሳቸውን ለአገልግሎቱ አሳልፈው የሚሰጡትን ወደ ራሱ ሊወስድ ዳግመኛ ይመጣል። ‹እስከ ፍጻሜ ድረስ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ› ያለው ያ ድምጽ፣ በመንግሥቱ ‹እንኳን ደህና መጣችሁ› ብሎ ይቀበላቸዋል።*—The Acts of the Apostles, p. 33.

## ሐ. ቶማስ ስለ መንገዱ ምን ጥያቄ አቀረበለት? ምን መልስስ አገኘ? ዮሐንስ 14:5፣ 6

*"ወደ ሰማይ የሚያደርሱ መንገዶች ብዙ አይደሉም። እያንዳንዱ ሰው የራሱን መንገድ መምረጥ አይችልም። ክርስቶስ «መንገድ... እኔ ነኝ፣ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ማንም ወደ አብ የሚመጣ የለም» ብሎአል። የመጀመሪያው የወንጌል ስብከት በተሰበከበት በኤደን ገነት የሴትዋ ዘር የእባቡን ራስ እንደሚቀጠቅጥ ከተነገረበት ጊዜ አንስቶ ክርስቶስ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት መሆኑ ጐልቶ ታይቶአል። በአዳም ዘመን አቤል የአዳኛችን ደም ምሳሌ የሆነውን የበግ ደም ለእግዚአብሔር ባቀረበ ጊዜ የሱስ መንገድ ነበር። ክርስቶስ አበውና ነቢያት የዳኑበት መንገድ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት የምንችልበት ብቸኛው መንገድ እርሱ ነው።"*—The Desire of Ages, p. 663.

## ሀ. የሱስ ራሱን ከአብ ጋር አንድ አድርጎ ያሳወቀው እንዴት ነው—ይህስ ከእኛ ጋር ምን ግንኙነት አለው? ዮሐንስ 14፡7

"ክርስቶስ እግዚአብሔርን የፍቅር፣ ምሕረት፣ ርኅራኄ እና ቸርነት የሞላበት አምላክ አድርጎ ለዓለም ሊገልጥ መጣ። ሰይጣን የመለኮትን ዙፋን ሊሸፍንበት የሞከረበት ድቅድቅ ጨለማ በዓለም ቤዛ ተጠራርጎ ጠፋ፣ አብም እንደገና ለሰዎች የሕይወት ብርሃን ሆኖ ተገለጠ።"—Testimonies for the Church, vol. 5, pp. 738, 739.

## ለ. ፊልጶስ ለየሱስ ምን ልመና አቀረበ? የጌታ ምላሽስ ምን ትርጉም ነበረው? ዮሐንስ 14፡8-11

"ፊልጶስ አብን አሳየንና ይበቃናል ብሎ ወደ የሱስ በመጣ ጊዜ … ክርስቶስ የአብ መገለጫ ሆኖ ወደ ዓለም እንደተላከ ገልጿል። በባሕርይው ጨዋነት፣ በምሕረቱና በርኅራኄው፣ በፍቅሩና በቸርነቱ፣ የመለኮታዊ ፍጹምነት ምሳሌ፣ የማይታየው አምላክ አምሳል ሆኖ በፊታችን ቆሞአል።—Ibid., vol. 5, p. 739.

"ክርስቶስ አብን በእምነት ብቻ ማየት እንደሚችሉ በአጽንኦት አሳስቧቸዋል፤ አምላክ በማንኛውም ሰው በውጫዊ መልክ ሊታይ አይችልምና።"—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 5, pp. 1141, 1142.

"ክርስቶስ ሰው በመሆኑ አምላክነቱ አልተቋረጠም። ምንም እንኳን ሰው እስከ መሆን ድረስ ራሱን ቢያዋርድም ከሦስቱ ስላሴዎች አንዱ መሆኑ አልቀረም። በሰዎች መካከል እግዚአብሔር አብን በትክክል መወከል የሚችል ክርስቶስ ብቻ ነበር፣ ደቀ መዛሙርቱ ይህንን ውክልና ለሶስት ዓመታት የማየት እድል ነበራቸው። …

"እምነታቸው ማንም ሰው በራሱ ኃይል ባልሠራው ወይም ፈጽሞ ሊሠራው በማይችለው በክርስቶስ ሥራ ምስክርነት ላይ ያለ ምንም ስጋት ሊመሠረት ይችላል። የክርስቶስ ሥራ ስለ መለኮታዊነቱ መስክሮአል። አብም በእርሱ አማካይነት ተገልጾአል።

"ደቀ መዛሙርቱ በአብና በወልድ መካከል ያለው ይህ ዋና ግንኙነት መኖሩን ቢያምኑ ክርስቶስ በመጥፋት ላይ ያለውን ዓለም ለማዳን ሲል የሚደርስበትን ስቃይና ሞት በሚያዩበት ጊዜ እምነታቸው አይናጋም። ክርስቶስ ተከታዮቹን ከነበሩበት ዝቅተኛ የእምነት ደረጃ አንስቶ እርሱ ሥጋ የለበሰ አምላክ መሆኑን በማመን ልዩ ሕይወት ሊያገኙ ወደሚችሉበት ደረጃ ለማድረስ ምኞቱ ነበር።"—The Desire of Ages, pp. 663, 664.

## ሀ. የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ምን ታላቅ አጋጣሚዎችን ሰጥቷቸዋል? ዮሐንስ 14፡12

*"አዳኛችን መለኮታዊነቱ ለምን ምክንያት ከሰብአዊነት ጋር እንደተዋሃደ ደቀ መዛሙርቱን እንዲያስተውሉ ለማድረግ ከፍተኛ የሆነ ጉጉት ነበረው። ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣው ሰውን በማደስ ወደ ላይ ከፍ ለማድረግ የሚችለውን የእግዚአብሔርን ኃይል ለመግለጽ ነው። ክርስቶስ በተከታዮቹ ለዓለም ይገለጽ ዘንድ እግዚአብሔር በክርስቶስ ተገለጸ። ክርስቶስ ሰው በእምነት ሊያገኝ የማይችለው ባሕርይ አልታየበ ትም፤ እንዲሁም ሰው በእምነት ሊያገኘው የማይችል ኃይልም አልተጠቀ መም። የክርስቶስ ተከታዮች እንደ ክርስቶስ ራሳቸውን ለእግዚአብሔርቢያስገዙ እንደ እርሱ ፍጹም የሆነ ሰብአዊ ሕይወት ለመኖር ይችላሉ።"*

*"«እንዲያውም ከዚህ የበለጠ ይሠራል፣ ምክንያቱም እኔ ወደ አብ እሄዳለሁ።» ይህን ሲል የሱስ የደቀ መዛሙርቱ ሥራ ከእርሱ ሥራ በዓይነት ሳይሆን በስፋት እንደሚልቅ ማመልከቱ ነው። እርሱ የተናገረው ተአምርስለመሥራት ብቻ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ስለሚከናወኑት ነገሮች ሁሉ ነው።"*

*"ደቀ መዛሙርቱ የሱስ የሰጣቸው ተስፋ መፈጸሙን የተገነዘቡት ከእርገቱ በኋላ ነው። ለእነርሱ የክርስቶስ ስቅለት፣ ትንሣኤና እርገት አሌ የማይባል እውነታ ነው። ትንቢቶች በግልጽ ሲፈጸሙ አዩ። ቅዱሳት መጻሕፍትን መርምረው በውስጣቸው የሚገኘውን ትምህርት ከዚያ በፊት ባልነበራቸው እምነትና እርግጠኛነት ተቀበሉት። መለኮታዊዩ መምህር ስለማንነቱ የተናገረው ሁሉ እውነት እደሆነ አወቁ። በእነርሱ ሕይወት ላይየደረሰውን እየተናገሩና እግዚአብሔርን ስለ ፍቅሩ እያሞገሱ የሰዎችን ልብ በመሳብ ብዙ ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ አደረጉ።"*—The Desire of Ages, pp. 664, 667.

## ለ. በሁሉም ዘመናት ተስፋ ለማምጣት የሱስ ምን ማረጋገጫ ሰጥቷል? ዮሐንስ 14:13፣ 14

*"ደቀ መዛሙርቱ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ከአዳኛችን ወሰን የሌለው ኃይል የሚገኝ መሆኑን ገና አላወቁም ነበር። ስለዚህ «እስከ አሁን በስሜ ምንም ነገር አልለመናችሁም፣» አላቸው። ዮሐ 16:24። በሥራቸው ክንውን ለማግኘት ምስጢሩ ብርታትና ጸጋ ለማግኘት በእርሱ ስም መጠየቅ መሆኑን አስረዳቸው። ጥያቄያቸውን ለማቅረብ እርሱ በአብ ፊት እንደሚገኝ ነገራቸው። ራስን ዝቅ በማድረግ የሚቀርብን የልመና ጸሎት የሱስ በጠያቂው ስም የራሱ እንደሆነ አድርጐ ለአብ ያቀርበዋል። እያንዳንዱ እውነተኛ ጸሎት በሰማይ ተደማጭነት ያገኛል። ጸሎቱ የሚቀርበው በተጐላደፈ አንደበት ይሆን ይሆናል ይሁን እንጂ ከልብ የመነጨ ከሆነ የሱስ ከሚያገለግልበት ቤተ መቅደስ ስለሚደርስ አዳኛችን በራሱ የፍጽምና መአዛ አሰውቦና የተዛባውን አቃንቶ ለአባቱ ያቀርበዋል።"*—Ibid., p. 667.

## ሀ. የሱስ ከአብ ጋር ያለውን ግንኙነት ሲገልጽ ደቀ መዛሙርቱ ከየሱስ ጋር ያሳለፉትን ልዩ ጊዜ ግለጽ (ዮሐንስ 14፡8–10)—እና እኛ ደግሞ ከሰማይ ጋር እንደዛ ያለ ሕብረት እንዴት ማጣጣም እንደምንችል ግለጽ። መኃልየ መሓልይ 2:3፣ 4

"ክርስቶስ [በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14፡8-10] እነዚህን ቃላት ሲናገር የእግዚአብሔር ክብር በፊቱ በራ፣ እናም ሁሉም ቃሉን በጥሞና ሲያዳምጡ የተቀደሰ ፍርሃት ተሰምቷቸው ነበር። ልባቸውም የበለጠ ወደ እርሱ እንደቀረበ ተሰማቸው፣ እናም በላቀ ፍቅር ወደ ክርስቶስ ሲሳቡ በዛው ልክ በላቀ ፍቅር እርስ በርሳቸው ተሳሳቡ። ሰማይ ለእነሱ እጅግ ቅርብ እንደሆነና የሚሰሙትም ቃል ከሰማዩ አባት በቀጥታ የተላከላቸው መልዕክት እንደሆነ ተሰማቸው።"—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 5, p. 1142.

"ብዙ ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች በጭንቀትና በውጥረት የተሞሉ፣ በሥራ የተጠመዱ በመሆናቸው በእግዚአብሔር ተስፋዎች ውስጥ በጸጥታ ለማረፍ (ለማሰላሰል) ጊዜ የላቸውም፤ ሰላምና ጸጥታ ማግኘት እንደማይችሉ ሆነው የሚሠሩ ብዙዎች ናቸው። ለእነዚህ ሰዎች የተሰጠው የክርስቶስ ግብዣ ግን "ወደ እኔ ኑ፣ እኔም አሳርፋችኋለሁ" የሚል ነው። .

"በክርስቶስ ፍቅር ጥላ ሥር ለማረፍ ከአቧራማ የሕይወት ጎዳናዎች እንመለስ። በእዚያ ስናርፍ ለታላቁ ተጋድሎ ብርታት እናገኛለን። በእዚያ ድካምንና ጭንቀትን እንዴት መቀነስ እንደምንችል እና እግዚአብሔርን ለማመስገን እንዴት መናገር እና መዘመር እንደምንችል እንማራለን። ደካሞችና ሸክም የከበደባቸው ሁሉ የጸጥታ እምነትን ከክርስቶስ ይማሩ። በጥላው ሥር መቀመጥ አለባቸው፤ ያኔ የሠላም እና የእረፍት ባለበት ይሆናሉ።" —Testimonies for the Church, vol. 7, pp. 69, 70.

"የአምላክ ሕዝቦች በየዋህነትና ርኅራኄ ሲሞሉ፣ በላያቸው ላይ ያለው የእርሱ አርማ ፍቅር እንደሆነ ይገነዘባሉ፣ ፍሬውም ለጣዕማቸው ይጣፍጣል። ለላይኛው ሰማይ ሲዘጋጁ በታች በምድርም የሰማይን ኑሙና ያንጸባርቃሉ።"—Ibid., p. 131.



1. ጴጥሮስ ከገባበት ወጥመድ መራቅ የምችለው እንዴት ነው?

2. ክርስቶስ ለእኔ መኖሪያ ቤት ሥፍራ ከገባልኝ ተስፋ አንጻር በምድር ላይ ያለኝ ግዴታ ምንድን ነው?

3. የየሱስን ተግባሮች እኔም ለመፈጸም የምችለው እንዴት ነው?

4. የሱስ ደቀ መዛሙርቱን የእርሱን ከእነሱ መለየት በሰሙ ጊዜ ያጽናናቸው እንዴት ነው?

5. የሱስ ሊፈጸም የሚገባ "ታላቅ ሥራ" ሲል ምን ማለቱ ነው? እንዴትስ ይፈጸማል?

# የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፥ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው።” የሐዋ. ሥራ 5፡32**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, vol. 8, pp. 19–23; The Acts of the Apostles, pp. 47–56.

*“የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ በየትኛውም ዘመን ወይም ዘር ላይ ብቻ የተገደበ አይደለም፤ ክርስቶስ የመንፈሱ መለኮታዊ ተጽዕኖ እስከ መጨረሻው ድረስ ከተከታዮቹ ጋር እንደሚሆን ተናግሯል።”*—The Acts of the Apostles, p. 49.

## 1. ታዛዥነት - የእምነት ፍሬ — እሁድ፣ ሐምሌ 27

### ሀ. ክርስቲያኖች የሱስን በእምነት ሲቀበሉ በልባቸው ምን ይቀበላሉ? ሮሜ 5፡1-5

### ለ. የክርስቶስ ፍቅር በአማኝ ሕይወት ውስጥ እንዴት ይገለጣል? ዮሐንስ 14:15፣ 21፤ 1ኛ ዮሐንስ 2፡3

*“[ክርስቶስ] ሰዎችን የሚያድናቸው በኃጢአት እንዲኖሩ ሳይሆን ከኃጢአት እንዲነጹ ስለሆነ የሚወዱት ፍቅራቸውን በመታዘዝ ይገልጻሉ።”*

*“እውነተኛ ታዛዥነት የሚፈልቀው ከልብ ነው። የክርስቶስ ሥራ የሚያተኩረው በልብ ላይ ነው። እኛ ፈቃደኛ ከሆንን አሳቡን አሳባችን፣ ዓላማውን ዓላማችን በማድረግ ልባችንና ሕሊናችንን ከእርሱ ፍላጐት ጋርስለሚያዋህደው እርሱን በምንታዘዝ ጊዜ የራሳችንን ስሜት ተግባራዊ እናደርጋለን። ፍላጐታችን የነጠረና የተቀደሰ ስለሚሆን ጌታን ማገልገል ከፍተኛ ደስታ ይሰጠናል። እግዚአብሔርን ለማወቅ እድለኞች ስለሆንን ዘወትር እርሱን በመታዘዝ እንኖራለን። የክርስቶስን ባሕርይ ስናጣጥምና ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ስንመሠርት የኃጢአት ጥላቻ ያድርብናል።”*—The Desire of Ages, p. 668.

## ሀ. የሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለማጽናናት ማንን እንደሚልክ ነው ቃል የገባው? ዮሐንስ 14፡16-18

*"የማዳን ሥራ ከተጠነሰሰበት ጊዜ ጀምሮ በሰዎች ልብ ላይ ይንቀሳቀስ ነበር። ነገር ግን ክርስቶስ በምድርላይ በነበረ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሌላ ረዳት አላስፈለጋቸውም ነበር። ክርስ ቶስ ከተለያቸው በኋላ ግን መንፈስ ስለሚያሻቸው መምጣቱ አስፈላጊ ሆነ።"*—The Desire of Ages, p. 669.

## ለ. ክርስቶስ በደቀ መዛሙርቱ ልብ ውስጥ ‹የሚኖረው› እንዴት ነው? ዮሐንስ 14፡19-23

*"መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ ተወካይ ሲሆን የሰብአዊነት ባሕርይ ስለሌለው ውስንነት የለበትም። ክርስቶስ ግን ሰብአዊነትን ስለተላበሰ በአንድ ጊዜ በየቦታው መገኘት አልቻለም። ስለዚህ የሱስ ወደ አባቱ ሔዶ የእርሱ ተተኪ የሆነውን መንፈስ መላኩ ለደቀ መዛሙርቱ ጠቃሚ ነበር። ይህ በመሆኑም አንድ ግለሰብ በመኖሪያ አካባቢ ወይም ከክርስቶስ ጋር ባለው የግል ግንኙነት ምክንያት የተለየ እድል አይኖረውም» በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ሁሉም ሰው ወደ ክርስቶስ መቅረብ ይችላል። በዚህ መሠረት የሱስ ወደ ሰማይ ከመሔዱ በፊት ከነበረው በተሻለ አኳኋን ለደቀ መዛሙርቱ በጣም የቀረበ ይሆናል።"*

*"«እኔን የሚወድደኝን አባቴ ይወድደዋል! እኔም እወድደዋለሁ፣ ራሴንም እገልጥለታለሁ።» ይህን በተናገረ ጊዜ የሱስ የደቀ መዛሙርቱ የወደፊት ታሪክ ይታየው ነበር። ከእነርሱ መካከል አንዱ በእንጨት ላይ ሲንጠለጠል፣ ሌላው በመስቀል ላይ ሲሰቀል፣ አንዱ በባሕር በተከበበ ቋጥኝ ላይ ሲጋዝና ሌሎቹም ሲሳደዱና ሲሞቱ ታየው። ስለዚህ ማንኛውም ፈተና በሚደርስባቸው ጊዜ አብሮአቸው እንደሚሆን ተስፋ በመስጠት አደፋፈራቸው። የሰጣቸው ተስፋ ሁሉ ተፈጽሞአል። ጌታ ለእርሱ ሲሉ እስር ቤት ስለሚገቡት ወይም በደሴት ላይ ብቻቸውን ስለሚጋዙት ታማኝ አገልጋዮቹ ሁሉን ነገር ያውቃል። በመሆኑም አብሮአቸው በመሆን ያጽናናቸዋል። አንድ አማኝ ለሐቅ ሲል በግፈኛ ዳኞች ፊት በቀረበ ጊዜ ክርስቶስ በጐኑ ይቆማል። በእርሱ ላይ የሚሰነዘረው ዘለፋ ሁሉ በክርስቶስ ላይ ያርፋል። በደቀ መዛሙርቱ ምክንያት ክርስቶስ በድጋሚ ወገዛ ይደርስበታል። አንድ የክርስቶስ ተከታይ እስር ቤት በገባ ጊዜ ክርስቶስ ልቡን በፍቅሩ ያረካዋል። ...*

*"በማንኛውም ጊዜና ቦታ፣ በማንኛውም ሐዘንና ችግር ወቅት፣ ማንኛውም ነገር የጨለማና መጪውም ጊዜ ግራ የሚያጋባ ሲመስለን፣ አቅመቢስነትና ብቸኝነት ሲሰማን በእምነት ለምናቀርበው የጸሎት መልስ አጽናኙ ይላክልናል። አንዳንድ ሁኔታዎች ከምድራዊ ወዳጆቻችን ይለዩን ይሆናል ነገር ግን ምንም ዓይነት ሁኔታ ወይም የቦታ ርቀት ከሰማያዊዩ አጽናኛችን ሊለየን አይችልፃ «ባለንበት ቦታና በምንሔድበት ቦታ ሁሉ እኛን ለመደገፍ፣ ለማበረታታትና ለማጽናናት ሁልጊዜ በአጠገባችን ይገኛል።"*—Ibid., pp. 669, 670.

## ሀ. አጽናኙ የደቀ መዛሙርቱን ትውስታ እና ግንዛቤ እንዴት ይነካባቸዋል? ዮሐንስ 14፡26

“[ደቀ መዛሙርቱ] ክርስቶስ ያቀረበላቸውን የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅም ማስተዋል ስለ አቃታቸው ያስተማራቸው ትምህርት ሁሉ በአብዛኛው መና እንደቀረ ያህል ሆነ። የነገራቸውን ቃላት ትክክለኛ ትርጉም እንዳላስተዋሉ በማወቅ የሱስ በርህሩህነቱ እርሱ የነገራቸውን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እንደሚያስታውሳቸው ቃል ገባላቸው። ነገር ግን ደቀ መዛሙረቱ ሊያስተውሉት አይችሉም በማለት ሳይነግራቸው የቀረ ብዙ ነገር ስለነበረ ይህንንም መንፈስ ቅዱስ እንደሚገልጽላቸው ነገራቸው። ሰማያዊ ነገሮችን ለመውደድ እንዲችሉ መንፈስ፤ ቅዱስ ሕሊናቸውን ማነቃቃት ነበረበት። ስለዚህ የሱስ «የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል አላቸው።—The Desire of Ages, pp. 670, 671.

## ለ. አጽናኙ በክርስቶስ እውነተኛ ተከታዮች ፋንታ ሆኖ ሌላ ምን ያደርጋል? ዮሐንስ 16፡12-14

“ያልተረዳችሁት የእውነት ነጥብ፣ እንዲሁም ያልተስማማችሁበት ካለ፣ መርምሩ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር አወዳድሩ፣ የእውነትን ግንድ ወደ እግዚአብሔር ቃል ውስጥ በጥልቀት አስገቡ። ራሳችሁንና አስተያየታችሁን በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ አስቀምጡ፣ አስቀድማችሁ የያዛችሁትን የግል ሀሳባችሁን አስወግዱ፣ እናም የሰማይ መንፈስ ወደ እውነት ሁሉ እንድመራችሁ ፍቀዱ።”—Selected Messages, bk. 1, pp. 412, 413.

“ቃሉ የተሰጠበት ያ ቅዱስ መንፈስ ካልረዳን በስተቀር መለኮታዊውን መገለጥ በትክክል ልንረዳው ወይም ልናደንቀው አንችልም።”—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 241.

“አብዛኛውን ጊዜ ፈተናዎች መቋቋም የማይቻሉ ይመስላሉ፤ ምክንያቱም ፀሎትንና የመጽሐፍ ቅዱስን ጥናት ቸል በማለቱ ተፈታኙ ሰው የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ወዲያውኑ አስታውሶ በመጽሐፍ ቅዱስ [ጥቅስ] መሳሪያዎች ሰይጣንን መፋለም ስለማይችል ነው። በመለኮታዊ ነገሮች ለመማር ፈቃደኛ በሆኑት በእነርሱ ግን መላእክት በዙሪያቸው ናቸው፤ እጅግ አስፈላጊ በሆነው ሰዓትም፣ አስፈላጊ የሆኑትን፣ ለዚያ ጊዜ ገጣሚ የሆኑትን እውነቶች እንዲያስታውሱ ያደርጋቸዋል። ስለዚህም “ጠላት እንደጽኑ ፈሳሽ ሲመጣ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ ምልክቱን ያነሳበታል” [ኢሳይያስ 59÷19]።

የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ተስፋ ሲሰጥ እንዲህ አላቸው፣ “አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል” [ዮሐ 14÷25]። በአደጋ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲያስታውሰን፣ የክርስቶስ ትምህርቶች አስቀድመው በአዕምሮ ውስጥ መከዘን (መጠራቀም) አለባቸው።—The Great Controversy, pp. 599, 600.

## ሀ. የሱስ ለታማኝ ተከታዮቹ የሰጣቸውና በመከራ ጊዜ እጅግ የሚረዳቸው ተስፋ ምንድን ነው? ዮሐንስ 14፡27-29

"የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ባደረገው ንግግር ስለ ራሱ መከራና ሞት ምንም ዓይነት ነገር በሐዘን አልተናገረም። ለእነሱ ያለው የመጨረሻ ውርስ የሰላም ውርስ ነበር።"—The Desire of Ages, p. 672.

"[ዮሐንስ 14:27 የተጠቀሰው] ይህ ሰላም ከዓለም ጋር በመስማማት የሚገኘው ሰላም አይደለም። ክርስቶስ ሰላምን ፈጽሞ ከክፉ ጋር በመደራደር አልገዛም፤ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የተወው ሰላም ውጫዊ ሳይሆን ውስጣዊ ነው፤ ስለዚህም ይህ ሰላም በየትኛውም መከራና ሥቃይ መካከል እንኳን ሁልጊዜ ከምሥክሮቹ ጋር ይኖራል።"—The Acts of the Apostles, p. 84.

"የእውነት ታሪክ በትክክል እና በስህተት መካከል የተደረገ የትግል ታሪክ ሆኖ ቀይቷል። በዚህ ዓለም ተቃውሞ፣ አደጋ፣ ኪሳራ እና ስቃይ እያለ የወንጌል አዋጅ ተካሂዷል።

"ቀደም ሲል ስለ ክርስቶስ ስደትን የተቀበሉ ሰዎች ብርታታቸው ምንድር ነበር? ከእግዚአብሔር ፣ ከመንፈስ ቅዱስና ከክርስቶስ ጋር ያለው አንድነት ነበር። ስድብና ስደት ብዙዎችን ከምድር ወዳጆች ለያይቷቸዋል፣ ነገር ግን ከክርስቶስ ፍቅር ፈጽሞ አላራቃቸውም። በአደባባይ የተፈረደበት ነፍስ ለእውነት ሲል በድብቅ ነቀፋ ሲሰቃይ ከነበረው በተለየ ሁኔታ በአዳኙ የተወደደ አይደለም። 'እኔ እወደዋለሁ' ሲል ክርስቶስ ተናግሯል፣ 'ራሴንም ለእርሱ እገልጣለሁ።' ዮሐ 14፡21 ለእውነት ሲል፣ አማኙ በምድራዊ ፍርድ ቤቶች ብረት ቤት ሲቆም፣ ክርስቶስ ከጎኑ ይቆማል። በእስር ቤት ግድግዳዎች መካከል ሲታሰር፣ ክርስቶስ ራሱን ይገልጣል እንዲሁም በፍቅሩ ልቡን ያስደስተዋል። —Ibid., p. 85.

## ለ. በተልዕኮው መጨረሻ፣ የሱስ ስለራሱ ምን ማረጋገጥ ቻለ? ዮሐንስ 14፡30

"ሰይጣን በሰው ልብ ውስጥ እግሩን የሚያስገባበትን የተወሰነ ነጥብ ያገኛል፤ የሚንከባከባቸውን አንዳንድ ኃጢአተኛ ምኞቶችን ያገኛል፣ በዚህም ፈተናዎቹን ለማምጣት ኃይል ይሆንለታል። ክርስቶስ ግን ስለ ራሱ እንዲህ ሲል ተናግሯል፡ - "የዚህ ዓለም ገዥ ወደ እኔ ይመጣል፣ በእኔም አንዳች አያገኝም"። የፈተና አውሎ ነፋሶች ተወረወሩበት፣ ነገር ግን ለአምላክ ካለው ታማኝነት እንዲያፈገፍግ ሊያደርጉት አልቻሉም።"—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, p. 927.

## 5. የክርስቶስ ሰላም | ሐሙስ፣ ነሐሴ 01

### ሀ. ከአምላክ ጋር ሰላም መፍጠር የምንችለው በምን መንገድ ብቻ ነው? ዮሐንስ 16:33፤ ኤፌሶን 2:13፣ 14

*“እኛ በራሳችን ኃይል የረከሰውን ተፈጥሮአችንን ፍላጎት ለመቋቋም አንችልም። ሰይጣን በዚህ መስመር ፈተና ያመጣብናል። ከዘር በወረስነው ድክመት በመጠቀም በሐሰት ማታለያ ዘዴው በእግዚአብሔር የማይተማ መኑትን ሁሉ ለማጥመድ ሰይጣን ወደ እያንዳንዱ ግለሰብ እንደሚመጣ የሱስ ያውቅ ነበር። ሰው ሊጓዝበት በሚገባው ምድር ላይ በማለፍ ጌታችን ድል አድራጊ የምንሆንበትን መንገድ አዘጋጅቶልናል። ከሰይጣን ጋርበምናደርገው ተጋድሎ ተጠቂ እንድንሆን የሚያደርገን ነገር እንዲኖርፈቃዱ አይደለም። እባቡ በሚያደርስብን አደጋ ምክንያት እንድንደናገጥና ተስፋ እንድንቆርጥ አያደርገንም። «አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ» ይለናል። ዮሃንስ 16:33።”*—The Desire of Ages, p. 122.

### ለ. ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንዲኖረው የሚፈልግ አማኝ ምን ማድረግ ያስፈልገዋል? መዝሙረ ዳዊት 119:165 የዚህ አይነት አማኝ ልምድ ምን ይሆናል? 1ኛ ዮሐንስ 3፡22

*“ጌታ ለሌሎች እንደሚነግር ሁሉ ለእኛም ተግባራችን ምን እንደሆነ ለመንገር ፈቃደኛ ነው። በእምነት ወደ እርሱ ከቀረብን ምስጢሩን ለእያንዳንዳችን በቀጥታ ይነግረናል። ከሄኖክ ጋርእንዳደረገው ጌታ ከእኛም ጋር ግንኙነት ለመመሥረት በቀረብን ጊዜ መንፈሳችን ይግላል። እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ነገር ላለማድረግ የሚወስኑ ሁሉ ችግራቸውን ለእርሱ ሲያቀርቡለት ምን ማድረግ እንዳለ ባቸው ይነግራቸዋል። ጥበብ ብቻ ሳይሆን ኃይልም ጭምር ይሰጣቸዋል። ክርስቶስ በሰጠው ተስፋ መሠረት ለመታዘዝና ለማገልገል ኃይል ይኖራቸዋል።”*—Ibid., p. 668.

## የግል የግምገማ ጥያቄዎች | አርብ፣ ነሐሴ 02

1. በትክክል በክርስቶስ ስም እየጸለይኩ መሆኔን እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁ?
2. ዓለም ከሚያቀርበው ሰላም ይልቅ የክርስቶስ ሰላም ሊማርከኝ የሚገባው ለምንድን ነው?
3. የክርስቶስን ሰላም እንዴት ላገኝ እችላለሁ?
4. ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ስላለው አማኝ ሕይወት ግለጽ።
5. የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ጠቅለል አድርገህ አብራራ።

ሰንበት፣ ነሐሴ 10፣ 2017

7ኛ ትምህርት

# እውነተኛው የወይን ግንድ የሱስ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና።" (ዮሐንስ 15፡5)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, vol. 4, pp. 353–355; vol. 1, pp. 248, 249

ከክርስቶስ ጋር በሕያው እምነት ያለው ሕብረት ብቻ ዘላቂ ነው፤ ሌላ ሕብረት ሁሉ መጥፋት አለበት። . . . ሌላ ሕብረት ዋጋ ያስከፍለናል። በትዕቢተኛ ተፈጥሮአችን ላይ ፍጹም ጥገኛ እንድንሆን የሚያደርግ ነውና።—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 231.

## 1. ተሰባሪ እና ጥገኛ

**እሁድ፣ ነሐሴ 04**

### ሀ. የሱስ ራሱን ከምን ጋር አነጻጽሮታል? ለምንስ? ዮሐንስ 15፡1 (የመጀመሪያው ክፍል)።

"የሱስ በተዋበው የዘምባባ ዛፍ፣ ግዙፍ በሆነው አርዘ ሊባኖስ ወይም በጠንካራነቱ በታወቀው በባጦስ ዛፍ ፈንታ ለመንጠላጠያ የሚያገለግሉ ሐረጎች ባሉት የወይን ተክል ራሱን መመሰል ፈለገ። ዘምባባ፣ አርዘ ሊባኖስና ባጦስ ለብቻቸው የሚቆሙ ዛፎች ናቸው። ድጋፍ አያሻቸውም። የወይን ተክል ግን በፍርግርግ አጥር ላይእየተንጠላጠለ ወደ ላይ ይወጣል። እንደዚሁም የክርስቶስ ሰብአዊነት በመለኮታዊ ኃይል መተማመን ነበረበት። «እኔ በራሴ ሥልጣን ምንም ማድረግ አልችልም፣» ሲል ተናግሮአል። ዮሐ 5:30"—The Desire of Ages, pp. 674, 675.

### ለ. የሱስ በወይኑ ግንድ ምሳሌ በኩል ለማስረዳት የፈለገው ሌላ ትምህርት ምንድን ነው? ዮሐንስ 15፡1-3

"በአይሁዶች ዘንድ ወይን ተደናቂ፣ ብርቱ፣ ውብና ፍሬአማ ተክል እንደሆነ ይገመት ነበር። እሥራኤላውያን እግዚአብሔር በተስፋው ምድር የተከላቸው የወይን ተክል ናቸው ይባል ነበር። አይሁዶች የመዳናቸውን ተስፋ ከእሥራኤል ጋርበነበራቸው ግንኙነት ላይ መሠረቱት። የሱስ ግን እውነተኛው የወይን ግንድ እኔ ነኝ አለ። ይህን በማለቱ አይሁዶች ከእሥራኤል ጋር በነበራቸው ግንኙነት የእግዚአብሔር ሕይወት ተሳታፊና የተስፋው ወራሽ መሆን እንችላለን ብለው እንዳያስቡ ነገራቸው። መንፈሳዊ ሕይወት የሚገኘው በእኔ አማካይነት ብቻ ነው አላቸው።"—Ibid., p. 675.

## ሀ. ፍሬያማ የሆነ ክርስቲያናዊ ሕይወት ለማግኘት አስፈላጊ የሆነው የትኛው ቅድሜ ሁኔታ ነው? ዮሐንስ 15፡4

"በተክሉ ግንድና ቅርንጫፎች መካከል ያለው ግንኙነት እናንተ ከእኔ ጋር ዘወትር ሊኖራችሁ የሚገባውን ግንኙነት ያመለክታል አላቸው። አንድ ቅርንጫፍ በሌላ ተመሳሳይ ግንድ ላይ ሲከተብ መላ አካሉ ከግንዱ ጋር ተዋህዶ ያድጋል። የግንዱ ሕይወት የቅርንጫፉ ሕይወት ይሆናል። እንደዚሁም በመተላለፍና በኃጢአት የሞተች ነፍስ ከክርስቶስ ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሕይወት ታገኛለች። አንድነቱ የሚፈጠረው ክርስቶስን በእምነት የግል አዳኝ አድርጎ በመቀበል ነው። ኃጢአተኛው ድክመቱን ከክርስቶስ ብርታት ጋር፣ ባዶነቱን ከጌታ ሙሉነት ጋር፣ አቅመቢስነቱንም ከአዳኛችን ዘላለማዊ ኃይል ጋር ማገናኘት አለበት። ይህን ባደረገ ጊዜ አስተሳሰቡ ሁሉ እንደ ክርስቶስ ይሆናል። የክርስቶስ ሰብአዊነት ከእርሱ ሰብአዊነት ጋር ስለሚገናኝ የእኛ ሰብአዊነት ከእርሱ መለኮታዊነት ጋር ይነካካል። በዚህ አኳኋን ሰው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የመለኮታዊ ባሕርይ ተሳታፊ ይሆናል። በአዳኛችንም ዘንድ ተቀባይነት ያገኛል።—The Desire of Ages, p. 675.

## ለ. ከክርስቶስ የተለየ ሰው ምን ይሆናል? ዮሐንስ 15፡6

"ይህ ከክርስቶስ ጋር የሚደረግ ግንኙነት መናጋት የለበትም። ... ይህ የግድየለሽነትን ንክኪነት ወይም እንዳሻው የሚቋረጥን ግንኙነት አያመለክትም። ቅርንጫፍ ሕያው የሆነው ግንድ አካል ነው። ከሥሩ እስከ ቅርንጫፉ ያለው ሕይወታዊ ግንኙነት፣ ጥንካሬና ፍሬአማነት ያለማቋረጥ ይካሔዳል። ቅርንጫፉ ከግንዱ ተለይቶ መኖርአይችልም። እንደዚሁም ከእኔ ተለይታችሁ መኖር አትችሉም ብሎአል የሱስ። ከእኔ የተቀበላችሁት ሕይወት ሊቀጥል የሚችለው ዘወትር ከእኔ ጋርግንኙነት ሲኖራችሁ ብቻ ነው ማለቱ ነው። ያለ እኔ አንድን ኃጢአት ማሸነፍ ወይም አንድን ፈተና መቋቋም አትችሉም አለ።"—Ibid., p. 676.

## ሐ. እውነተኛ ደቀመዝሙርነት እንዴት ይገለጣል? ዮሐንስ 15:4፤ 8:31፤ 13፡35።

"ሰዎች በግድ ወይም በራስ ወዳድነት ሳይሆን በፍቅር የተሳሰሩ እንደሆን ከሰው የላቀ ኃይል እየሠራ መሆኑን ያሳያሉ። ይህ ዓይነት አንድነት ባለበት ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔር ምስል በሰብአዊነት ውስጥ እየታደሰ መሆኑንና አዲስ የሕይወት መርሕ መመሥረቱን ያስረዳል። ይህ ዓይነት የፍቅር መተሳሰር መለኮታዊ ባሕርይ ከሰው አቅም በላይ የሆነ ኃይል ያላቸውን የሰይጣንን ተወካዮቹ ለመቋቋም የሚችል ኃይል እንዳለውና የእግዚአብሔር ጸጋም ሥጋዊ ባሕርይ የሆነውን ራስ ወዳድነትን እንደሚያሸንፍ ያሳያል።"—Ibid., p. 678.

## ሀ. ከክርስቶስ ጋር ያለን የማያቋርጥ ግንኙነት አስተማማኝ ውጤት ምን ይሆናል? ዮሐንስ 15:5፣ 8

*"የተክሉ ሥር ለምግብነት የሚያገለግሉ ንጥረ ነገሮችን በትልልቆቹ ቅርንጫፎች አማካይነት በጫፍ ላይ ለሚገኙት ጥቃቅን ቅርንጫፎች ያስተላልፋል። እንደዚሁም ክርስቶስ መንፈሳዊ ኃይል ለእያንዳንዱ አማኝ እንዲደርሰው ያደርጋል። አንድ ነፍስ ከክርስቶስ ጋር ግንኙነት እስካለው ድረስ የመጠውለግ ወይም የመድረቅ አደጋ አያጋጥመውም።...*

*በእግዚአብሔር ልጅ በማመን ከኖርን አንድም ሳይቀር ሁሉንም የመንፈስ ፍሬዎች እናፈራለን።"*—The Desire of Ages, p. 676.

*"የሚያስፈልገን የሱስ ነው፤ ብርሃኑ፣ ህይወቱ፣ መንፈሱ፣ ያለማቋረጥ የኛ መሆን አለበት። በየሰዓቱ ያስፈልገናል። እና ጠዋት መጸለይ ያለብን ፀሀይ መልክዓ ምድሩን እንደምታበራ እና አለምን በብርሃን እንደምትሞላ፣ የፅድቅ ፀሀይ ወደ አእምሯችን እና ልባችን ክፍል እንድያበራ እና ሁላችንንም በጌታ ብርሃን እንዲያደርገን ነው። ያለ እሱ መገኘት ምንም ነገር ማድረግ አንችልም። ጌታችን ያለእሱ አንዳች ነገር ለማድረግ ብንሞክር ጠላታችን በቅጽበት ከጽናታችን እንድንወድቅ በሚያደርጉ በክፉ ሃሳቦቹ ሊሞላን ዝግጁ መሆኑን ያውቃል። ስለዚህም በእያንዳንዱ ቅጽበት በእርሱ እንድንኖር እና በእርሱም ፍፁም እንድንሆን የጌታ ፍላጎት ነው።"*—My Life Today፣ p. 15.

*"ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርገው የተቀበሉ ሁሉ የወንጌልን እውነት እና በህይወት ላይ ያለውን የማዳን ኃይሉን ማሳየት አለባቸው። እግዚአብሔር ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ሳያደርግ ተጠያቂ አያደርግም። ስለዚህ በክርስቶስ ጸጋ እግዚአብሔር የሚፈልግብንን ሁሉ ማድረግ እንችላለን። የሰማይ ሀብት ሁሉ በእግዚአብሔር ሕዝብ በኩል ይገለጣልና።"*—Christ's Object Lessons, p. 301

## ለ. በክርስቶስ ፍቅር መኖር የምንችለው በምን ሁኔታ ላይ ነው? ዮሐንስ 15:9፣ 10፤ 1ኛ ዮሐንስ 2፡5

*"እግዚአብሔር በእናንተ አማካይነት የቅድስና፣ የርህሩህነትና የመሐሪነት ባሕርዩ እንዲገለጽ ይፈልጋል አላቸው። ቢሆንም አዳኛችን ደቀ መዛሙርቱ ፍሬ ለማፍራት መልፋት እንዳለባቸው አላዘዘም። ነገር ግን በእኔ ኑሩ አላቸው እንጂ።"*—The Desire of Ages, p. 677.

*"እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚፈጽምበት ታላቁ መንገድ ሰዎች ባህሪያቸውን እንዲያዳብሩ እድል መስጠትና በመፈተን ነው። በዚህም ለትዕዛዙ ታዛዥ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ያረጋግጣል። መልካም ስራዎች የእግዚአብሔርን ፍቅር አይገዙም ነገር ግን ፍቅሩ በውስጣችን እንዳለ ያሳያሉ።"*—Christ's Object Lessons, p. 283

## ሀ. የሱስ በራሱ እና በአማኞች መካከል ያለ መገናኛ ድልድይ ስለሆነው ቃሉ ምን አለ? ዮሐንስ 15:3፣ 7፤ 6፡63።

*"ክርስቶስ ከተከታዩቹ ጋር የሚኖረው በቃሉ አማካይነት ነው። ይህ በቃሉ አማካይነት የሚገኝ ግንኙነት ሥጋውን በመብላትና ደሙን በመጠጣት ከሚገኘው ግንኙነት ጋር ተመሳሳይ ነው። የክርስቶስ ቃል መንፈስም፤ ሕይወትም ነው። ይህን ቃል መቀበል ማለት የወይኑን ግንድ ሕይወት መቀበል ማለት ነው። «ሰው የሚኖረው እግዚአብሔር በሚናገረው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይደለም።» ማቴ 4:4። የክርስቶስ ሕይወት በእኛ ውስጥ ካለ እርሱ ያፈራውን አይነት ፍሬ እንድናፈራ ያደርገናል።*—The Desire of Ages, p. 677.

## ለ. ለእግዚአብሔር ቃል በምንገዛበት ጊዜ በመንፈሳዊ ቀዶ ጥገና ውስጣዊ መሻቶቻችንና አመለካከታችንን እንዴት እንደሚለውጥ ግለጽ። ዕብራውያን 4:12፤ መዝሙረ ዳዊት 51:10

*"የአምላክ አገልጋዮች ተፈጥሮአዊ ልብን የሚቀርጥ እና ባህርይን የሚያዳብር ትክክለኛ ምስክርነት መስጠት መቻል አለባቸው።"*— Testimonies for the Church፣ vol.1, p. 249.

*"መጽሐፍ ቅዱስ ... በየቀኑ ለነፍሳችን የሚናገር የእግዚአብሔር ድምፅ ነው። . . . የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የጨለመውን ማስተዋል ማብራት፣ ራስ ወዳድነትን እና ድንጋያማ ልብን ማቅለጥ፣ ዓመፀኛውን ተላላፊዎችን በማንበርከክ እና ከዓለም ክፉ ተጽዕኖዎች ለማዳን ነው። ክርስቶስ ስለ ደቀ መዛሙርቱ የጸለየው ጸሎት: - "በእውነት ቀድሳቸው፤ ቃልህም እውነት ነው" የሚል ነበረ። የእግዚአብሔር ቃል የሆነው የመንፈስ ሰይፍ የኃጢአተኛውን ልብ ይወጋል እና ይቆርጠዋል።"*—Ibid., vol. 4, p. 441.

*"ራሳቸውን ለመንፈስ ቅዱስ በሚያስገዙ ሁሉ ውስጥ አዲስ የሕይወት መመሪያ ሊተከል ይገባል፤ የጠፋው የእግዚአብሔር መልክ በሰው ልጆች ውስጥ ሊታደስ ይገባልና።"*—Christ's Object Lessons, p. 96.

*"እግዚአብሔር እውነትን ለተራቡትና ለተጠሙት ልጆቹ እጅግ የተከበረውን ምስጢሩን ይገልጽላቸዋል። የሱስ የግል አዳኝ መሆኑን ይረዳሉ። ቃሉን እንደተመገቡ መጠን መንፈስና ሕይወት መሆኑን ይገነዘባሉ። ቃሉ ተፈጥሮአዊዩንና ምድራዊዩን ባሕርይ ደምስሶ በየሱስ ክርስቶስ አዲስ ሕይወትን ይሰጣል። ቅዱስ መንፈስም ነፍስን ለማጽናናት ይመጣል። የመለወጥ ኃይል ባለው ጸጋው አማካይነት የእግዚአብሔር ምስል በደቀ መዝሙሩ ላይ ስለሚቀረጽ አማኙ አዲስ ፍጡር ይሆናል። ይህ ሲሆን በጥላቻ ፈንታ ፍቅር ይተካል፣ ልብም የመለኮትን ምሳሌነት ይይዛል» «ሰው የሚኖረው እግዚአብሔር በሚናገረው ቃል ሁሉ፣» ነው ማለት ይህ ነው። ከሰማይ የወረደውን እንጀራ መብላት ማለትም ይህ ነው።"*—The Desire of Ages, p. 391.

## ሀ. በክርስቶስ አለሁ እያለ ፍሬ የማያፈራውን አማኝ ክርስቶስ ምን ያደርገዋል? ዮሐንስ 15፡2 (የመጀመሪያ ክፍል)።

"በግንዱ ላይ የተከተበ ቅርንጫፍ ከውጭ ሲያዩት ከግንዱ ጋር የተዋሃደ መስሎ ነገር ግን ሕይወት እንዲኖረው የሚያደረገው ግንኙነት ላይኖረው ይችላል። ይህ ከሆነ ደግሞ ማደግና ፍሬ መስጠት አይችልም። እንደዚሁም እኛ በእምነት ከክርስቶስ ጋር እውነተኛ ግንኙነት ሳይኖረን ከውጭ ሲያዩን ከእርሱ ጋር ግንኙነት ያለን እንመስል ይሆናል። ሰዎች ሃይማኖትን በመቀበል ወደ ቤተክርስቲያን ይገቡ ይሆናል፣ ነገር ግን ባሕርያቸውና ጠባያቸው ከክርስቶስ ጋር ግንኙነት ያላቸውና የሌላቸው መሆኑን ይመሰክራል። ፍሬ ካላፈሩ የሐሰት ቅርንጫፎች ናቸው። ከክርስቶስ መለየታቸው በደረቀ ቅርንጫፍ ላይ የሚደርስ ዓይነት ጥፋት ያመጣባቸዋል።"—The Desire of Ages, p. 676.

## ለ. የሱስ በእርሱ ለሚኖሩ ቅርንጫፎች ምን ያደርጋል? ዮሐንስ 15፡2 (የመጨረሻው ክፍል)።

"አትክልተኛው ለምን ይህን እንደሚያደርግ የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በጥንቃቄ ገለጸላቸው። ግረዛው ያሳምማል! ገራዡ ግን ሰማያዊዩ አባታችን ነው። ይህ ሰማያዊ አባታችን በግድየለሽነት አይሠራም። አንዳንድ በምድር ላይ የሚሳቡ ቅርንጫፎች ወደ ላይ በማደግ ከእግዚአብሔር ድጋፍ እንዲያገኙ ከምድራዊ ድጋፍ ጋር ያስተሳሰሩዋቸው መተብተቢያ ሐረጎቻቸው መቆረጥ አለባቸው። ለፍሬው የሚያስፈልገውን ምግብ የሚሻማ ትርፍ ቅጠል ሁሉ መቆረጥ አለበት። ከጽድቅ ጸሐይየሚመጣውን ፈውስ ሰጪ ጨረር የሚከልል ማንኛውም ተቀጥላ ወይም ጥገኛ አካል ሁሉ መቆረጥ አለበት። ፍሬው ጥራትና ብዛት ያለው እንዲሆን ለማድረግ አትክልተኛው ማንኛውንም ጉጂ አካል ሁሉ ከተክሉ ያስወግዳል።"—Ibid., p. 677.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች



1. በክርስቶስ እንዴት ልኑር?
2. የእሱን "የመነንደል/የመገረዝ" ጥቅሞች የበለጠ ተቀባይ መሆን የምችለው እንዴት ነው?
3. በሕይወቴ ውስጥ የዚህ "ጉንደላ" ውጤት ምን ይሆናል?
4. ክርስቶስ ይህን ግኑኝነት በምሳሌ ለማስረዳት የወይኑን ግንድ ምሳሌ የተጠቀመው ለምንድን ነው?
5. ፍሬያማ ክርስቲያናዊ ሕይወት ለማግኘት መሠረቱ ምንድን ነው?

## ሰንበት፣ ነሐሴ 17፣ 2017

## 8ኛ ትምህርት

# የወንድማማችነት ፍቅር

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።" (ዮሐ. 13፡34)።**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** Christ's Object Lessons, pp. 376–389

*"በእርሱ መንፈስ የተሞሉ ሁሉ እርሱ እንደወደደ ይወዳሉ። ክርስቶስን ያነሳሳው መርሕ እነርሱንም ያነሳሳቸዋል።"*—The Desire of Ages, p. 678.

## 1. አዲስ ትእዛዝ — እሁድ፣ ነሐሴ 11

### ሀ. በታላቁ ምሳሌያችን ምን ያህል ፍቅር ታይቷል፣ ይህስ ለተከታዮቹ ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው? ዮሐንስ 13:1 (የመጨረሻው ክፍል)፤ 15፡13።

*"ይህ ፍቅር ምንኛ ሰፊ ነው፣ ምንኛ ፍጹም ነው! ደቀ መዛሙርቱ ክርስቶስ እንደ ወደዳቸው እርስ በርሳቸው ሊዋደዱ ይገባ ነበር። ይህም ክርስቶስ በውስጣቸው የክብር ተስፋ እንዳፈነጠቀ ለዓለም ምስክር ይሆን ነበር። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ የዚህን ትእዛዝ አዲሱን ክፍል አልተረዱም ነበር፤ ነገር ግን ከክርስቶስ መከራ በኋላ፣ ከስቅለቱ እና ከትንሣኤው እንዲሁም ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር ካስተዋሉ በኋላ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመረዳት የተወሰነ ሀሳብ አገኙ። መንፈስ ቅዱስ በጰንጠቆስጤ ቀን በላያቸው ላይ ሲያርፈ፣ ያ ፍቅር ተገለጠ።"*—The Signs of the Times, October 20, 1898.

### ለ. የመንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያ ፍሬ ምንድን ነው እና ይህ ፍሬ በእኛ ውስጥ ፍጹም እየሆነ ስለመሆኑ ማስረጃዎች ምንድናቸው? ገላትያ 5:22፤ 1ኛ ዮሃንስ 4:11-13፤ 3፡18።

*ሌሎችን ለመርዳትና ለመባረክ የሚገፋፋው ስሜት ያለማቋረጥ ከውስጥ ሲመነጭ የክርስቲያናዊ ባሕርይ ሙላት ይሆናል።"*— The Acts of the Apostles, p. 551.

## ሀ. ክርስቶስ የወንድማማችነትን ፍቅር “አዲስ ትእዛዝ” ሲል የጠራው ከምን አንጻር ነው? ዮሐንስ 13፡34

“ክርስቶስ እንደወደዳቸው ስላልተዋደዱ ይህ ትእዛዝ ለደቀ መዛሙርቱ አዲስ ነበር። የሱስ ደቀ መዛሙርቱ ለአዲስ አስተሳሰብና ምኞት ተገዢ መሆን፣ በአዲስ የሕይወት መርሕ መመራትና በእርሱ ሕይወትና ሞት አማካይነት ስለ ፍቅርአዲስ ግንዛቤ ማግኘት እንደነበረባቸው ታየው። ከእርሱ የሕይወት መስዋዕት አንጻር ሲታይ እርስ በእርስ የመዋደድ ትእዛዝ አዲስ ትርጉም አለው። መላው የጸጋ ሥራ የማያቋርጥ የፍቅር አገልግሎት፣ ራስን የመካድና ራስን የመሰዋት ጥረት ነው። ክርስቶስ በዚህ ዓለም ላይ በኖረበት በእያንዳንዱ ሰዓት ከእርሱ የእግዚአብሔር ፍቅር እንደ ኃይለኛ ጅረት ይፈስስ ነበር። በእርሱ መንፈስ የተሞሉ ሁሉ እርሱ እንደወደደ ይወዳሉ። ክርስቶስን ያነሳሳው መርሕ እነርሱንም ያነሳሳቸዋል።”—The Desire of Ages, pp. 677, 678.

## ለ. የእግዚአብሔር ልጆች እና የክርስቶስ ወዳጆች መሆናችንን የሚያሳየው ምንድን ነው? ሮሜ 8:14፤ 1ኛ ዮሐንስ 3፡10

“ሃይማኖት የክርስቶስን ቃል በመፈጸም ላይ ነው። ይህንንም የምናደርገው የእግዚአብሔርን ሞገስ ለማግኘት ሳይሆን ፣ ግን ሳይገባን ያንን ሁሉ የፍቅሩን ስጦታ ስለተቀበልን መሆን አለበት። ክርስቶስ የሰውን መዳን አምናለሁ በማለት ብቻ ሳይሆን በጽድቅ ሥራ በሚገለጥ እምነት ላይ አድርጓል። ዝም ብሎ መናገር ብቻ ሳይሆን ፣ ትክክለኛ ተግባር ከክርስቶስ ተከታዮች የሚጠበቅ ነው። ባሕርይ የሚገነባው በተግባር ነውና። በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። ሮሜ 8:14 በመንፈስ ልባቸው የሚነካ ሳይሆን፣ አሁንም ሆነ በጊዜው ለሥልጣኑ የሚገዙ ሳይሆኑ፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጆች የሚሆኑት በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ ናቸው።”—Thoughts From the Mount of Blessing, pp. 149, 150.

“የክርስቶስ ተከታዮች ባህርይ እና ዝንባሌ እንደ ጌታቸው ያለ ይሆናል። የእሱ፣ ቅዱስ እና ፍጹም የሆነው ምሳሌ ለክርስቲያኖች የተሰጠ ምሳሌ ነው። እውነተኛ ተከታዮቹ ወንድሞቻቸውን ይወዳሉ እንዲሁም ከእነሱ ጋር ተስማምተው ይኖራሉ። ክርስቶስ ምሳሌ እንደሰጣቸው ባልንጀሮቻቸውን ይወዳሉ እናም ከቻሉ ነፍሳት ኃጢአታቸውን እንዲተዉ እና ወደ እውነት እንዲመለሱ ለማድረግ ማንኛውንም መስዋዕትነት ይከፍላሉ።—Testimonies for the Church, vol. 3, pp. 58, 59

## ሀ. የሱስ ለታማኝ ተከታዮቹ ምን ዓይነት ማዕረግ ሰጣቸው? ለምንስ? ዮሐንስ 15:15፣ 14

*"ክርስቶስ አለ፡- እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ። የሰዎችን ባሕርይ የሚያረጋግጠው ይህ ፈተና ነው።"*—Testimonies for the Church, vol. 4, p. 188.

*"አሁን ያለንበት ጊዜ ለእግዚአብሔር አገልጋዮች ታላቅ ዕድል እና የተቀደሰ አደራ ነው። እነዚህ አደራዎች በታማኝነት ከተጠበቁ፣ መምህሩ፡- የመጋቢነትህን መዝገብ ስጥ ሲል የታማኝ አገልጋዩ ሽልማት ታላቅ ይሆናል። ልባዊ ድካም፣ ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ ሥራ፣ ታጋሽነት፣ ታታሪነት፣ ብዙ ዋጋ ያስገኛል። "ከእንግዲህ እኔ ባሮች አልላችሁም፣ ነገር ግን ወዳጆቼ፣ እንግዶቼ እላቸዋለሁ። የመምህሩ እውቅና የሚሰጠው በተከናወነው ሥራ ታላቅነት ወይም ብዛት አይደለም፣ ግን በጥቂት ነገሮች ውስጥ ባሳያችሁት ታማኝነት መሠረት ነው። እኛ ባገኘነው ታላቅ ውጤት ሳይሆን ለመሥራት በተነሳሳንበት ምክንያት ነው በእግዚአብሔር ዘንድ ተግባራችን የሚመዘነው። ከተሰራው ስራ ታላቅነት ይልቅ ያሳየናቸው መልካምነትን እና ታማኝነትን ነው አምላክ የሚሸልመው።"*—Ibid., vol. 2, pp. 510, 511.

## ለ. የሱስ እኛን የመረጠን ለምን ዓላማ ነው? ከዚህ ልዩ መብት ጋር የተያያዙት ኃላፊነቶችስ ምን ምን ናቸው? ዮሐንስ 15:16፣ 17

*"አዳኛችን ማንም ሰው ፍቅር ፈጽሞ ሊስተካከለው የማይችል ፍቅር ለእኛ ገልጦልናል። ቀሳስለን በሞት አፋፍ ላይ በነበረንበት ጊዜ አዘነልን፤ ራራልን እንጂ መንገዱን ቀይሮ ያለረዳትና ያለተስፋ እንድንጠፋ ገለል ብሎ አላለፈንም፡፡ በሰማይ ሠራዊት ዘንድ እጅግ የሚወደድበት ቅዱስና የደስታ ቤቱ ተቀምጦ አልቀረም። ቁስላችንን አከመልን፣ ጉዳያችን የራሱ አድርጎ ወሰደ፤ ማንነቱን ከሰበአዊ ዘር ጋር አቀራኘ። ጠላቶቹን ለማዳን ሞተ። ለገዳዮቹ ጸለየ። ራሱን ምሳሌ በማድረግ ለተከታዮቹ እንዲህ አለ "እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ይህቺ ትዕዛዜ ናት"፤ "እንግዲህ እኔ እንደወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ።" ዮሐንስ 15:17፤ 13:34።"*— Christ's Object Lessons, pp. 381, 382.

*"የክርስቶስ ተከታዮች ነን ልንል እንችላለን፣ በአምላክ ቃል ውስጥ ያለውን እውነት ሁሉ እናምናለን እንል ይሆናል፤ ነገር ግን እምነታችን በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ እስካልተገበርን ድረስ ይህ ለባልንጀራችን ምንም አይጠቅምም።"*—Ibid., p. 383.

## ሀ. ዓለም ለክርስቶስ ወዳጆች ምን ያሳያል? ለምን? ዮሐንስ 15:18፣ 19

“ሰዎች በግድ ወይም በራስ ወዳድነት ሳይሆን በፍቅር የተሳሰሩ እንደሆን ከሰው የላቀ ኃይል እየሠራ መሆኑን ያሳያሉ። ይህ ዓይነት አንድነት ባለበት ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔር ምስል በሰብአዊነት ውስጥ እየታደሰ መሆኑንና አዲስ የሕይወት መርሕ መመሥረቱን ያስረዳል። ይህ ዓይነት የፍቅር መተሳሰር መለኮታዊ ባሕርይ ከሰው አቅም በላይ የሆነ ኃይል ያላቸውን የሰይጣንን ተወካዮቹ ለመቋቋም የሚችል ኃይል እንዳለውና የእግዚአብሔር ጸጋም ሥጋዊ ባሕርይ የሆነውን ራስ ወዳድነትን እንደሚያሸንፍ ያሳያል።”

ይህ ፍቅር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተከሰተ ሰይጣንን እንደሚ ያስቆጣው አያጠራጥርም። ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ ችግር የሌለበት ጉዳና አልቀየሰላቸውም።”—The Desire of Ages, p. 678.

## ለ. ዓለም ክርስቶስን ያሳደደው ለምንድነው፣ ተከታዮቹስ ለምን ይሰደዳሉ? ዮሐንስ 3:19፣ 20፤ 15:20፣ 21

“በጽድቅና በኃጢአት፣ በፍቅርና በጥላቻ፣ በእውነትና በውሸት መካከል ታላቅና ከባድ ግጭት አለ። አንድ ሰው የክርስቶስን ፍቅርና የቅድስና ውበት ሲያቀርብ፣ የሰይጣንን መንግሥት ተገዢዎችን ወደ ራሱ እየሳበ ነው፣ ስለዚህ የክፋት አለቃው ሊቃወመው ይነሳሳል። በክርስቶስ መንፈስ የተሞሉትን ሁሉ ስደትና ነቀፋ ይጠብቃቸዋል። የስደቱ ባህርይ ከዘመኑ ጋር ይለዋወጣል፣ ነገር ግን መርሆ - የሚያነሳሳው መንፈስ - ከአቤል ዘመን ጀምሮ የጌታን መንገድ የመረጡትን የሚገድለው ያው አንድ ነው።”—Thoughts From the Mount of Blessing, p. 29.

“የእግዚአብሔር እውነት በዓለም ዘንድ ተወዳጅ ሆና አታውቅም። ሰበአዊ ልብ እውነትን ይጠላል። የቀራኒዮ ሰው ተከታዮች እንድንሆን የዓለምን ፍቅር፣ የልብ ትምክህትን እና ወደ ጣዖት አምልኮ የሚወስደን ነገር ሁሉ እርግፍ አድርገን መተው ስላለብን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። እውነትን የሚታዘዙ ሰዎች በዓለም ዘንድ ፈጽሞ አይወደዱም አይከበሩምም። በሰው ልጆች መካከል በትሕትና ሲመላለስ ከመለኮታዊው መምህር አንደበት፡ “ማንም ደቀ መዝሙሬ ሊሆን የሚወድ መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ” የሚሉ ቃላቶች ተሰምተው ነበር። አዎ፣ ምሳሌያችንን ተከተሉ። እሱ የሰውን ውዳሴና ክብር ይፈልግ ነበርን? በፍፁም! ታዲያ ከዓለማዊ ሰዎች ክብርን ወይስ ምስጋናን እንሻለንን?።

“እግዚአብሔርን የማይወዱ የእግዚአብሔርን ልጆች አይወዱም። የሰማያዊውን ምክር ቃል አድምጡ፦ ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ።” — Testimonies for the Church, vol. 2, p. 491.

## 5. መለኮታዊ ፍቅር በአማኞች ሕይወት | ሐሙስ፣ ነሐሴ 15

### ሀ. ሐዋርያው ጳውሎስ ከእውነተኛ ክርስቲያናዊ ፍቅር እና በማስመሰል መካከል ያለውን ልዩነት የሚገልጸው እንዴት ነው? 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡1-8

*"እምነቱ የቱንም ያህል ከፍ ያለ ቢሆንም፣ ልቡ በእግዚአብሔርና በሰዎች ፍቅር ያልተሞላ ከሆነ እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ሊሆን አይችልም። ምንም እንኳን ታላቅ እምነት ቢኖረውና ተአምራትን ለማድረግ እንኳ ኃይል ቢኖረውም፣ ያለ ፍቅር ግን እምነቱ ከንቱ ይሆናል። እርሱ ታላቅ ነቸርነትን ሊያሳይ ይችላል፤ ነገር ግን ከእውነተኛ ፍቅር ውጭ ሌላ ነገርን በማሰብ ንብረቱን ሁሉ ለድሆች ቢሰጥ ድርጊቱ ወደ እግዚአብሔር ፊት አያቀርበውም። በቅንዓቱ በሰማዕትነት ሞት ሊሞት ይችላል፤ ሆኖም በእውነተኛ ፍቅር ካልተገፋፋ አምላክ እንደ አታላይ ቀናተኛ ወይም ታላቅ ግብዝ አድርጎ ይመለከተዋል።"*—The Acts of the Apostles, pp. 318, 319.

### ለ. በራዕይ 3፡10 -12 ላይ በክርስቶስ ስለተመሰገኑት ባህርያት እና እንደዚያ ያሉ ባሕርይ ባለቤቶች ስለሰጣቸው ተስፋዎች ምን ልንገነዘብ ይገባናል?

*"ንጹሕና የተቀደሰ ልብስ ማንም ሰው ወደ ከተማይቱ በር ከገባ በኋላ እንድለብሰው አልተዘጋጀም። የሚገቡም ሁሉ አስቀድመው የክርስቶስን የጽድቅ ልብስ ይለብሳሉ የእግዚአብሔርም ስም በግምባራቸው ይታያል። ይህ ስም ሐዋርያው በራዕይ ያየው ምልክት ነው፣ እና አእምሮን በጥበብ እና በታማኝነት ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ መታዘዛቸውን የሚያሳይም ነው። የባይርያቸውን ጉድለት እና ኃጢአተኝነታቸውን መሸፋፈን የሚባል ነገር ፈጽሞ የለም፤ የትኛውም ልብስ ግማሽ ንጹህ ግማሽ የቆሸሸ አይሆንም፤ ነገር ግን ሁሉም ንጹሕና ነውር የለሽ ይሆናሉ እንጂ።"*—The Youth's Instructor, August 18, 1886

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች | አርብ፣ ነሐሴ 16

1. ክርስቶስ በእኔ ውስጥ ምን ዓይነት መለኮታዊ ፍቅር እንዳዳብር ይፈልጋል?
2. የክርስቶስን ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ ፍቅር በሙላት እንዳላገኝ የሚከለክለኝ ምንድን ነው?
3. የክርስቶስ ትእዛዝ ለእኔ አዲስ የሚሆነው እንዴት ነው?
4. ስደት ቢነሳ ሊገርመኝ የማይገባው ለምንድን ነው?
5. በፊላደልፊያ ጊዜ ለነበሩ ምእመናን የተሰጡ በረከቶችን ግለጽ።

# የመንፈስ ቅዱስ ተልእኮ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤” (ዮሐ. 16፥8)።**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, vol. 8, pp. 14–23.

*“መንፈስ ቅዱስ ግን በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት መልእክት ወደ ሕሊናችን እንዲደረስ በማድረግ እውነተን በልባችን ያትመዋል። በዚህ አኳኋን ስህተትን እያጋለጠ ከሕሊና እንዲወጣ ያደርገዋል። ክርስቶስ የመረጣቸውን ወገኖቹን ለእርሱ እንዲገዙ የሚያደርጋቸው በእግዚአብሔርቃል አማካይነት በሚሠራው በእውነት መንፈስ ነው።”*—The Desire of Ages, p. 671.

## 1. “ያለ አጽናኝ አልተዉህም” — እሁድ፣ ነሐሴ 18

### ሀ. ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ምን ችግሮች አጋጠሟቸው? ዮሐንስ 16፡1-3

*“ጌታ ለእርሱ ሲሉ እስር ቤት ስለሚገቡት ወይም በደሴት ላይ ብቻቸውን ስለሚጋዙት ታማኝ አገልጋዮቹ ሁሉን ነገር ያውቃል። በመሆኑም አብሮአቸው በመሆን ያጽናናቸዋል። አንድ አማኝ ለሐቅ ሲል በግፈኛ ዳኞች ፊት በቀረበ ጊዜ ክርስቶስ በጐኑ ይቆማል። በእርሱ ላይ የሚሰነዘረው ዘለፋ ሁሉ በክርስቶስ ላይ ያርፋል። በደቀ መዛሙርቱ ምክንያት ክርስቶስ በድጋሚ ወገዛ ይደርስበታል። አንድ የክርስቶስ ተከታይ እስር ቤት በገባ ጊዜ ክርስቶስ ልቡን በፍቅሩ ያረካዋል።”*—The Desire of Ages, p. 669.

### ለ. ለደቀ መዛሙርቱ ምን ማረጋገጫ ተሰጣቸው—እንዴትስ? ዮሐንስ 14:18፤ 15፡26።

*“[ክርስቶስ] የመለኮት ሦስተኛ አካል የሆነውን ወኪሉን ሊሰጥ ወሰነ። ሁሉንም ስጦታዎች በአንዴ ስለፈለገ መለኮታዊውን መንፈስ፣ የሚለውጥ፣ ብርሃን የሚሰጥ እና የሚቀደሰውን ኃይል በስጦታ ሰጠን።”*—My Life Today, p. 36.

## ሀ. ከእርገቱ በኋላ በክርስቶስ እና በተከታዮቹ መካከል ባለው ግንኙነት ምን ልዩነት ይፈጠራል? ዮሐንስ 16፡7

"ከዚህ በኋላ በመንፈስ፣ ክርስቶስ በልጆቹ ልብ ውስጥ ያለማቋረጥ እንዲኖር ነበረ። እርሱ ከእነርሱ ጋር ከነበረበት ጊዜ ይልቅ አሁን ከእርሱ ጋር ያላቸው አንድነት ይበልጥ የቀረበ ነበር። በውስጣቸው ያለው የክርስቶስ ብርሃን፣ ፍቅር እና ኃይል በእነርሱ በኩል በራ።"—Steps to Christ, p. 75.

## ለ. መንፈስ ቅዱስ ለኃጢአተኞች ምን ያህል ሰፊ ሥራ ይሠራል? ዮሐንስ 16፡8-11

"መንፈስ ቅዱስ በአዳኛችን ሞት የተገኘውን መዳን ውጤታማ እንዲሆን ሕይወት የሚዘራ ወኪል ነው። መንፈስ ዘወትር በቀራንዮ መስቀል ላይ ወደ ተዘጋጀው ታላቅ መስዋዕት የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለአለም ለማሳየት እና ለተፈረደባት ነፍስ የቅዱሳት መጻህፍትን ውድ ነገሮች ለመክፈት ዘወትር ይፈልጋል።

መንፈስ ቅዱስ የኃጢአተኛነታችን እንድናምን ካደረገ እና የጽድቅን መለኪያ በአእምሮ ፊት ካቀረበ በኋላ፣ ፍቅራችንን ከዚህ ምድር ነገር እንድናነሳ አድርጎ ነፍስን በቅድስና ምኞት ይሞላል። "ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል" (ዮሐንስ 16፡13) ሲል አዳኙ ተናግሯል። ዳግም ለመሠራት ዝግጁ ስንሆን መላው ተፈጥሯችን ወደ ቅድስና ይመጣል። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ነገሮች ወስዶ በነፍሳችን ላይ ያትማል። በእርሱም ኃይል የሕይወት መንገዶች ማንም እንዳይሳሳት ዘንድ ፍጹም ግልጽ ይሆናሉ።"—The Acts of the Apostles, pp. 52, 53.

## ሐ. መንፈስ ቅዱስ በዓለም ፊት ምን ሌላ አስፈላጊ ተልእኮ ይፈጽማል? ዮሐንስ 15፡26

"ለዓለም ማስጠንቀቂያ የሚያደርሰው የመንፈስ ቅዱስና የሕያው ምስክር ምስክርነት ሕብረት ነው። የእግዚአብሔር አገልጋይ ሰማይ ለዓለም መልዕክቱን የሚያስተላልፍበት ወኪል ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የእውነትን ቃል መለኮታዊ ሥልጣን ይሰጠዋል።"—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 6, p. 1053.

## ሀ. ከመንፈስ ቅዱስ ሌላ ስለ ክርስቶስ የሚመሰክረው ማን ነው? ዮሐንስ 15:27፤ 1ኛ ዮሐንስ 1፡1-3 እንዴት?

*"ነጋዴው በታማኝነት ሲነግድ ጌታውን በሚያስከብር መንገድ እየሰራ ነው ማለት ነው። እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ ካሆነ በሚያደርገው ነገር ሁሉ ኃይማኖቱን ያሳያል ፣ የክርስቶስንም መንፈስ ለሰዎች ይገልጻል። የእጅ ሙያ ያለው ደግሞ በታታሪጉልና በታኘነቱ በገሊላ ተሪ ስራ ሲሰራ የነበረውን የኢየሱስን ባህሪይ ያንጸባርቃል። እያንዳንዱ የክርስቶስን ስም የሚጠሪ ሁሉ ሌሎች መልካም ስሪውን በማየት የእርሱን ፈጣሪና አዳኝ ያክብሩ ዘንድ ስራውን በታማኝነት መስራት አለበት።*

*"በሰው ዘንድ አነስተኛ ግምት የሚሰጠው አገልግሎትም ቢሆን «ለጌታ እንደምናደርገው (ቆላ 3: 23) በማሰብ በደስታ መንፈስ እናገልግል። የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ውስጥ ካለ በሕይወታችን ይገለጣል። የክርስቶስ መልካም ማዕዛ ዙሪያችንን ይክበናል። በሌሎች ላይ የምናሳድረው ተጽእኖም ወደ ሰማይ ከፍ የሚያደርጋቸውና የሚባርካቸው ይሆናል።"* — Steps to Christ, pp. 82, 83.

## ለ. በብሉይ ኪዳን ዘመን ለእግዚአብሔር ሕዝብ በነቢዩ ኢዩኤል በኩል ለወደፊት ምን ልዩ ተስፋ ተሰጥቷል? ኢዮኤል 2:28፣ 29

## ሐ. ይህ የተስፋ ቃል በከፊል የተፈጸመው መቼ እና እንዴት ነው? የሐዋርያት ሥራ 2:1-7፣ 16–18

*"የክርስቶስ እርገት ተከታዮቹ የተስፋውን በረከት እንደሚቀበሉ የሚያሳይ ምልክት ነበር። ለዚህም ወደ ሥራቸው ከመግባታቸው በፊት መጠበቅ ነበረባቸው። ክርስቶስ በሰማያዊ ደጆች ውስጥ ሲያልፍ በመላእክቱ ስግደት መካከል በማለፍ በዙፋኑ ተቀመጠ። ይህ ሥርዓት እንደ ተፈጸመ መንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ በኃይል ፈሰሰ፣ ክርስቶስም ከአብ ጋር ከዘላለም እስከ ዘላለም በነበረው ክብር ከበረ። የጴንጤቆስጤው ቀን የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የአዳኛችን ስመት ወይም መቀባት በሰማይ መፈጸሙን የሚያሳይ መልዕክት ነበር። እንደ ተስፋ ቃሉ፣ ካህንና ንጉሥ ሆኖ በሰማይና በምድር ሥልጣንን ሁሉ እንደተቀበለና በሕዝቡ ላይ የተቀባ መሆኑን ለማመልከት መንፈስ ቅዱስን ከሰማይ ወደ ተከታዮቹ ልኳል።"*—The Acts of the Apostles, pp. 38, 39.

## ሀ. በኢዩኤል 2፡28-32 ያለው የተስፋ ቃል እኛንም እንደሚመለከት እንዴት እናውቃለን? የሐዋርያት ሥራ 3፡19

*"ይህ የተስፋ ቃል ለእነርሱ የተሰጠውን ያህል ለእኛም የተሰጠ ነው፣ ነገር ግን ይህ ርዕስ በሕዝብ ፊት የሚቀርበው አልፎ አልፎ ነው፣ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ አቀባበሉ የሚነገረው በጣም በጥቂቱ ነው። በዚህ በጣም አስፈላጊ ጭብጥ ዙሪያ ባለው ዝምታ ምክንያት፣ ከዚህ ለሥራችን በሙሉ ኃይል ከሚሆነው የመንፈስ ቅዱስ በሙላት ከመፍሰስ ተስፋ ቃል ሌላ ተግባራዊ ፍጻሜውን በጥቂቱ የምናውቀው ስለ ምን ተስፋ ቃል ነው? የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ በንግግራችን ውስጥ የሚገባው በቸልታ ወይም በአጋጣሚ ነው። ትንቢቶች ተፈጽመዋል፣ አስተምህሮዎችም ተብራርተዋል፣ ነገር ግን በመንፈሳዊ ጥንካሬ እና ቅልጥፍና እንድታድግ፣ ሰብከቶች ኃይልን እንዲኖራቸው እና ነፍሳት ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ፣ ለቤተክርስቲያን አስፈላጊ የሆነው ይህ አስፈላጊው ነገር በአብዛኛው በአገልግሎታችን ጥረት ጥረት ሳይደረግበት ተትቷል።"*—Testimonies to Ministers, p. 174.

*"የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሊሠሩት የሚችሉትን ሥራ ለመሥራት ቢነቃቁ፣ በራሳቸው ተነሳሽነት ወደ ውጊያው ቢገቡ፣ እያንዳንዱም ነፍሳትን ወደ የሱስ በማሸነፍ ረገድ ምን ያህል ማከናወን እንደሚችሉ ቢያዩ፣ ብዙዎች ከሰይጣን ሰልፍ ወጥተው በክርስቶስ ባንዲራ ሥር ሲቆሙ እናይ ነበር። ህዝባችን በእነዚህ ጥቂት የማስተማሪያ ቃላቶች የተሰጠውን ብርሃን ተግባራዊ ካደረገ፣ በእርግጥ የእግዚአብሔርን ማዳን እናያለን። አስደናቂ መነቃቃቶች ይከተላሉ። ኃጢአተኞች ይለወጣሉ፣ እና ብዙ ነፍሳት ወደ ቤተ ክርስቲያን ይጨመራሉ። ልባችንን ከክርስቶስ ጋር ወደ አንድነት ስናመጣ እና ሕይወታችንን ከሥራው ጋር ስናስማማ በበዓለ ሃምሳ ቀን በደቀ መዛሙርት ላይ የወረደው መንፈስ ዛሬ በእኛም ላይ ይወርዳል።"*—Testimonies for the Church, vol. 8, p. 246.

## ለ. በዛሬው ጊዜ በዋነኝነት የሚያሳስበን ነገር ሊሆን የሚገባው ምንድን ነው? ወደ ጌታ ከልብ መጸለይ ያለብንስ ስለ ምንድን ነው? ዮሐንስ 16:12–14፤ ዘካርያስ 10፡1

*"እ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምን ያህል ለሁላችንም ያስፈልገናል? ያን ጊዜ በክርስቶስ ባለ ሃሳብ፣ በደግነት፣ በርኅራኄ እና በኃዘኔታ፣ ኃጢአትን በፍጹም ጥላቻ እየጠላን ለኃጢአተኛው ፍቅር በማሳየት ሁልጊዜ እንሠራለን።"*—Evangelism, p. 369.

*"ሥራው በኃይል እንዲፈጸም በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል መነቃቃት ያስፈልጋል፤ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ያስፈልገናል። አምላክ ዓለምን በማስጠንቀቅ ረገድ የበኩላቸውን ሚና የሚጫወቱትን ችሎታና ተጽዕኖ ያላቸውን ሰዎች በሕዝቡ መካከል እንደሚጨምር ማስተዋል አለብን።"*—Ibid., pp. 558, 559.

## 5. ዝግጅት

**ሐሙስ፣ ነሐሴ 22**

### ሀ. በኋለኛው የዝናብ ኃይል ለመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ መዘጋጀት ያለብን እንዴት ነው? ሆሴዕ 6:1-3

*"ብዙዎች በጌታ ቀን ገጣሚ ሆነው ለመገኘትና በዓይኖቹ ሥር ለመኖር 'መታደስን' እና 'የኋለኛውን ዝናብ' ብቻ በመሻት በእጅጉ አስፈላጊ የሆነውን ዝግጅት የማድረጉን ነገር ቸል ብለውት እንደነበር ተመልክቻለሁ።" በመከራው ወቅት ያለ ከለላ የቀሩትን ስንቶችን አየሁ! እነዚህ ሰዎች ዝግጅት የማድረግን አስፈጊነት ችላ በማለታቸው በተቀደሰው አምላክ ፊት ገጣሚ አድጎ የሚያቆማቸውን መታደስ መቀበል አልቻሉም ነበር። በነቢያት ለመታነጽ የተቃወሙና መላውን እውነት በመታዘዝ ነፍሳቸውን ለማጥራት ያልቻሉ፣ እንዲሁም እነርሱ ከሚገኙበት ተጨባጭ ሁኔታ በእጅጉ የተሻለ እንደሆኑ አድርገው ለማመን ፈቃደኞች የሆኑ ሁሉ መቅሰፍቶቹ በሚወርዱ ጊዜ የግንቡ አካል ይሁኑ ዘንድ መታነጽና መጠረብ ያስፈልጋቸው እንደነበር ይመለከታሉ። ነገር ግን ይህን ለማድረግ ጊዜ የለም፤ ልመናቸውን ተቀብሎ ከአብ ዘንድ የሚማልድም አይኖርም። ከዚህ ጊዜ በፊት 'ዓመፀኛው ወደ ፊት ያምፅ፣ ርኩሱም ወደ ፊት ይርከስ፣ ጻድቁም ወደ ፊት ጽድቅ ያድርግ፣ ቅዱሱም ወደ ፊት ይቀደስ' የሚል አስፈሪ አዋጅ ይወጣል። በማንኛውም ጭንቀት፣ በትዕቢት፣ በራስ ወዳድነት፣ በዓለም ፍቅር፣ እና በእያንዳንዱ የተሳሳተ ቃል እና ድርጊት ላይ ድል እስካላገኙ ድረስ ማንም 'የሚያድሰ'ውን መንፈስ ሊቀበል እንደማይችል አየሁ። ስለዚህ ወደ ጌታ ይበልጥ መቅረብ አለብን እንዲሁም በጌታ ቀን በሰልፉ ለመቆም የሚያስችለንን አስፈላጊውን ዝግጅት በትጋት እንሻ። እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ እና ማንም ከቅዱሳን በቀር በፊቱ ሊኖሩ እንደማይችሉ ሁሉም ያስታውሱ።*—Early Writings, p. 71.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

**አርብ፣ ነሐሴ 23**

1. *መንፈስ ቅዱስ በእኔ ውስጥ እየሰራ ያለው ሥራ ምንድን ነው—እንዲሁም በእግዚአብሔር እጅ እንዳለ መሳሪያ አድርጎ ሊጠቀምብኝ የሚፈልገው እንዴት ነው?*
2. *መንፈስ ቅዱስን በሙላት እንዳላገኝ ምን እንቅፋት ሊሆንብኝ ይችላል?*
3. *ቤተ ክርስቲያኔ የመንፈስን ሙላት እንድታገኝ ለመርዳት የእኔ ድርሻ ምንድን ነው?*
4. *በምድር ላይ የመንፈስ ቅዱስን ተግባራት ግለጽ።*
5. *የኢዩኤል 2፡28–32ን ትንቢት ግለጽ።*

# የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ
# ሰንበት፣ ጳጉሜ 01፣ 2017




## በማሃኮ፣ ሩዋንዳ የሚገኝ ትምህርት ቤት



የሩዋንዳ ሪፐብሊክ በምስራቅ አፍሪካ የምትገኝ ሀገር ስትሆን ከታንዛኒያ፣ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ ኡጋንዳ እና ብሩንዲ ጋር ትዋሰናለች። የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከ2000ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ በቡና እና ሻይ ኤክስፖርት እንዲሁም በእርሻ ምርት፣ በሳሙና፣ በሃይል፣ በታሸገ ውሃ እና በሌሎችም ከፍተኛ እድገት አሳይቷል። የሺህ ኮረብቶች ምድር በመባል የምትታውቀው ሩዋንዳ በቅርብ አመታት በውበቷ በተለይም በወንዞቿ እና በሐይቆቿ፣ የትምህርት ቤት ፕሮጄክታችን ባለበት በማሆኮ ከተማ አቅራቢያ ቱሪስቶችን የበለጠ እየሳበች ነው።

ከ13 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያሏት ሩዋንዳ፣ አገር በቀል የሆነው ኪኛርዋንዳ፣ ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዝኛ (20% ሕዝብ የሚናገረው ይፋዊ ቋንቋ) እና ስዋሂሊ ቋንቋዎች ይነግርባታል። ከሕዝቡ መካከል 43.7% ካቶሊኮች፣ 37.7% ዋና ፕሮቴስታንቶች፣ 11.8% የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች (ከሌሎች ፕሮቴስታንቶች የተለየ ምድብ ተብሎ ይጠቀሳሉ) እና 2.0% ሙስሊም፣ ሌሎችም ይከተላዋቸዋል።

ምንም እንኳን ሁሉም ቤተ እምነቶች እዚህ ቢኖሩም፣ እጅግ በወደቀው ዓለም፣ ልጆቻችንን በጥልቀት ለማስተማር ኢንቨስት ማድረግ እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ እንመለከታለን። “እውነተኛ ትምህርት የወንጌላዊያን ሥልጠና ነው። እያንዳንዱ የአምላክ ወንድና ሴት ልጅ ወንጌላዊያን እንዲሆኑ ተጠርተናል፤ የተጠራነው አምላክንና ወንድሞቻችንን ለማገልገል ነው፤ ለዚህ አገልግሎት ብቁ ማድረግ የትምህርታችን ዓላማ ሊሆን ይገባል።”—The Ministry of Healing, p. 395.

ልጆቻችን በየቀኑ በዚህ ዓለም ነገር እየተሳቡ እነሱን ከጠላት ሽንገላ መከላከል አዳጋች እየሆነ መጥቷል። በአንድ ወቅት በተደራሽነት ውስን የነበረው አሁን በማይታመን ፍጥነት በ”ስማርት” ስልኮች እና ሌሎች መሳሪያዎች በኩል ዓለማዊነት ከልጆቻችን ጋር ተያይዟል። የገዛ ልጆቻችን ለወንጌል ሥራ ማዘጋጀት ሲሳነን እንዴት ለወንጌል ሥራ ብቁ ሆነን ሊንገኝ እንችላለን? በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ልጆቻችን በሰንበት ቀን ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ስለሚገደዱ አሁን የበለጠ ስጋት ወድቀናል። ስለዚህ፣ የዚህ ፕሮጄክት አስፈላጊነቱ እጅግ አስቸኳይ ነው።

እኛ ያለን የገንዘብ አቅማችን በቂ ስላልሆነ፣ በአለም ዙሪያ ያሉ ወንድሞቻችን የዚህን ትምህርት ቤት ህንጻ ለመሥራት እንዲረዱን በአክብሮት እንጠይቃለን።

የመጀመሪያው የሰንበት ሥጦታ በሚሰበሰብበት ጊዜ፣ በዚህ በሺህ ኮረብቶች መካከል በዚህ የትምህርት ቤት ፕሮጀክት እግዚአብሔር ይከብር ዘንድ፣ እባካችሁ በልግስና ስጡ። ጌታ ስጦታዎችን እና ሰጭዎችን አብዝቶ እንዲባርክ ጸሎታችን ነው!

ወንድሞቻችሁ እና እህቶቻችሁ ከሩዋንዳ

# ክርስቶስ ስለ ደቀ መዛሙርቱ ጸለየ (1)

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "እኔ ስለ እነዚህ እለምናለሁ፤ ስለ ዓለም አልለምንም ስለ ሰጠኸኝ እንጂ፤ የአንተ ናቸውና፤ የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው የአንተውም የእኔ ነው፤ እኔም ስለ እነርሱ ከብሬአለሁ።" (ዮሐንስ 17:9፣ 10)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, vol. 5, pp. 737–746.

"ይህ ጸሎት (በዮሐንስ 17 ላይ) አዳኙ ስለሰዎች ያቀረበው ታላቅ መስዋዕትነት፣ እራሱን ያቀረበበት መስዋዕትነት ሊጠናቀቅ በተገባበት ጊዜ፣ በመጋረጃው ውስጥ ስለሚያደርገው ምልጃ ትምህርት ነበር።—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 5, p. 1145.

| 1. ክርስቶስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ያደረገው የመጨረሻ ጸሎት | እሁድ፣ ነሐሴ 25 |
|---|---|

## ሀ. የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ መመሪያ ከሰጠ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ምን አደረገላቸው? ዮሐንስ 17:1፣ 9

"[ዮሐንስ 17:1–6 የተጠቀሰ] ይህ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሆኖ ያቀረበው የመጨረሻ ጸሎት ነበር፣ ሊካድ እና ተላልፎ ሊሰጥበት ወዳለው ወደ ጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ከመግባቱ በፊት ነበር።"—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 5, p. 1145.

## ለ. ክርስቶስ በዚህ ጸሎት መክፈቻ ላይ ምን ገለጠ? ዮሐንስ 17:1፣ 2

"የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አሥራ ሰባተኛው ስለ አምላክና ስለ ክርስቶስ ማንነት እንዲሁም እርስ በርስ ስለሚኖራቸው ግንኙነት በግልጽ ይናገራል።"—Ibid.

"የዮሐንስ ወንጌልን አሥራ ሰባተኛውን ምዕራፍ በጸሎት አጥኑ። ይህ ምዕራፍ ተደጋግሞ መነበብ ብቻ ሳይሆን እውነቶቹም መበላትና ከሕይወታችን ጋር መዋሃድ አለባቸው።"—Testimonies for the Church, vol. 8, p. 80.

## ሀ. የሱስ የዘላለም ሕይወት መሠረት የሆነውን የትኛውን መሠረታዊ እውነት ተናግሯል? ዮሐንስ 17፡3

"በክርስቶስ የተገለጠው የእግዚአብሔር እውቀት የሚድኑት ሁሉ ሊኖራቸው የሚገባው እውቀት ነው። ይህ እውቀት የባህሪ ለውጥን የሚያመጣ ነው። ወደ ሕይወታችን ስንቀበል ነፍስን በክርስቶስ መልክ እንደገና ይፈጥራል። ይህን እውቀት እንዲቀበሉ እግዚአብሔር ልጆቹን ይጋብዛል፣ ከዚህም ሌላ ሁሉም ከንቱና ዋጋ ቢስ ነው።"—The Acts of the Apostles, p. 475.

"የሱስም፦ "አብ ራሱ ይወዳችኋል" አለ። እምነታችን በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ላይ የተመሰረተ ከሆነ፣ 'እንደ ነፍስ መልሕቅ፣ አስተማማኝና ጽኑ፣ ቀዳሚውም ወደ መጋረጃውም ውስጥ እንደሚገባ" ያረጋግጣል። እውነት ነው ተስፋ መቁረጥ ይመጣል፤ መከራም የሚጠበቅ ነገር መሆን አለበት፤ ነገር ግን ሁሉንም ነገር ከትልቅ እስከ ትንሹ ለእግዚአብሔር አደራ መስጠት አለብን። እርሱ በጥያቄአችን ብዛት ግራ አይጋባም ወይም በሸክማችን ክብደት አይሸነፍም። ተንከባካቢው የእሱ እጅ እያንዳንዱን ቤተሰብ እና እያንዳንዱን ግለሰብ ይከብባል፤ እሱ በእያንዳንዱ ጉዳዮቻችን እና ሀዘኖቻችን ጊዜ ሁሉ ያስብልናል። እንባዎችን ሁሉ ምልክት ይመዘግባል፤ በድካማችን ስሜቱ ይነካል። እዚህ የሚያጋጥሙን መከራዎች እና ፈተናዎች ሁሉ የተፈቀዱት፣ ለእኛ ያለውን የፍቅር አላማዎች እንዲፈጸሙ፣ 'የእርሱ ቅድስና ተካፋዮች እንድንሆን' እና በዚህም በእርሱ ፊት ባለው የደስታ ሙላት ተካፋዮች እንድንሆን ነው።"

"የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን የአምላክን እውቀት የማግኘትን አስፈላጊነት በፊታችን ይገልጥልናል።"—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 742.

## ለ. ክርስቶስን ማወቅ ሲባል ምን ማለት ነው? የዚህ ዓይነቱ እውቀት ውጤትስ ምንድን ነው? ሆሴዕ 6፡3ን ከዮሐንስ 17፡3 ጋር አወዳድር።

"እግዚአብሔርን ማወቅ የምንችለው ክርስቶስን በማወቅ ብቻ ነው። … የክርስቶስን ማዳን ማወቅ ማለት በመንፈሳዊ እውቀት መነቃቃትና ቃሉን መተግበር ነው። ያለዚያ ፣ ሁሉም ነገር ከንቱ ነውና።

"ክርስቶስ አብን ሊገልጥ ወደዚህ ዓለም መጣ። እንዴት ያለ ትዕግስት፣ እንዴት ያለ ርኅራኄ፣ እንዴት ያለ መለኮታዊ ርኅራኄ፣ ምን ዓይነት የዓላማ ጥንካሬን የሚገልጥ ነው! አልወደቀም ወይም ተስፋ አልቆረጠም። የንጽህና መገለጫ ነበር፣ ፍቅሩም ምንም መሳይ አልነበረውም። በእያንዳንዱ እርምጃ ራስን መካድ እና ራስን መስዋዕትነትን ተለማምዷል። በሞቱም በአምላክና በሰው መካከል እርቅ መፈጠሩን መግለጫ ሆነ።—The Signs of the Times, January 27, 1898.

"እግዚአብሔርን ማወቅ እሱን መውደድ ነው።"—The Desire of Ages, p. 22.

## ሀ. በአገልግሎቱ ወቅት፣ ክርስቶስ በምድር ላይ ያሳለፈው ሕይወት ምንን የያዘ ነበር? ዮሐንስ 17፡4

"የሱስ ባደረጋቸው የጸጋ ተግባራት ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን የወላጅነት እና ቸር ባሕርያት በሰዎች አዕምሮ ላይ ለማስገንዘብ ፈልጎ ነበር። በትምህርቱ ሁሉ 'በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ እግዚአብሔር ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና' የሚለውን አስደናቂ እውነት ለሰዎች ለማስተማር ይፈልግ ነበር። የሱስ የአብን ፍቅር እንድንገነዘብ ይፈልጋል፣ እናም የወላጅነት ፀጋውን በማቅረብ ወደ እርሱ ሊስበን ይፈልጋል።

"የሱስ ወደ ዓለም የመጣው የእግዚአብሔርን ባሕርይ በራሱ ሕይወት ለማስረዳት ነው፤ ሰይጣንም የፈጠረውን የተሳሳተ መግለጫ ወደ ኋላ ገፍፎ የእግዚአብሔርን ክብር ገለጠ። የሰማዩ አባቱን ምሕረት፣ ርኅራኄና ፍቅር ሊገልጥ የቻለው በሰዎች መካከል በመኖር ብቻ ነው፤ የእግዚአብሔርን ጸጋ መግለጽ የቻለው በበጎነት ብቻ ነበርና።"—Sons and Daughters of God, p. 139.

## ለ. የሱስ በምድራዊ ተልእኮው መጨረሻ ላይ አብን ምን ጠየቀው? ዮሐንስ 17፡5

"ክርስቶስ ለሰበአዊ ክብር አልጸለየም፤ ምክንያቱም ሰበአዊነቱ በቀድመው ህልውናው ፈጽሞ አልነበረምና። በእግዚአብሔር አንድነት ስላለው ክብር ወደ አባቱ ጸለየ እንጂ። ጸሎቱ በአማላጅነቱ ነው፤ የሚለምነው ጸጋ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ በነበረ ጊዜ ለእርሱ የነበረውን የመለኮታዊ ክብር መገለጫ ነው፡ ፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ከአንተ ዘንድ የነበረኝ ክብር መጋረጃው ተገልጦ ወደፊት ይዉጣ ብሎ ነውና የሚጸልየው።"—The Signs of the Times, May 10, 1899.

"ይህ ዓለም እግዚአብሔር በሚመራበት ሰፊ ግዛት ውስጥ ያለ አቶም ብቻ ነው, ነገር ግን ይህች ትንሽ የወደቀች ዓለም - የጠፋችው በግ - ከመንጋው ካልጠፉ ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ በፊቱ የከበረች ናት፣ ክርስቶስ በሰማያዊ አደባባዮች ውስጥ የተወደደው አዛዥ፣ ከከፍተኛ ግዛቱ ዝቅ ብሎ ይህችን አንዷን የጠፋችውን ዓለም ከኃጢአት ለማዳን ሲል ከአብ ጋር የነበረውን ክብር ጥሏል። እርሱን የወደዱትን በኀጢአትም ያልወደቁትን ዘጠና ዘጠኙን ዓለማትን ትቶ ወደዚች ምድር መጥቶ 'ስለ መተላለፋችን ቈሰለዋል' 'ስለ በደላችንም ደቀቀ። (ኢሳይያስ 53:5ን አንብብ።) የጠፉትን በጎች መልሶ የመቀበል ደስታ እንዲያገኝ አምላክ ራሱን በልጁ በኩል አሳልፎ ሰጠ።"—Christ's Object Lessons, pp. 190, 191.

## ሀ. ደቀ መዛሙርቱ ከክርስቶስ ጋር በመተባበራቸው ቃሉን በተመለከተ ምን እምነት ነበራቸው? ዮሐንስ 7:17፤ 17፡7። ዛሬ የእኛ ግዴታ ምንድን ነው?

"እውነትን ለማወቅ እና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመረዳት የሚፈልጉ፣ ለብርሃን ታማኝ የሆኑ እና የእለት ተእለት ተግባራቸውን በመፈፀም ቀናተኞች የሆኑት፣ ትምህርቱን በእርግጥ ያውቃሉ፣ ወደ እውነት ሁሉ ይመራሉና። እግዚአብሔር ሰዎች እውነትን በማይፈልጉበት ጊዜ እና እውነትን የማወቅ ፍላጎት በማይኖራቸው ጊዜ፣ ድንቅ በሆነው ተግባር፣ ሰዎችን በግድ ወደ እውነት እውቀት ለማምጣት ቃል አልገባም። ሰዎች የእግዚአብሔርን መንፈስ የማራቅ ሥልጣን አላቸው፤ የመምረጥ ሥልጣን በእጃቸው ላይ ነውና። የተግባር ነፃነት አላቸው። በአዳኛችን ስም እና ጸጋ ታዛዥ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ወይም አንታዘዝም ማለት ይችላሉ፣ ነገር ግን ውጤቱን ያጭዳሉ። ሰው የተቀደሰ እና ዘላለማዊ እውነትን የመቀበል ወይም የመቃወም ሙሉ ስልጣን አለው። የእግዚአብሔር መንፈስ ያለማቋረጥ ይወቅሳል፣ እንዲሁም ነፍሳት እውነትን ለመቀበል ወይም ለመቃወም እየወሰኑ ነው።—Testimonies for the Church, vol. 3, pp. 427, 428

## ለ. የሱስ የሐዋርያትን እምነት በተመለከተ ለአባቱ ምን ብሏል? ዮሐንስ 17፡8 እነዚህ ቃላት ዛሬ በእኛ ላይ የሚሠሩት እንዴት ነው?

"[ዮሐንስ 17:3፣ 8 የተጠቀሰው] በዓለማችን እርሱ የአብ ወኪል እንደነበረው የክርስቶስ ተወካዮች እንድንሆን በፊታችን የተቀመጠው ሥራ ይኸውና። በክርስቶስ ትምህርት የተሰጡንን ቃላት ልናስተምር ይገባናል። ... በምሳሌያዊው የስርየት ቀን ሲወከል በነበረው አሁን በዋናው የሥርየት ቀን ላይ ነን፣ እናም ልባችንን በማዋረድ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢያታችንንም መናዘዝ ብቻ ሳይሆን የተሰጠን መክሊታችን ሁሉ በመጠቀም አምላክንና የላከውን የሱስ ክርስቶስን እንዲያውቁ የምናገኛቸውን ሰዎች ሁሉ ወደ አምላክ ለማምጣት በትእዛዛትና በምሳሌ ማስተማር አለብን።"—Christian Education, p. 157.

## ሐ. በተለይ የሱስ በዮሐንስ 17 ላይ ጸሎቱን ያቀረበው በማን በኩል ነው? ዮሐንስ 17:9፣ 20

"[ክርስቶስ] እጅግ በጣም የተቸገሩት፣ እጅግ ለተጨቆኑትና በመከራ ለተፈተኑት ይማልዳል።"—Our High Calling, p. 49.

## 5. ክርስቶስ በደቀ መዛሙርቱ ከበረ | ሐሙስ፣ ነሐሴ 29

### ሀ. የሱስ በደቀ መዛሙርቱ የከበረው እንዴት ነው? ዮሐንስ 17:10፣ 11 ይህ ሥራ እንዲሠራ ምን ያስፈልጋል?

"ክርስቶስ በሰማይ የሰፈነው ሥርዓት፣ የአስተዳደር እቅድና ሕብረት በምድር ላይ ባለችው ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንዲሰፍን ዓላማው ነው። በዚህ አኳኋን በሕዝቡ ስለሚከበር በእነርሱ አማካይነት የጽድቅ ጸሐይ ሳይደበዝዝ ብሩህ ሆኖ ለዓለም ብርሃኑን ያዳርሳል። ... የክርስቶስ ጽድቅ የተሰጣት ቤተ ክርስቲያን የጌታ ምሕረት፣ ጸጋና ፍቅር በግልጽ ለትእይንት የሚቀርቡባት የአደራ እቃ ማስቀመጫ ቦታ ናት። የክብር ሁሉ መነሻ የሆነው ታላቁ ማዕከል ክርስቶስ የውርደቱ ዋጋና የክብሩ ማሚያ የሆኑትን ወገኖቹን ንጹህና ፍፁም እንደሆኑ አድርጐ ይገምታቸዋል።"—The Desire of Ages, p. 680.

"ደቀ መዛሙርቱ የመንፈስ ቅዱስን ኃይልና የሰማይ መላዕክትን ትብብር እንደሚያገኙ ተሰፋ የሚኖራቸዉ ከክርስቶስ ጋር ሲተባበሩ ብቻ ነበር። በእነዚህ መለኮታዊ ወኪሎች እርዳታ በዓለም ፊት አንድ ግንባር ሲፈጥሩ ከጨለማ ኃይሎች ጋር በሚያደርጉት በማያቋርጥ ጦርነት አሸናፊ ይሆናሉ። በአንድነት መሥራታቸውን ሲቀጥሉ፣ የሰማይ መልእክተኞች መንገዱን እየከፈቱ ከፊታቸው ይሄዳሉ። እውነትን ለመቀበል ልቦች ይዘጋጃሉ፣ እና ብዙዎች ወደ ክርስቶስ ይመጣሉ። አንድ ሆነው እስከቀዩ ድረስ ቤተ ክርስቲያን 'እንደ ጨረቃ የተዋበች፣ እንደ ፀሐይም የጠራች፣ ዓላማ ይዞ እንደ ተሰለፈ ሠራዊት የምታስፈራ' ሆና ትወጣለች። ወደፊት ግስጋሴዋን የሚቋቋማት ምንም ነገር አይኖርም። ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ለዓለም የማወጅ መለኮታዊ ተልእኮዋን በክብር በመወጣት ከድል ወደ ድል ትሸጋገራለች።"—The Acts of the Apostles, pp. 90, 91.

## የግል የግምገማ ጥያቄዎች | አርብ፣ ነሐሴ 30

1. ስለ ክርስቶስ ያለኝ የግል እውቀት እጣ ፈንታዬን ሊነካው የሚችለው እንዴት ነው?
2. ክርስቲያናዊ ልምዴ በአምላክ እጅ የሚገኝ የማስተማሪያ መሣሪያ ሊሆን የሚችለው በየትኞቹ መንገዶች ነው?
3. ክርስቶስን በሙላት ለማስከበር ምን ማድረግ እችላለሁ?
4. የሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለመጨረሻ ጊዜ የጸለየው በምን ሁኔታዎች ውስጥ ነው?
5. የክርስቶስን የመጀመሪያ መምጣት ምክንያቶች ግለጽ።

# ሰንበት፣ መስከረም 03፣ 2018

**11ኛ ትምህርት**

## ክርስቶስ ስለ ደቀ መዛሙርቱ ጸለየ (2)

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "እኔንም የወደድህባት ፍቅር በእነርሱ እንድትሆን እኔም በእነርሱ፥ ስምህን አስታወቅኋቸው አስታውቃቸውማለሁ። (ዮሐ. 17:26)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** The Sanctified Life, pp. 61–69.

"*የተቀደሰ ሊቀ ካህን በመሆኑም ለሕዝቡ ያማልዳል። ታማኝ እረኛ ስለሆነም መንጋው በኃያሉ አምላክ ጥላ ሥር ጠንካራና አስተማማኝ በሆነ መጠለያ ውስጥ እንዲሰበሰቡ ያደርጋል። እርሱ ግን ከሰይጣን ጋር የሚያ ደርገው የመጨረሻ ተጋድሎ ይጠብቀው ስለነበር ጠላቱን ለመጋፈጥ ወጣ።*"—The Desire of Ages, p. 680.

## 1. አንድነት በክርስቶስ — እሁድ፣ ጳጉሜ 02

### ሀ. የሱስ በአማላጅነት ጸሎቱ ውስጥ ለቤተክርስቲያን ስኬት አስፈላጊ የሆነውን የትኛውን ነጥብ ደጋግሞ ተናግሯል? ዮሐንስ 17፡11 (የመጨረሻው ክፍል)፣ 21–23

"*[ክርስቶስ]እርሱና አብ አንድ እንደሆኑ ደቀ መዛሙርቱ አንድ እንዲሆኑ ይጸልያል፤ እናም ይህ የአማኞች አንድነት እርሱ እንደላከን እና የጸጋውን እንደተሸከምን ለዓለም ምስክር እንዲሆን ነው።*"—My Life Today, p. 252.

"*በግላችን ወደ እግዚአብሔር ከቀረብን ውጤቱ ምን እንደሚሆን አይታይህምን? በዚህም እርስ በእርሳችን እንደምንቀራረብ አታውቅምን? ነገር ግን ልባችን ፍጹም በሆነ አንድነት ካልተዋሃደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እና ወደ አንዱ መስቀል ሥር መምጣት አንችልም።*"— Our High Calling, p. 96.

### ለ. የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዴት ሊመጣና እንዴት ሊጠበቅ ይችላል? 1ኛ ዮሐንስ 1፡7

"*ከክርስቶስ ጋር የሚኖረው የአማኞች አንድነት፣ በተፈጠሮው ወደ እርስ በርስ አንድነት ይመራናል፣ ይህም የአንድነት ትስስር በምድር ላይ የሚገኝ እጅግ ዘላቂው አንድነት ነው። ክርስቶስ ከአብ ጋር አንድ እንደሆነ እኛ በክርስቶስ አንድ እንሆናለን። ክርስቲያኖች በሕያው ወይን ግንድ ላይ የሚገኙ ቅርንጫፎችና ብቸኛ ቅርንጫፎች ናቸው።*"—Our High Calling, p. 96.

## ሀ. ክርስቶስ ስለ ደቀ መዛሙርቱ እና ስለ ዓለም ምን አለ? ዮሐንስ 17:13፣ 14 ዓለም የሚያሳድዳቸው ለምንድን ነው?

"የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በርግጥም የተለዩ ሕዝቦች ነበሩ። ነቀፋ የሌለው ባህርያቸውና የማይዋዥቀው እምነታቸው የኃጢአተኛውን ሰላም የሚረብሽ ቀጣይ ተግሳጽ ነበር። በቁጥር ጥቂት ቢሆኑም፣ ድሃዎች፣ ደረጃ-የለሽና የክብር ማዕረግ የሌላቸው የነበሩ ቢሆኑም ባህርያቸውና አስተምህሮዎቻቸው በታወቀበት ሥፍራ ሁሉ ለክፉ አድራጊዎች ድንጋጤ ነበሩ። ስለዚህ አቤል የእግዚአብሔር መሰልነት በሌለው ቃየን ይጠላ እንደነበር እነርሱም በኃጢአተኞች ተጠሉ። ቃየን አቤልን ለገደለበት ተመሳሳይ ምክንያት፣ የመንፈስ ቅዱስን ገደብ አሽቀንጥረው መጣል የሚፈልጉ ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ገደሉ። የዚህ ባህርይ ንጽህናና ቅድስና ለራስ ወዳድነታቸውና ለብልሹነታቸው የማያቋርጥ ነቀፋ ስለሆነባቸው፣ አይሁዳውያን የሱስን ያልተቀበሉትና የሰቀሉት በዚሁ ተመሳሳይ ምክንያት ነበር። ከክርስቶስ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ፣ ታማኝ ደቀ መዛሙርቱ የኃጢአትን መንገድ የሚወዱትንና የሚከተሉትን ጥላቻና ተቃውሞ ቀስቅሰዋል።—The Great Controversy, p. 46.

## ለ. የአለም ተጽእኖን በተመለከተ እግዚአብሔር ለልጆቹ ያለው እቅድ ምንድን ነው? ዮሐንስ 17:15፣ 16

"አዳኛችን ተከታዮቹ በዓለም ውስጥ ሊሆኑ እንደሚችሉ ነገር ግን ከዓለም እንደማይሆኑ በራሱ ምሳሌ አሳይቷል። እርሱ የመጣው ከሚያስደስት ተድላ ለመካፈል፣ በልማዶች ለመታለል እና ልምምዳቸውን ለመከተል ሳይሆን የአባቱን ፈቃድ ለማድረግ፣ የጠፉትን ለመፈለግ እና ለማዳን ነው። ይህ ነገር በፊቱ አጥብቀ ከያዘ ክርስቲያን በየትኛውም አካባቢ ሳይበከል በታማኝነት ሊቆም ይችላል። ቦታው ወይም ሁኔታው ምንም ይሁን ምን ከፍ ከፍ ወይም ዝቅ ቢልም በታማኝነት ግዳጁን በመፈጸም የእውነተኛውን ሃይማኖት ሃይል ሊያሳይ ይችላል።"—The Acts of the Apostles, p. 467.

"ዓለም በቂ እውነተኛ ክርስቲያኖች የሏትም፤ ቤተ ክርስቲያን ትፈልጋቸዋለች፤ ኅብረተሰቡም አይተዋቸውም። ስለዚህ ክርስቶስ ስለ ደቀ መዛሙርቱ ያቀረበው ጸሎት፡- "ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልጸልይም" የሚል ነበር። የሱስ በዓለም ውስጥ እንዳለን ያውቃል፣ ለፈተናዎቹ እንደተጋለጥን ያውቃል፣ ነገር ግን እሱ ይወደናል እና በሚያበላሹ ተጽዕኖዎች እንዳንሸነፍ ጸጋን ይሰጠናል። በባሕርያችን ፍጹም እንድንሆን ይፈልጋል፤ ይህም የእኛ የባሕርይ መበላሸት በሌሎች ላይ የሥነ ምግባር ጉድለት እንዳያመጣ ነው።"—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 334.

## ሀ. እውነትን የሚያውቁትንና የሚታዘዙትን እውነት ምን ያደርጋቸዋል? ዮሐንስ 8:32፤ 17፡17።

*"የእውነት እርሾ ወደ ልብ ሲገባ ምኞቶችን ይቆጣጠራል፣ ሃሳቦችን ያጸዳል፣ ስሜትንም ያጣፍጣል። . . .*

*"የእግዚአብሔር ቃል ከእያንዳንዱ የሰው ቤተሰብ አባል ጋር ባለን ግንኙነት ላይ የመቀደስ ውጤት ይኖረዋል። የእውነት እርሾ የፉክክር መንፈስን፣ በምኞት ፈረስ የመጋለብና አኔ ልቅደም ማለትን መንፈስ አያመጣም። እውነተኛና ከሰማይ የሆነ ፍቅር፣ ራስ ወዳድና ተለዋዋጭ አይደለም። በሰዎች ሙገሳና ምሥጋና ላይ የተመሠረተም አይደለም። የእግዚአብሔርን ጸጋ የተቀበለ ሰው ልብ ለእግዚአብሔርና ክርስቶስ ለሞተላቸው ሁሉ ፍቅርን ያፈሳል። ሌሎችን የሚወደው እነሱ ስለሚወዱትና ስለሚያወድሱት፣ ችሎታውን ስለሚያደንቁለት ሳይሆን በክርስቶስ የተገዙ ውዶች ስለሆኑ ብቻ ነው። ቃላቱ፣ አላማውና ድርጊቱ ባይስተዋል ወይም በመጥፎ ቢተረጎም ምንም አይከፋውም፤ የያዘውን መንገድ ብቻ ይዞ ይጓዛል! እንዲህ ዓይነቱ ሰው መልካም፣ ደግ አሳቢ፣ ስለራሱ በትህትና የሚናገር፣ በተስፋ የተሞላና ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፍቅርና ምህረት የሚታመን ነው።*—Christ's Object Lessons, pp. 100, 101

## ለ. እውነት እንዴት ይገለጻል? መዝሙረ ዳዊት 119:142

*"በየሱስ ላይ ያለው እውነት ለጄሆቫ ትእዛዝ ሁሉ መታዘዝ ነው። ይህም የልብ ሥራ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መቀደስ ቅዱሳን ጽሑፎችን የማይመረምር፣ እውነትን እንደተሰወረ ሀብት ከመፈለግ ይልቅ በጥሩ ስሜትና በስሜታዊነት የሚታመን አስመሳይ ቅድስና አይደለም። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅድስና ባለቤቱን የእግዚአብሔርን የሕግ መጠይቆችን እንድያዉቅና እንድታዘዝ ይመራዋል፡ ፡*—Lift Him Up, p. 152.

## ሐ. በእውነት እንዴት እንቀደሳለን? ዮሐንስ 17:19፤ 16፡13 (የመጀመሪያ ክፍል)።

*"ክርስቶስ ራሱን እንደ ቀደሰ እኛም ደግሞ እንድንቀደስ ተናግሯል። እርሱ ተፈጥሮአችንን ለብሶ ለሰው ልጆች እንከን አልባ ምሳሌ ሆነ። እኛ ደግሞ አሸናፊዎች እንድንሆን ወደ መንግሥቱም እንድንገባ ዘንድ እሱ ምንም ስህተት አልሠራም። እኛ በእውነት እንቀደስ ዘንድ ስለ እኛ ጸለየ። ታዲያ እውነት ምንድር ነው? ይህንንም ሲመልስ፡ "ቃልህ እውነት ነው" አለ። ደቀ መዛሙርቱ የሚቀደሱት ለእውነት በመታዘዝ ነው።"*—My Life Today, p. 252.

## ሀ. ክርስቶስ እኛን በአማላጅነት ጸሎቱ ውስጥ እንዳካተተ እንዴት እናውቃለን? ዮሐንስ 17፡20

"ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የሆነላቸውን ሁሉ፣ ዛሬ ላሉት ለልጆቹ መሆን ይፈልጋል።"—Steps to Christ, p. 75.

"ለክርስቶስ የተዋጁት ዕንቁዎቹ፣ ውድና ልዩ ሀብቱ ናቸው።"—Testimonies for the Church, vol. 6, p. 309.

## ለ. ዛሬ በመንፈስ ቅዱስ በኩል የክርስቶስ ጥበቃ በእኛ ላይ መሆኑን ምን ማረጋገጫ አለን? ዮሐንስ 14፡16

"ለደቀ መዛሙርቱ የተነገሩት ቃላቶች ለእኛም ናቸው። አፅናኙ የነሱ የሆነውን ያህል የእኛም ነው። በአለም ጥላቻ እና የእራሳቸው ውድቀቶች እና ስህተቶች በሚገነዘቡበት ጊዜ መንፈስ በእያንዳንዱ ድንገተኛ ሁኔታ ለነፍሳት ለውጊያው ብርታትን ይሰጣል። በሀዘን እና በመከራ ውስጥ፣ የሚታየው ሁሉ ጨለማ እና መጪው ጊዜ ግራ የሚያጋባ በሚመስልበት ጊዜ፣ ረዳት አልባነት እና ብቸኝነት ሲሰማን—እነዚህ ጊዜያት ለእምነት ጸሎት መንፈስ ቅዱስ ለልብ መጽናኛን የሚሰጥባቸው ጊዜያት ናቸው።"—The Acts of the Apostles, p. 51.

"በጣም በሚያስፈልግበት ሰዓት፣ ተስፋ መቁረጥ ነፍስን በሚያደክምበት ጊዜ፣ የየሱስ የማያንቀላፋው ዓይን የእሱ እርዳታ እንደሚያስፈልገን ያያል። የሰው ልጆች እርዳታ የሚያስፈልግባቸው ጊዜ የእግዚአብሔር እርዳታ የሚደርስበት ሰዓት ነው። ሁሉም የሰው ልጆች ድጋፍ ሲጠፋ፣ ያን ጊዜ የሱስ እኛን ለመርዳት ይመጣል፣ እንዲሁም የእሱ መገኘት ጨለማውን ይበትንና የጨለማውን ደመና ያነሳል።"—Testimonies for the Church, vol. 4, p. 530.

## ሐ. የሱስ በጸሎቱ መጨረሻ ላይ ለሕዝቡ ሲል ምን ፍላጎት አሳይቷል? ዮሐንስ 17፡24

"ምድር ከመመሠረቷ በፊት አብና ወልድ ሰው በሰይጣን ድል ከተነሣ ለመቤዠት በቃል ኪዳን ተባበሩ። ክርስቶስ ለሰው ዘር ዋስ እንዲሆን እጃቸውን ተያይዘው ነበር። ይህንንም ቃልኪዳን ክርስቶስ ፈጸመው።—The Desire of Ages, p. 834.

## 5. ስሙን እናውቅ ዘንድ | ሐሙስ፣ መስከረም 01

### ሀ. በክርስቶስ በኩል አብን እንዴት እናንጸባርቃለን? ዮሐንስ 17:25፣ 26

"ክርስቶስ የአብ ተወካይ ሆኖ ራሱን ወደ አለም መምጣቱን ገልጿል። በባሕርዩ ልዕልና፣ በምሕረቱና በርኅራኄው፣ በፍቅሩና በቸርነቱ፣ የመለኮታዊ ፍጹምነት ምሳሌ፣ የማይታየው አምላክ አምሳል ሆኖ በፊታችን ቀሞአል።"— Testimonies for the Church, vol. 5, p. 739.

### ለ. በሕይወታችን ውስጥ ዘውትር ስለ ምን ትኩረት ልንሰጠው ይገባል? ኤርምያስ 9:23፣ 24

"በራሳችን ላይ ያለን ስለመልካምነታችን የምንናገረው ትምክህት ሁሉ ቦታ የለውም።

"የሚመካ ሁሉ በእግዚአብሔር እንጂ በራሱ ይመካ አይልም ትእዛዙ። … እንግዲህ ሰዎች ለራሳቸው ክብርን የሚያገኙበት ምንም ምክንያት የለም፤ ምክንያቱም ላገኙት መልካም ነገር ሁሉ ለክርስቶስ ጸጋ ባለ ዕዳ ናቸውና። ማንም ጥበብና ጽድቅ እንዳለው ራሱን ከፍ ከፍ አያድርግ። . . ."

"በእግዚአብሔር ነገር ጥልቅ ልምድ ያላቸው ከትምክህት ወይም ራስን ከፍ ከፍ ከማድረግ እጅግ በጣም የራቁ ናቸው። ስለራሳቸው በጣም ትሁት የሆነ አስተሳሰብ አላቸው፣ እንዲሁም ስለ ክርስቶስ ክብር እና ልዕልና እጅግ የላቀ ፅንሰ-ሀሳብ አላቸው። … ዓይኖቻችንን ወደ ሰማይ አድርገን የክርስቶስን ባህሪይ በግልፅ ስንመለከት ጌታን በልባችን ከፍ ከፍ እናደርጋለን።

"አንድ ሰው ስለ አዳኙ ታሪክ ሲያውቅ፣ ያሉበትን ከባድ ጉድለቶችን ይገነዘባል፤ ከክርስቶስ ጋር ያለው ልዩነት በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ በሕይወቱ ውስጥ ሥር ነቀል ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ይገነዘባል። በዚያም እንደ ታላቁ አርአያ ለመሆን ባለው ፍላጎት ይማራል።"—Sons and Daughters of God, p. 235.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች | አርብ፣ መስከረም 02

1. በወንድሞች መካከል አንድነት እንዲኖር ምን ማድረግ እችላለሁ?
2. ክርስቶስ ስለ ደቀ መዛሙርቱ ካቀረበው ጸሎት ምን ጥቅም ማግኘት እችላለሁ?
3. ስለ እግዚአብሔር ስም ጥልቅ እውቀት ማዳበር የምችለው በየትኞቹ መንገዶች ነው?
4. ክርስቶስ "እነሱ ከዓለም አይደሉም" ያለውን አባባል ግለጽ።
5. የ "እውነት"ን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቺዎች ጠቅለል አድርገህ አብራራ።

# የክርስቶስ ለፍርድ መቅረብ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "የሱስም ጴጥሮስን። ሰይፍህን ወደ ሰገባው ክተተው፤ አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣትምን? አለው። (ዮሐንስ 18:11)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** Early Writings, pp. 165–168.

*"የዓለምን እጣ ፈንታ የሚወስን አስፈሪው ጊዜ መጥቶ ነበር።"*—The Desire of Ages, p. 690.

## 1. ልዩ ጊዜ — እሁድ፣ መስከረም 04

**ሀ. የሱስ ምልጃውን ጸሎት ሲያጠናቅቅ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የት ሄደ እና ለምን ዓላማ? ዮሐንስ 18:1፤ ማቴዎስ 26፡36**

**ለ. ሦስት ደቀ መዛሙርት አብረውት እንዲሄዱ ሲጠይቅ ጌታ ምን ጥያቄ አቀረበላቸው? ለምንስ? ማርቆስ 14:33፣ 34**

*"ሥርየት የማይቻል እስኪመስል ድረስ፣ በዚህም የጠፋውን ዓለም ለማዳን የፈለገ የእግዚአብሔር ልጅ በኃጢአት እርግማን ይደቅቅ ዘንድ የኃጢአትን መጠን ማብዛት (የሰይጣን) ዓላማ ነበር። የንቁ ጠላቶች መጠነ ሰፊ በደልን ለክርስቶስ በማቅረቡ ሥራው በጣም የሚያሳዝን ስቃይ ስለፈጠረ እርሱ በማንም ሰው ፊት ሊቀይ እንደማይችል ተሰምቶት ነበር። የዓለምን ወዮታ ሲያሰላስል ደቀ መዛሙርቱ እንኳ ስቃዩን እንዲመሰክሩት በፊታቸው መቀየት አልቻለም። በጣም የሚወዷቸው ጓደኞቹ እንኳን በዚህ ሁኔታ ከእርሱ ጋር መሆን የለባቸውም። የፍትህ ሰይፍ ከሰገባው ወጥቶ ነበር፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ቁጣ በአመጽ ላይ በሰው ምትክ በሆነው በአብ አንዲያ ልጅ በየሱስ ክርስቶስ ላይ ወረደ።"*—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 5, pp. 1102, 1103.

## ሀ. በጌቴሴማኒ የክርስቶስ የመጀመሪያ ጸሎት ፍሬ ነገር ምንድን ነው? ማርቆስ 14:35፣ 36

"በዚያ ወቅት የየሱስ ሁኔታ ከዚያ በፊት ከነበረው ፈጽም የተለየ ነበር። ነቢዩ«የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ ሰይፍ ሆይ ንቃ! የቅርብ ወዳጄ ሆኖ አብሮኝ በሚመራው በእረኛየ ላይ ተነሥ፣ » ሲል የተናገ ረው የየሱስን ሰቃይ በበለጠ አኳኋን ይገልጸዋል። ዘካ.13:7። የኃጢአተኛ ሰው ተወካይና ዋስ በመሆኑ ክርስቶስ መለኮታዊ ብያኔ የወሰነበትን ስቃይተቀበለ፣ ፍትሕ ምን እንደሆነም አየ። እስከዚያ ጊዜ ድረስ እርሱ ለሌሎች አማላጅ ነበር፣ አሁን ግን ለራሱ አማላጅ ቢያገኝ ምኞቱ ነበር።"

"ክርስቶስ ከአብ ጋር የነበረው አንድነት የተቋረጠ ስለመሰለው ከሰይጣን ጋር የሚያደርገውን ግብግብ ሰብአዊ ባሕርዩ መቋቋም ይሳነዋል የሚል ስጋት አደረበት። በምድረ በዳ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ የሰብአዊ ዘር የመጨረሻ እድል በስጋት ላይ ወድቀ ነበር። ነገር ግን ክርስቶስ ድል ነሳ። አሁን ደግሞ ፈታኙ የመጨረሻውን የሞት ሽረት ትግል ለማድረግ መጣ። ሰይጣን ለዚህ ትግል ክርስቶስ አገልግሎቱን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ለሶስት ዓመት ሲዘጋጅ ቆይቶአል። ለሰይጣን ሁሉም ነገር በሚያሰጋ ሁኔታ ላይ ሆነበት። በዚህ ትግል ሰይጣን ከተሸነፈ ጌታ የመሆን ተስፋው ይከሽፋል፤ የዓለም መንግሥታት የኋላ ኋላ የክርስቶስ ይሆናሉ፤ እርሱም ከሥልጣኑ ወርዶ የትም ይጣላል። በአንጻሩ በዚህ ትግል ክርስቶስ ቢሸነፍ ዓለም የሰይጣን ግዛት ትሆንና ሰብአዊ ዘር በሙሉ ለዘላለም በእርሱ ሥልጣን ሥርይወድቃሉ ማለት ነው። ከፊቱ ላይ የተደቀነው ትግል የሚያስከተለው ውጤት እጅግ ስላሳሰበው ከእግዚአብሔር የመለየት ስጋት መንፈሱን አስጨነቀው። ለኃጢአተኛው ዓለም ተያዥ ከሆነ ከእግዚአብሔር ለዘላለም መለየት የማይቀርለት መሆኑን ሳይጣን ለየሱስ ነገረው። ከእርሱ መንግሥት ጋር ስለሚቀላቀል ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ሊሆን አይችልም ማለቱ ነው።"—The Desire of Ages, pp. 686, 687.

## ለ. ከአስጨናቂው ጸሎቱ ሲመለስ፣ የሱስ ደቀ መዛሙርቱን በምን ሁኔታ አገኛቸው? ምንስ ተግሣጽ ሰጣቸው? ማርቆስ 14:37፣ 38

"በግንባሩ ተደፍቶ ይጸልይበት ከነበረው ቦታ በብዙ ጥረት ከተነሳ በኋላ እየተንገዳገደ ሶስቱን ደቀ መዛሙርት ትቶአቸው ወደመጣበት ቦታ ተመለሰ። ነገር ግን «በመጣ ጊዜ ተኝተው አገኛቸው።» ሲጸልዩ አግኝ ቶአቸው ቢሆን ኖሮ ከጭንቀት አሳብ በተገላገለ ነበር። የሰይጣን ኃይል እንዳያሸንፋቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ መከለያ ለማግኘት እንደሚሹ ቢያውቅ ኖሮ የእምነታቸው ጽኑነት የሱስን ባጽናናው ነበር። እነእርሱ ግን «ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ፣ »ብሎ በተደጋጋሚ የነገራቸውን ምክር አልተቀበሉም። ሁልጊዜ የረጋ መንፈስና ግርማ ሞገስ ያለው ጌታቸው ለማስተዋል ከማይችሉት የሐዘን ስሜት ጋር ሲታገል ባዩት ጊዜ መጀመሪያ ተጨንቀው ነበር። በስቃይ ላይ የነበረው ጌታ ሲጮህ በሰሙ ጊዜ ጸለዩ። እነዚህ ደቀ መዛሙርት ጌታቸውን ችላ የማለት ፍላጎት አልነበራቸውም ነገር ግን እግዚአብሔርን በመማጸን ቢቀጥሉ ሊወገድላቸው በሚችል እንቅልፍ ተሸነፉ። ፈተናን ለመቋቋም ነቅቶ የመጠበቅንና ከልብ የመጸለይን አስፈላጊነት አልተገነዘቡም ነበር።"—Ibid., p. 688.

## ሀ. የክርስቶስ ሁለተኛ ጸሎት ምን ነበር? ደቀ መዛሙርቱስ ምን እያደረጉ ነበር? ማቴዎስ 26:42፣ 43 በዚህም ፍጻሜውን ያገኘው የትኛው ትንቢት ነው? ኢሳይያስ 52:14

"ከጥቂት ጊዜ በፊት የሱስ እንደ ኃይለኛ የጥድ ዛፍ ቀጥ ብሎ ቆሞ የተሰነዘረበትን የተቃውሞ ማዕበል ሁሉ ለመቋቋም ችሎ ነበር። የእኛ አሳብ ካልተፈጸመ የሚሉና ልባቸው በተንኮልና በስውር ደባ የተሞላ ሰዎች እርሱን ለማደነጋገርና ለማሸነፍ ያደረጉት ጥረት ሁሉ አልተሳካም። መለኮታዊ ግርማ ሞገስ ተጐናጽፎ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አሳወቀ። አሁን ግን በኃይለኛ አውሎ ነፋስ እንደተንገላታና ለመውደቅ እንደ ዘመመ መቃ ሆነ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ የሱስ በየደረጃው የሰይጣንን ኃይል እያጠቃ በአሸናፊነት ወደ ሥራው መደምደሚያ ጊዜ ተቃርቦ ነበር። ክብር በመጐናጸፉም ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት እንደነበረው አሳወቀ። ፈራ ተባ ሳይል በእርግጠኛነት የውዳሴ መዝሙር አቀረበ። ደቀ መዛሙርቱን ያነጋገራቸው የማደፋፈርና የርህራሄ ስሜት በሚገልጹ ቃላት ነው። አሁን ግን የጨለማው ባለሥልጣን ሰዓት ደረሰ። በዚህ ጸጥ ባለው የምሽት ሰዓት የየሱስ ድምጽ በአሸናፊነት ቃና ሳይሆን ትልቅ ስቃይን በሚገልጽ አኳኋን ይሰማ ነበር።—The Desire of Ages, pp. 689, 690.

## ለ. በዚያ አስጨናቂ ሰዓት የአምላክ ልጅ የተጽናናው እንዴት ነው? ሉቃስ 22:43 ኢሳይያስ ስለ ክርስቶስ ጭንቀትና መጽናናትን የተናገረው በምን ዓይነት ቃላት ነበር? ኢሳይያስ 53:11

"ማንኛውም ነገርበአስጊ ሁኔታ ላይ በነበረበትና ምስጢራዊዩ ጽዋ በሚሰቃየው ጌታ እጅ ላይ በሚንቀጠቀጥበት በዚያች ቀውጢ ሰዓት ሰማይ ተከፍቶ ብረሃን ቦግ ሲል የሰይጣንን ቦታ የያዘውና በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው ኃያል መልአክ ክርስቶስን ለመርዳት መጣ። መልአኩ የመጣው ጽዋውን ከክርስቶስ እጅ ለመቀበል ሳይሆን እንዲጠጣው ለማበረታታትና የእግዚአብ ሔርን ፍቅር ሊያረጋግጥለት ነው። መልአኩ የመጣው መለኮትና ሰው ለሆነው ጸሎተኛ ኃይል ለመስጠት ነው። ወደተከፈተው ሰማይ በማመልከት በእርሱ ስቃይ ምክንያት ስለሚድኑት ነፍሳት ነገረው። በተጨማሪም አባቱ ከሰይጣን የበለጠ ኃይል ያለው እንደሆነ፣ በእርሱ ሞት ምክንያት የሰይጣን እቅድ እንደሚከሸፍና የዚህ ዓለም መንግሥት ለልዑል ቅዱሳን እንደሚሰጥ አረጋገጠለት። ከሰብአዊ ዘር ቁጥር ስፍር የሌላቸው ሰዎች ለዘላለም ስለሚድኑ የነፍሱን የድካም ፍሬ በማየት እንደሚደሰትም ገለጸለት።"—Ibid., pp. 693, 694.

## ሀ. የሱስን ያሰረውን ቡድን የመራው ማን ነበር? ዮሐንስ 18፡2-5

## ለ. የሱስ ራሱን ለእነሱ በገለጸ ጊዜ የተቆጡትን ሕዝብ ምን አጋጠማቸው? ዮሐንስ 18፡6

"የሱስ አሳልፎ የሚሰጠውን ለመገናኘት በወጣ ጊዜ ከጥቂት ጊዜ በፊት የደረሰበት ስቃይ ምልክት በፊቱ ላይ አይታይም ነበር። የሱስ ደቀ መዛሙርቱን አልፎ ሔደና ለመጡት ሰዎች «ማንን ትፈልጋላችሁ?» ሲል ጠየቃቸው። እነርሱም «የናዝሬቱን ኢየሱስ እንፈልጋለን፤» ባሉት ጊዜ «እኔ ነኝ፣» አላቸው። እነዚህን ቃላት በሚናገርበት ጊዜ ቀደም ሲል የሱስን ያገለግለው የነበረው መልአክ በእርሱና በሰዎቹ መካከል ጣልቃ ገባ። ወዲያውኑ መለኮታዊ ብርሃን በየሱስ ፊት ላይ ተንጸባረቀ፣ ርግብ የሚመስል ቅርጽም ዙሪያውን ከበበው። እነዚያ ነፍስ ገዳይ ሰዎች በዚያ መለኮታዊ ክብር ፊት ለአንዲት አፍታ እንኳ መቆም ስላልቻሉ ወደኋላ አፈገፈጉ። ካህናቱ፣ ሽማግሌዎቹ፣ ወታደሮቹና ይሁዳም ጭምር እንደሞቱ ሆነው በመሬት ላይ ተዘረሩ።

"ከዚያ በኋላ መልአኩ ገለል ስላለ ብርሃኑም ደብዘዝ እያለ ሔደ። በዚያ ወቅት የሱስ ማምለጥ ይችል ነበር፣ ግን ጸጥ ብሎ ያለ አንዳች መረበሽ ቆመ። ግርማ ሞገሱን ተጐናጽፎ አቅመቢስ ሆነው ከፊት ለፊቱ በወደቁት ልበደንዳና ሰዎች መካከል ቆመ። ደቀ መዛሙርቱ ጸጥ ብለው በመገረምና በፍርሃት ይመለከቱ ነበር።"—The Desire of Ages, p. 694.

## ሐ. የይሁዳ ክህደት በሕዝቡ ላይ ተጽዕኖ ያሳደረው እንዴት ነው? የየሱስ የዋህነት በጴጥሮስ በተሳሳተ መንገድ የተተረጎመው እንዴት ነው? ዮሐንስ 18:7-10፤ ሉቃስ 22፡47-50

"የሱስን ለመያዝ የመጡት አድመኞች ከጥቂት ጊዜ በፊት ክብር ተጐናጽፎ የነበረውን የየሱስን አካል ይሁዳ ሲነካው ባዩ ጊዜ የልብ ልብ ተሰማቸው። ስለዚህ እነርሱም ያዙትና ምንጊዜም ደግ ነገር ከመሥራት ተቆጥበው የማያውቁትን የተቀደሱ እጆቹን የማሰር ሥራቸውን ቀጠሉ።

ደቀ መዛሙርቱ ጌታቸው ዝም ብሎ የሚያዝ አልመሰላቸውም ነበር። ምክንያቱም ቀደም ሲል የሱስን ሊይዙ የመጡትን ሰዎች እንደ ሞተ ሰው በመሬት ላይ የረፈረፋቸው ኃይል የሱስና ተከታዮቹ ሸሽተው እስከሚያመልጡ ድረስ ሰዎቹን አሸመድምዶ ሊያቆያቸው ይችል ነበር።" የሚወዱትን ጌታቸውን እጆች ለማሰር የተዘጋጁትን ገመዶች ባዩ ጊዜ ሐዘንና ንዴት ተሰማቸው። ጴጥሮስ ስለተናደደ ፈጥኖ ጐራዴውን መዘዘና ለጌታው ለመከላከል በመሞከር የሊቀ ካህኑን አገልጋይ ጆሮ ቀረጠሙ።—Ibid., p. 696.

## 5. የወይኑን መጭመቂያውን ብቻውንመርገጥ ሐሙስ፣ መስከረም 08

### ሀ. የሱስ በተያዘበት ጊዜ ያሳየውን ታጋሽ ፍቅር ግለጽ። ማቴዎስ 26:51–53፤ ሉቃስ 22:50፣ 51 ሰማይስ እሱን እንዴት ተመለከተው?

*"ደቀ መዛሙርቱ ሕዝቡ ከነትራቸውና ከነሰይፋቸው በቅጽበት ወድቀው ሲያዩ ተስፋ ማድረግ ጀምረው ነበር። ነገር ግን ተነሥተው እንደ ገና የእግዚአብሔርን ልጅ ከበቡት፣ በዚህን ጊዜ ጴጥሮስ ሰይፋን መዘዘና የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ መትቶ ጆሮውን ቈረጠ። የሱስም፣ 'አባቴን እንድለምን እርሱም አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይቻል ይመስልሃልን?' በማለት ሰይፋን እንዲመልስ አዘዘው። እነዚህ ቃላቶች ሲነገሩ የመላእክት ፊት በተስፋ ሲፈካ አየሁ። ያን ጊዜም እዚያም አዛዦቻቸውን ከበው ያን የተቀጣ ሕዝብ ሊበትኑት ተመኙ። . . . የሱስ እሱን ጠላቶቹ እንድወስዱት በፈቀደ ጊዜ የደቀ መዛሙርቱ ልብ በተስፋ መቁረጥ ተሰበረ።*

*"ደቀ መዛሙርቱ ለነፍሳቸው ፈሩ፣ ሁሉም ትተውት ሸሹ፣ የሱስ በገዳዮቹ እጅ ብቻውን ቀረ። ለሰይጣን ኻረ እንዴት ያለ ድል ነው! ለእግዚአብሔር መላእክትስ እንዴት ያለ ሀዘን ይሆን! ብዙ የቅዱሳን መላእክት ማኅበር እያንዳንዳቸው ረጅምና አዛዥ መልአክ ያለው አጀብ ቦታውን ሁኔታውን ለመከታተል ተልከው ነበር። በእግዚአብሔር ልጅ ላይ የሚደርሰውን ማንኛውንም ስድብ እንዲሁም ጭካኔ መመዝገብ እና የሱስ ሊደርስበት የሚችለውን ጭንቀት ሁሉ መመዝገብ ነበረባቸው።"*—Early Writings, pp. 167, 168.

### ለ. የክርስቶስ ነን የሚሉ ሁሉ ጌታ ለጴጥሮስ ከሰጠው ምክር ምን መማር አለባቸው? ዮሐንስ 18:11፤ 1ኛ ዮሐንስ 3፡15

## የግል የግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ መስከረም 09

1. ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ያቀረበው ልመና በተለይ ለእኔም የሚሆነው የቱ ነው?
2. ጌታ በጌቴሴማኒ ያለው ተሞክሮ በእኔ ላይ እንዴት ተጽዕኖ ሊያሳድር ይገባል?
3. ጴጥሮስ የሱስ በተያዘበት ወቅት የሰጠውን ምላሽ ማስወገድ የምችለው እንዴት ነው?
4. ለክርስቶስ ጭንቀት ዋነኛው መንስኤ ምን ነበር?
5. ከመልአኩ ክብር ፊት ሲቆሙ ሕዝቡ ምን ሆኑ?

# ስምዖን ጴጥሮስ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “ጌታም። ስምዖን ስምዖን ሆይ፥ እነሆ፥ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና አለ።” (ሉቃስ 22:31, 32)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, vol. 5, pp. 331–336.

*“ጴጥሮስ የወደቀው በራስ ብቁነት ሀሳቡ ነው፤ እና እግሩ እንደገና የጸናው በንስሐና ራስን ዝቅ በማድረግ ነው ።”*—Christ’s Object Lessons, p. 155.

## 1. የጴጥሮስ ባሕርይ — እሁድ፣ መስከረም 11

### ሀ. ስምዖን መጀመሪያ ወደ የሱስ በመጣ ጊዜ መምህሩ ምን አለው? ዮሐንስ 1፡42 የጴጥሮስ ባሕርይ ከመለወጡ በፊት ምን እንደሚመስል እናውቃለን?

*“ስምዖን ሁለተኛ ጥሪ አልተጠባበቀም። እርሱም የዮሐንስን ስብከት አዳምጦ ነበርና ፈጥኖ ወደ መድኃኒታችን ሔደ። ጸባዩንና የሕይወት ታሪኩን በማንበብ ክርስቶስ ዓይኑን ጣለበት። ችኩልነቱን፤ አፍቃሪነቱን፤ ልበ ርኅሩኅ መሆኑን፤ ምኞቱን፤ በራሱ የሚተማመን መሆኑን፤ እንዴት እንደሚወ ድቅ፤ ንስሐ እንደሚገባ፣ ምን ሥራ እንደሚያከናውን፤ በሰማዕትነት እንደ ሚሞት በማንበብ መድኃኒታችን ትኩር ብሎ ተመለከተው።”*—The Desire of Ages, p. 139.

*“ጴጥሮስ ደካማ የነበረው ራሱን ጠንካራ አድርጎ ባሰበበት ወቅት ነበር፤ እና ደካማነቱን እስካላወቀ ድረስ በክርስቶስ መታመን እንደሚያስፈልገው ሊገነዘበው አልቻለም ነበር።”*—Ibid., p. 382.

### ለ. የሱስ በጴጥሮስ ላይ ጉድለት ያለበት ቢሆንምበ እንኳ ምን ግብዣ አቀረበለት? ማቴዎስ 4:18፣ 19

*“የእግዚአብሔርን ቅድስናና የራሱን ብቁ አለመሆን ካየ በኋላ ነበር ለኢሳይያስ የመለኮታዊ መልእክት አደራ የተሰጠው። ጴጥሮስም ለክርስቶስ እንዲሠራ ጥሪውን የተቀበለው እራሱን እንዲክድና በመለኮት ኃይል እንዲተማመን ከተደረገ በኋላ ነበር።”*—Ibid., p. 246.

## ሀ. ጴጥሮስ በጰንጠቆስጤ ቀን ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በኋላም ቢሆን እንደማንኛውም ሰው የሚሳሳት መሆኑን የሚያሳየው ምንድን ነው? ገላ 2፡11-14

“[ጴጥሮስ] ከአሕዛብ የተለወጡ ሰዎችን በተመለከተ ባሳየዉ አርቆ አስተዋይ (ጠንቃቃ) ባሕርይዉ የብዙዎችን እምነት አግኝቶ ነበር። በጊዜዉ ከሰማይ ባገኘዉ ብርሃን መሠረት ነበር ያደረገዉ። ተፈጥሮአዊ ጥላቻዉን በማሸነፍ ከአሕዛብ ከተለወጡት ጋር በአንድ ጠረጴዛ ተቀምጦም ነበር። ነገር ግን ለአይሁድ ሥርዓታዊ ሕግ የሚቀኑ የተወሰኑ ሰዎች ከየሩሳሌም በመጡ ጊዜ ጴጥሮስ ብልሃት በጎደለዉ (ፍሬ አልባ) በሆነ መንገድ ከአሕዛብ በተለዉጡት ላይ ጸባዩ ተቀየረ። የቀሩትም አይሁድ ደግሞ፥ ‘በርናባስ ስንኳ በግብዝነታቸው እስክሳብ ድረስ፥ ከእርሱ ጋር አብረው ግብዞች ሆኑ።’ በእነዚያ እንደ መሪ በተከበሩና በተወደዱ ሰዎች ላይ የታየዉ ደካማነት ከአሕዛብ በተለወጡ አማኞች አዕምሮ ዉስጥ እጅግ ሕመም የሚፈጥር አሻራ አሳርፎ ነበር። በዚህም ቤተ ክርስትያንቱም የመከፋፈል አደጋ ተጋርጦባት ነበር።”—The Acts of the Apostles, p. 198.

## ለ. ጴጥሮስ ከሰራው ስህተት እና ካደረገው ተሃድሶ ምን ትምህርት እናገኛለን? መዝሙረ ዳዊት 145:14

“ጴጥሮስ የወደቀበትን ስሕተቱን ተመለከተና ወዲያዉኑ ያለዉን ኃይል በሙሉ በመጠቀም ያንን ክፉ ነገር ለማስተካከል ተነሳ። ገና ከመጀመሪያዉ መጨረሻዉን የሚያዉቀዉ እግዚአብሔር ጴጥሮስ ይህን የባሕርይ ድክመቱን እንድገለጥ በመፍቀድ የተረጋገጠ ሐዋርያም እንኳን በራሱ የሚያኮራ ነገር እንደሌለዉ እንዲያዉቅ አደረገ። ምርጥ የሚባሉ ሰዎችም እንኳን ለራሳቸዉ ከተተዉ በዉሳኔ ላይ ይሳሳታሉ። የጴጥሮስ ውድቀት የተጻፈው እኔ በጴጥሮስ ቦታ የተተከው ነኝ በማለት ራሳቸውን ፍጹምና ኃጢአት ያልነካቸው የማይሳሳቱ አድርገው የሚያቀርቡ ራሳቸውን የሚያተልሉና ከሌሎች የተለየ እድል እንደተሰጠቸው እግዚአብሔር በጴጥሮስ ቦታ በማስቀመጥ ለእነርሱ ብቻ የተለየ ቦታ እንደሰጣቸው የሚናገሩ ሰዎች በቀጣይ ጊዜ እንደምመጡ ስላወቀ ነበር። . ይህ ተመዝግቦ የተቀመጠዉ የሐዋርያዉ ድክመት እርሱም ደካማና ከሌሎች ሐዋርያት በምንም እንደማይበልጥ የሚያሳይ ማረጋገጫ ነዉ።

“የዚህ ከትክክለኛ መርሆ የወደቀበት ታሪክ በእግዚአብሔር ሥራ ኃላፊነት ላይ ላሉ ሰዎች ከንጹሕ አቋማቸው ወይም ከታማኝነታቸው እንዳይወድቁ ነገር ግን መርሆን እንዲጠብቁ እንደ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ነው። አንድ ሰበአዊ ተወካይ ላይ ኃላፊነት ታላቅነትና የማዘዝና የመቆጣጠር አጋጣሚ ሰፋት መጠን፣ እርሱ በጥንቃቄ የጌታን መንገድ ካልተከተለና አጠቃላይ በአማኞች አንድነት መማክርት አካል ውሳኔዎች ጋር ተስማምቶ ካልሰራ የሚያመጣዉ አደጋ ታላቅ ነዉ።”—Ibid., pp. 198, 199.

## ሀ. የሱስ ስለ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ምን አለ? ማቴዎስ 16፡16-19

"ጴጥሮስ የተናገረው እውነት የምእመናን እምነት መሠረት ነው። ይህንኑ ነው ክርስቶስ ራሱ የዘላለም ሕይወት ነው ያለው። ነገር ግን የዚህ እውቀት ባለቤት መሆን ለራስ ማስከበሪያ ምክንያት አይሆንም። ይህ ነገር ለጴጥሮስ የተከሰተለት በራሱ ጥበብ ወይም ደግነት አይደለም። ሰብአዊ ፍጡር በራሱ ስለ መለኮት ፈጽሞ ማወቅ አይችልም። . . .

"ንግግሩን በመቀጠል የሱስ «አንተ ደንጊያ ነህ በዚችም ደንጊያ ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ። የገሃነምም ደጆች አይጉለብቱባትም፣» አለ። ጴጥሮስ የሚለው ቃል ትርጉሙ የሚንከባለል ድንጋይ ማለት ነው። ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን የሚመሠረትበት አለት ድንጋይ አልነበረም። ጌታውን በመማልና በመገዘት በካደው ጊዜ የሲኦል በሮች በእርሱ ላይ አሸናፊነትን አገኙ። ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው የሲኦል በሮች በማያሸንፉት በክርስቶስ ላይ ነው።"—The Desire of Ages, pp. 412, 413.

## ለ. ልክ እንደ ጴጥሮስ፣ ሌሎች ነቢያትና ሐዋርያት ስለ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ መሠረት ምን አሉ? ኢሳይያስ 28:16፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 3:11፤ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡3-6

"እግዚአብሔር፣ የሰማይ ነዋሪዎችና የማይታዩት የሲኦል ሠራዊት ሁሉ ባሉበት ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን በሕያው አለት ላይ መሠረታት። ያም ቋጥኝ እርሱ ራሱ፣ ማለትም ለእኛ ሲል የተሰበረውና የቆሰለው አካሉ ነው። በዚህ የመሠረት ደንጊያ ላይ የተመሠረተችውን ቤተ ክርስቲያን የሞት ኃይል አያሸንፋትም። . . .

"እምነት ለስድስት ሺህ ዓመታት በክርስቶስ ላይ ሲገነባ ቆይቶአል። እንደዚሁም ለስድስት ሺህ ዓመታት የሰይጣን የቁጣ ማዕበል የደህንነታችን መሠረት በሆነው አለት ላይ ሲጋጭ ኖሯል፣ ቢሆንም እምነት ጸንቶ ቀመ እንጂ አልተናጋም።"

"ጴጥሮስ የቤተ ክርስቲያን እምነት መሠረት ስለሆነው እውነት ስለተናገረ መላው ምዕመናንን እንደወከለ አድርጐ በማየት ክርስቶስ አከበረው። ስለዚህ «እነሆ ለአንተ የመንግሥተ ሰማይን መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፣ በምድር ያሰርከው በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የፈታኸውም በሰማይ የተፈታ ይሆናል፣» አለው።"

"«የመንግሥተ ሰማይ መክፈቻዎች፣» የተባሉት የክርስቶስ ቃላት ናቸው። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙት ቃላት ሁሉ የእርሱ ስለሆኑ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ተካትተዋል። እነዚህ ቃላት ሰማይን የመክፈትና የመዝጋት ኃይል አላቸው።"—The Desire of Ages, p. 413.

## ሀ. የጴጥሮስን ትልቁን የባህርይ ጉድለት ግለጽ። ማርቆስ 14:27-29

"በፈሪሳዊው እና በቀራጩ ለሚወከሉት ለእያንዳንዱ ክፍል በሐዋርያው ጴጥሮስ ታሪክ ውስጥ አንዳንድ ትምህርት አለ። ጴጥሮስ ቀዳሚ ደቀ መዛሙር በመሆኑ ራሱን ጠንካራ አድርጎ ያስብ ነበር። ልክ እንደ ፈሪሳዊው በራሱ ግምት 'እንደሌሎች ሰዎች' አልነበረም። . . ጴጥሮስ የራሱን አደጋ አላወቀም ነበር። በራስ የመተማመን መንፈሱ አሳሳተው። ፈተናን መቋቋም እንደሚችል አስቦ ነበር፣ ነገር ግን በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ፈተናው ሲመጣ፣ በእርግማንና በመሐላ ጌታውን ካደ።—Christ's Object Lessons, p. 152.

## ለ. የሱስ በራሱ የሚተማመን ደፋር የሆነውን ይህን ደቀ መዝሙር ያስተናገደው እንዴት ነው? ሉቃስ 22:31፣ 32

"የዶሮው ጩኸት የክርስቶስን ቃል ባስታወሰው ጊዜ ባደረገው ነገር ተገርሞና ተደናግጦ ወደ ጌታው ዘወር ብሎ ተመለከተ። በዚያን ጊዜ ክርስቶስ ጴጥሮስን ተመለከተ፣ ከዚያ ከኃዘኔታ እይታ መካከል ለእሱ ያለው ፍቅርና ርህራሄ የተቀላቀለበት መሆኑ ታየው፣ ጴጥሮስ ስለራሱ ተረዳ። ወጥቶም ምርር ብሎ አለቀሰ። ያ የክርስቶስ አስተያየት ልቡን ሰብሮታል። ጴጥሮስ ወደሚለወጠበት ደረጃ ደርሶ ነበር፣ ለኃጢአቱም መራራ ንስሐ ገባ። በጸጸትና በንስሐ እንደ ቀራጩ ሆነ፥ እንደ ቀራጩም ምሕረትን አገኘ። ያ የክርስቶስ አስተያየት ይቅርታን እንዳገኘ አረጋገጠለት።

"አሁን በራስ የመተማመን ስሜቱ ጠፍቷል። የድሮው የጉራ ቃልም ዳግመኛ አልተደገመም።""—Christ's Object Lessons, pp. 152–154

## ሐ. የሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ጴጥሮስን ምን ጠየቀው? ዮሐንስ 21፡15-17 የሱስ ይህን ሦስት ጊዜ የደገመው ለምንድን ነው? ጴጥሮስስ ምን ብሎ መለሰ? ሉቃስ 22:31፣ 32

"የ[ጴጥሮስ] ጌታውን መካድ ቀደም ሲል ካሳየው የታማኝነት ስሜት ጋር ሲነጻጸር አሳፋሪ ነበር። ጌታውን ስላሳፈረ ጓደኞቹ በጥርጣሬ ዓይን ይመለከቱት ነበር። ጓደኞቹ ሁሉ ቀደም ሲል የነበረውን ደረጃ መያዝ የለበትም የሚል አስተሳሰብ አደረባቸው፣ እርሱም እምነት እንዳጉደለ ተሰማው። የሐዋርያነት ሥራውን እንደገና ከመረከቡ በፊት ንስሐ መግባቱን በሁሉ ፊት ማሳየት ነበረበት። ምንም እንኳን ጴጥሮስ ኃጢአቱን ቢናዘዝም ንስሐ መግባቱን ካላስመሰከረ የክርስቶስ አገልጋይ የሆነ ሰው ሊኖረው የሚገባውን ጥሩ ስም እንዳይኖረው ያደርገው ነበር። ስለዚህ አዳኛችን ይህ ደቀ መዝሙር በጓደኞቹ ዘንድ የነበረውን አክብሮት እንደገና እንዲያገኝ ለማድረግና በወንጌል ላይ ላደረሰው ሐፍረት በተቻለው መጠን እንዲክስ እድል ሰጠው።"—The Desire of Ages, p. 811.

## 5. በአገልግሎቱ ተረጋገጠ
ሐሙስ፣ መስከረም 15

### ሀ. የደቀመዝሙርነት አንዳንድ ቁልፍ ባህሪያትን ጥቀስ። ቆላስይስ 1:10፣ 11፤ 3፡12–14። ክርስቶስ ጴጥሮስን ከያዘበት መንገድ ምን እንማራለን?

*"ወንጌል ከኃጢአት ጋር አይደራደርም፤ ለኃጢአትም ምክንያት አይፈልግለትም። ስውር ኃጢአትን በስውር ለእግዚአብሔር መናዘዝ፣ ግልጽ ኃጢአትን በግልጽ መናዘዝ አስፈላጊ ነው። በደቀ መዝሙሩ ኃጢአት ምክንያት የደረሰው ሐፍረት በክርስቶስ ላይ ያርፋል። ይህ ሐፍረት ሰይጣን እንዲያሸንፍና ወላዋይ ነፍሳት እንዲወድቁ ያደርጋል። ደቀ መዝሙሩ ንስሐ መግባቱን በማስመስከር በቶቻለ መጠን ይህን ሐፍረት ያስወግዳል።*—The Desire of Ages, p. 811.

*"አዳኛችን በጴጥሮስ ላይ ያደረገው ነገር ራሱ ጴጥሮስና ጓደኞቹ ጠቃሚ ትምህርት አግኝተውበታል። ሕግ የሚተላለፍን ሰው በትእግስት፣ በርህራሄና ይቅርታ በተሞላበት ፍቅር መያዝ እንዳለባቸው አስተ ምሮአቸዋል። ጴጥሮስ ጌታውን ቢክድም የክርስቶስ ፍቅር አልተለየውም። በክርስቶስ ሥር ሆኖ የክርስቶስን መንጋ የሚጠብቅ ሁሉ ለግልገሎቹና ለበጐቹ የዚህ ዓይነት ፍቅር ሊኖረው ይገባል። የራሱን ድክመትና ውድቀት በማስታወስ ጴጥሮስ ክርስቶስ ለእርሱ እንዳደረገለት እርሱም መንጋውን በእንክብካቤ እንዲይዝ ይጠበቅበት ነበር።*

*"ክርስቶስ ለጴጥሮስ ያቀረበው ጥያቄ መሠረታዊ ነው። ለደቀ መዝሙርነትና ለአገልግሎት ለመመረጥ መመልመያው ነጥብ አንድ ብቻ ነው። እርሱም «ትወደኛለህን?» የሚል ነው። ይህ ዋና መለያ ነጥብ ነው። ጴጥሮስ የተለያየ ችሎታ ቢኖረውም ያለ ክርስቶስ ፍቅር ለጌታ መንጋ ታማኝ እረኛ ሊሆን አይችልም ነበር። እውቀት! ምግባረ ሰናይነት፣ ኣንደበተ ርቱዕነት፣ አመስጋኝነትና ቀናኢነት ለጥሩ ሥራ ድጋፍ ሰጭዎች ናቸው። ነገር ግን የክርስቶስ ፍቅር በልቡ ውስጥ ከሌለ የወንጌል መልእክተኛው ሥራ የተሳካ አይሆንም።"*—Ibid., p. 815.

## የግል የግምገማ ጥያቄዎች
አርብ፣ መስከረም 16

1. እኔ እንደ ጴጥሮስ የራሴን ባሕርይ በተሳሳተ መንገድ እየተረዳሁ ይሆንን?
2. ጴጥሮስ ያሳየውን የባህርይ ጉድለት እንዴት ማስወገድ እችላለሁ?
3. ከጴጥሮስ ውድቀት እና መመለስ ምን ትምህርት ማግኘት እችላለሁ?
4. ክርስቶስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ክርስቶስ በወንድሞቹ ፊት ለጴጥሮስ አንድ ቁልፍ ጥያቄ መጠየቅ ያስፈለገው ለምንድን ነው? እኛስ ከዚህ ምን እንማራለን?
5. ክርስቶስ ቤተክርስቲያኑን የገነባበትን መሰረት አብራራ እና የመንግሥተ ሰማያትን ቁልፎች ለይተህ አውጣ።

# የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታዎች




## ሰንበት፣ ሰኔ 28

### በታሂቲ ለሚገኘው ለአሩ ቤተክርስቲያን

ራቅ ብላ በፓስፊክ ውቅያኖስ ላይ በምትገኘው በዚህች ደሴት ለእግዚአብሔር የብርሃን ማማ መኖሩ ምንኛ አስፈላጊ ነው! (ገጽ 3ን ይመልከቱ)



## ሰንበት፣ ሐምሌ 26

### ለጂ.ሲ. ትምህርት ክፍል

ውጤታማ ወጣት ሚስዮናውያን እውቀት ያላቸው መሆን አለባቸው። ሥርዓተ ትምህርታቸውን ማዘጋጀታችንን እንቀጥል! (ገጽ 24 ይመልከቱ)




## ሰንበት፣ ጳጉሜ 01

### ለትምህርት ቤት ማሠሪያ በማሆኮ፣ ሩዋንዳ

ልጆችን መጠበቅ እና ለጌታ ታማኝ ወንጌላዊያን እንዲሆኑ ማስተማር እጅግ አስፈላጊ ነው! (ገጽ 50 ይመልከቱ)